# ምዕራፍ ስድሳ ስምንት

## ያፄ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የቅርብ ግንኙነት

ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ያለ ምንም ማንገራገር በቅድሚያ መጥተው ላፄ ምኒልክ እንደ ገቡላቸው፣ ከዚያም የኢጣልያ ጦር በሰሜን ኢትዮጵያ ተስፋፍቶ የመጨረሻው ጦርነት በዓድዋ በኢትዮጵያ አሸናፊነት በተፈጸመበት ሰዓት ሁለቱ እንደ ታላቅና ታናሽ ወንድማማች እየተመካከሩ ሁሉንም ይሠሩ እንደነበረ በየሰነዱ ላይ ይነበባል።

ራስ በዛብህና ደጃዝማች በለው፣ ካባታቸው ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተጣልተው አዲስ አበባ በነሩበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ እንደ አማላጅ ሆነው፣ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልሰው ለመላክና ከንጉሡ አባታቸው እንዳንድ ጉልት ተቀብለው እዚያው ጐጃም እንዲቀመጡ ባሳሰቡዋቸው ጊዜ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተሰጠው መልስ እንደዚህ የሚል ነበር።

> "ይድረስ ኃበ ሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ጃንሆዬ የልጆቹንም ነገር የላኩብኝ ክቡር ማኅተምዎ ደረሰኝ። ጃንሆይ፣ ራስ ደጃዝማች እሰኝቼ ያልሆኑልኝን ዛሬ ጉልት ሰጥቼ በጥቂት ነገር እደሩ ብል ይሆናል? ትግሬም ዘምተን ሳለ እግዚአብሔር ደህና ቢመልሰን እንግዲህ እሰር እናሰርም፤ የታሰረውንም እንፈታለን ብለን ብጽዓት(ስለት) አድርገን መነጋገራችን እውነት ነው።...ለራሴ ብፈራ ነው እንጂ..እኔ ሰገዛ፣ ልጆቼ ታስረው ሊቀመጡ ወድጄ ነው?...አሁንም አንዱን ወደራስ መኰንን፣ አንዱን ወደ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ሰደው ባልደረባ ሰጥተው ያኖሩዋቸው እንደሆነ ነው እንጂ፣ ከኔ ጋራማ ተፈትተው መቀመጥ እንዴት ይሆናል?...."

በሁለቱም መካከል፣ የሁለቱን ወዳጅነት የሚያጠብቁት፣ ለሁለቱም እንደ ሽማግሌ አባት ተቆጥረው በዚህ ዘመን የሚከበሩት ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ ነበሩ። በዕድሜ የገፉ ባፄ ዮሐንስም ዘንድ በሁሉም የተከበሩ እንደነበሩ የሚታሰብ ነው።

በዳኝነትና በፍርድ ረገድ የንጉሠ ነገሥቱና የንጉሡ ግንኙነት በመከባበርና በመተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነበር ። በፍትሐ ብሔርም ፣ በወንጀልም አንድ ተራ ሰው ወይም መኰንን የተከሰሰ እንደሆነ ራሱ ቀርቦ ፣ በደረጃ ተራምዶ አፈ ንጉሡ ላይ በይግባኝም እንደ ተለመደው ወደንጉሠ ነገሥቱ ችሎት ይቀርባል ። ሆኖም ይህን ደንብ ጥሰው ከጐጃም አንዳንድ መኳንንት ወይም ተራ ሰዎች ወደ አዲስ አበባ እየመጡ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ላይ ክስና ወቀሳ የሚያቀርቡ አልጠፉም ። ከነዚህም አንዱ ብዙ ዘመን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጠቅላይ የጦር አለቃ የነበሩት ራስ ደረሶ ናቸው ። እርሳቸውም ወደ መጨረሻው ዘመን ስላረጁ ሥልጣናቸው ወደራስ ወርቄ ስለሔደና ከንጉሡ ጋር ስምምነት ስላጡ ፣ በመልእክት ወደንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ ልከው ኖሮ ዐፄ ምኒልክም ሁለታችሁም ቀርባችሁ ከኔ ፊት ተነጋገሩ በማለት ፈንታ ጉዳዩን እዚያው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንዲያዩላቸው ጽፈው ነበር ።

ለዚህም መልስ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለንጉሠ ነገሥቱ በ1889 ዓ. ም. በጻፉት ደብዳቤ ላይ ባንደኛው ፣

"... ጃንሆዬ የራስ ደረሶን ነገር የላኩብኝ ክቡር ማኅተምዎ ደረሰኝ ። እርሱ ዘንድሮ የሚያደርገው ነገር ሁሉ የጤና አይደለም ። ራስ ደረሶ አባቴ ነው እንጂ ሎሌዬ አልነበረም ። እኔ አብሮ የተጠመደ አብሮ ይፈታል ፤ አብሮ የበላ አብሮ ይሞታል ብዬ ፣ እርሱም ያዝንልኛል ፣ እኔም እረዳዋለሁ መስሎኝ ነበር ። እንዲህ እየሆነ አስቸገረኝ ። አሁንስ ጃንሆዬ በምክር ተሆነ ደብረ መዊዕም ዘጌም ቢሆን እሺ ፤ ከወደደው ላይ ይሁን"...

የሚል ይገኛል ። በ1890 ዓ.ም. በጻፉት ላይ ደግሞ ፣ "...ከእግዚአብሔርና ከጃንሆይ የሚሠወር የለም ። እየዋሉ እያደሩ ያገኙታል ። ሰይጣን አገብሮት* ነው እንጂ ፣ ምንም የሆነው ነገር የለም ነበር ። ዛሬም ይኸው ገባ ፤ ከልብ ታረቅነ..." ብለው ደምድመዋል ።

ሌላው ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ፣ ማመልከቻም እየላኩ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ያስቸግሩ የነበሩት ፊታውራሪ ውድነህ የሚባሉ ናቸው ። እርሳቸውም ከፈረንጆች ጋር በመኖር ጥበብ የገበዩ መሆናቸው በደብዳቤው ላይ ተጠቅሶ ይነበባል ። እኚህ ሰው በደላቸውን በዝርዝር ላዔ ምኒልክ ቢያቀርቡ ፣ ጥበበኛና የትልቅ ወገንም ቢሆኑ ዐፄ ምኒልክ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ተከሰሃል ናና መልስ ስጥ ማለት ቀርቶ ፣ እንደዚህ ብሎ ክስ አቅርቧልና ምክንያቱን እንኳ ጻፍልኝ ሳይሉ ክሳሹን የተደፈነ ደብዳቤ አሲይዘው ውድነህን ወደጐጃም

* አስቶት ለማለት ነው ።



መልሰው ላኩዋቸው ። ደብዳቤው የሚለውም እንደዚህ ብኋልና ቻለው ፤ እዚያው አንተ እንደ ዳኝነትህ አድርግለት የሚል መሆኑ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልስ ላይ ያስታውቃል ። በዚህም አያያዝ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ስለዚሁ ስለ ፊታውራሪ ውድነህ ጉዳይ መጋቢት 14 ቀን 1886 ዓ.ም. ላዔ ምኒልክ በጻፉት ደብዳቤ ላይ እንደዚህ ሲሉ መልሰዋል ። "ጃንሆዬ የላኩብኝ የፊታውራሪ ውድነህ ነገር ደረሰኝ ። ሁልጊዜ ይመቹኛልና እግዚአብሔር ያስመችዎ ። ጠላትዎን ዲያብሎስን አስሮ ከጻድቃን ከወዳጅዎ ጋር መንግሥተ ሰማይ ያግባዎ ፤ መንግሥትዎን ይባርክልዎ ፤ ከወዳጅዎ አይለይዎ" በማለት ከዘመሩ በኋላ ፣ ፊታውራሪው የበደሏቸውን በመዘርዘር መደምደሚያውን ፣ "እሺ ታርቄዋለሁ... ገንዘቡንም አልፈልገውም ...እሺ ጃንሆይ ፣ እንደ ላኩብኝ እችለዋለሁ" ብለዋል። ዐፄ ምኒልክ ፣ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ላይ የተሰነዘሩትን ክሶች እየመለሱ ወደ ራሳቸው ስለላኩላቸው ንጉሡ ልባቸው ተነክቶ ፣ "ከምኒልክ በፊት እግዚአብሔር የኔን ሞት ያስቀድመው" ይሉ እንደ ነበር ይነገራል ።*

ያዔ ምኒልክ ያገዛዝ ዘዴ ፣ ከዚህ ዐይነቱ ዓላማ አኳያ ጭፍራ ከለቃው ፣ ባላባት ከሕዝቡ ተስማምቶ በሰላም አገሪቱ ዕድገትና ሥልጣኔ እንድታገኝ እንጂ ፣ የራሳቸውን የሥልጣን ዕድሜ ለማቆየት ሲሉ ሌሎችን ለማጣላት አለመሻታቸውን ይጠቁማል ። ይህ ዓይነቱ የአስተዳደር ዘዴ ፣ ለዐፄ ምኒልክ ብዙ ታላላቅ የጦርና ያስተዳደር መሳፍንትና መኳንንት አስገኝቶላቸዋል ። በነዚህም አማካይነት ከመረብ ሻገር ካለው በስተቀር የኢትዮጵያን ጥንታዊ ግዛት በአንድነት አደላድለው ለማስተዳደር በቅተዋል ።

* ከደጃዝማች የማነ ሐለን የቃል ንግግር የተገኘ ።



ንጉሥ ተክለሃይማኖት አዲስ አበባ መጥተው ዘውዳቸውን ባስመረቁበት ጊዜ

ከፊሊክስ ሮሴር (ዲኒስ ዠራልድ)

# ምዕራፍ ስድሳ ዘጠኝ

## የራስ ዳርጌ ፣ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና የራስ መኰንን ሞት

### ሀ. የራስ ዳርጌ ሞት

ራስ ዳርጌ በ1892 ዓ.ም. መጋቢት 15 ቀን ዐረፉ ። ራስ ዳርጌ ዘራቸው ከዐፄ ልብነ ድንግል የወረደው የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከወይዘሮ ወሪጌ (የስልጤ ጉራጌ) የወለዱዋቸው የቀጥታ ልጃቸው ናቸው ። ዳርጌ የልጅነት ጊዜያቸውን በአንኮበርና በአንጐለላ ካሳለፉ በኋላ ፣ ሣህለ ሥላሴ በ1840 ዓ.ም. ሞተው ኃይለ መለኮት ሲነግሡ ፣ እርሳቸው ከታላቅ ወንድማቸው ከአቤቶ ሰይፉ ጋር ነበሩ ። ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ መጥተው ኃይለ መለኰትን አሸንፈው መርድ አዝማች ኃይሌን ሾመው ወደ ቤጌምድር እንደ ተመለሱ መርድ አዝማቹ ወንድማቸውን ሰይፉን ስላሰሩባቸው ዳርጌ ጐንደር ለአቤቱታ ወዳዬ ቴዎድሮስ ሔደው ነበር ። በመካከሉ ከመርዕድ አዝማች ኃይሌ በኋላ ለሸዋ ምስለኔ ሆነው በዛብህ ስለተሾሙ ፣ በዚሁም ሰይፉ "ከኛ ከመሳፍንቱ መካከል ሰው ጠፍቶ ነው ወይ በዛብህ የሚሾመው" ብለው አንኮበርን መውረራቸው ተሰማ ። ዳርጌም ለሰይፉ ልትሰልል ነው የመጣኸው ተብለው ታሰሩ ።

ዳርጌ ፣ ንጽሕናቸው ታውቆ ሲፈቱ ፍጹም ያዬ ቴዎድሮስ ባለሟል ሆኑ ። በጦርነት ላይ ዝግንነታቸው ፣ በጉግሥ ጨዋታ ጊዜ ዘንግ አወራወራቸው በቴዎድሮስና በመኳንንቱ ዘንድ ይደነቁ ነበር ። ዐፄ ቴዎድሮስም ከማፍቀር የተነሣ ዳርጌ በማለት ፈንታ ፣ "ዳሩ ወይም ዳርዬ" ይሉዋቸው ነበር ይባላል ።

መርድ አዝማች ኃይሌ በከዳት ተከሰው የታሰሩ ጊዜ ዳርጌን የሸዋን ግዛት ሰጥቸሃለሁ ብለዋቸው እጅ ከነሡና ከተዘጋጁ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የአቤቶ ዳርጌን የደመቀ ሠፈር ተመልክተው በነገሩ ስለሠጉበት አስጠርተው ፣ "ዳርጌ ፈራሁህ በጥንድ ጦር የሚስተውን ኃይሉን ሽሬ በነጠላ ጦር ደርበህ ሁለት ሰው የምትገድለውን አንተን በሸዋ ላይ አልሾምም" ብለው በሐቅና በግልጥ ከዷቸው ። ሥልጡኑ ዳርጌም "እንዴት ምነው" የሚል ሐተታ ሳያበዙ በዝምታ እሺ ብለው በትሕትና እጅ ነሡ ይባላል ።

በመጨረሻም ቴዎድሮስ ከዳተኛው በየጊዜው ቁጥሩ ስለበዛ ፣
ሰውን ሁሉ ጠርጥረው ፣ የትግሬን ፣ የቤጌምድርንና የጐጃምን ታላ
ላቅ መኳንንትና አማቾቻቸውን ምኒልክን ሳይተዉ በመቅደላ በግ
ዞት ያስቀመጡ ጊዜም ዳርጌንም የዚሁ የግዞት ዕድል አልማራቸውም ።
በመቅደላ በግዞት ከነበዓልጋዳ አርአያና ከነደጃች ብሩ ጐሹ ጋር እን
ዳሉ የእንግሊዝ ጦር በ1860 ዓ.ም. መጥቶ ዐፄ ቴዎድሮስን ካሸነፈ
በኋላ ፣ ሁሉም በየትውልድ አገሩ ሲገባ ዳርጌም ወደ ሸዋ ተመል
ሰው ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ተገናኙ ። በተገናኙ ጊዜ ምኒልክ ፣ "እር
ስዎ በቀጥታ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ስለሆኑ ንጉሥነቴን ለርስዎ
ልተውልዎ" ቢሏቸው ፣ "የለም አባታችን ሣህለ ሥላሴ አልጋቸውን
አውርሰው የሞቱት ላንተ አባት ለንጉሥ ኃይለ መለኮት ስለሆነ ፣
የነጋሢነት መስመሩ በዚያው ባንተ በኩል መውረድ አለበት"
ብለው እምቢ አሏቸው ይባላል ።[1]

ከዚያ ወዲህ እንደ ብዙዎቹ የኢትዮጵያ መሳፍንት በሥልጣን
አያያዝ ሳይጣሉ ዳርጌና ምኒልክ ከሠላሳ ዓመት በላይ እንደ አባትና
እንደ ልጅ ተማምነው ፣ ተደጋግፈው ጊዜያቸውን በሰላም አሳለፉ ።
ደጃች መሸሻ ሰይፉ በሸፈቱ ቁጥር ተቆጭና አስገቢ ፣ ዐፄ ዮሐንስና
ንጉሥ ምኒልክ በተቀያየሙ ጊዜ አማካሪ ፣ አወቃቃሽና አስማሚ
ነበሩ ።

ራስ ዳርጌ የደጃዝማች አስፋው ፣ የደጃዝማች ደስታ ፣ የፊታውራሪ
ሸዋረገድ ፣ የወይዘሮ ትሰሜ ፣ የወይዘሮ አስካለ ፣ የወይዘሮ ፀሐየ ወርቅና
የልጅ ጉግሣ አባት ናቸው ።[2] በዚህ ዐይነት ለንጉሠ ነገሥቱም
ለሁሉም እንደ አባት ሆነው አሩሲን አቅንተው ሰላሌንና አካባቢ
ውን በአስ ተዳደር ይዘው ሲኖሩ በ1892 ዓ.ም. በመጋቢት 15 ቀን
ዐርፈው ቤተሰቦቻቸው ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ፣ እቴጌ ጣይቱም ሐዘ
ንተኛ ሆነው ሰነበቱ ። የዚህንም ወሬ ንጉሠ ነገሥቱ ለንጉሥ ተክለሃ
ይማኖት ጽፈውላቸው ስለነበረ ፣ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የመጣ
ላቸው የማጽናኛ ቃል እንዲህ የሚል ነው ።

> ይድረስ ኃበ ሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ ምኒልክ . . . የራስ
> ዳርጌን ማረፍ የላኩብኝ ክቡር ማኅተምዎ ደረሰኝ ። እጅግ አዘንሁ ።

1 የሕይወት ታሪክ ፣ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ፣ ገጽ 86—87 ።

2 ጉልቈ ትውልድ ዘንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፣ ብ.ጌ.ማኅተመ ሥላሴ የዘር ግንድ
ይመልከቱ ።



> እኔስ ፊትም የሕማምዎን (የሕመማቸውን) ብርታት ሰምቼ እዛኹ
> እምሩን ጠይቅልኝና ና ብዬ ሰድጀው ነበር ። ደርሶ መጥቶ ድካማ
> ቸውን ነገረኝ ። እሰጊዜ ነፍስ አትለይም እንጂ መሸነፋቸውንስ ከዚ
> ህም ቀደም ሰማሁ እውነት ነው ። አሁንም ጃንሆይ ምንም የሁላችን
> አባት ቢሆኑ የልማዱን እግዚአብሔር ያጥናዎ ። እኔስ ጃንሆይ አት
> ምጣ ብለው ቢልኩብኝ ነው እንጂ እንኳን እንዲህ ያለ ነገር ሲሆን
> እንዲያውም ጃንሆይ ናፍቀውኝ እመጣለሁ ብዬ ነበር አሁንም የሐዘን
> ዳርቻ ያድርግልን ። በመጋቢት 27 1892 ቀን ዓ.ም.[1]

ስለ ሥርዓተ ቀብሩ ዝርዝር ታሪክ አላገኘንም ። ዕድሜያቸው
ወደ ሰማንያ ሳይጠጋ አይቀርም ።

ለ. የንጉሥ ተክለ ሃማኖት ዕረፍት

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የቀድሞ ስማቸው አዳል ነው ። ዘራ
ቸው ዘአባት በኩል ሲዘረዘር እንደዚህ ይሆናል ። የጐንደሩ ዐፄ
ኢያሱ አድያም ሰገድ (1674—1699) ታላቅ ወለተ እስራኤልን ሲወ
ልዱ ፣ ወለተ እስራኤል ምልምል ኢያሱን ፣ ምልምል ኢያሱ ከንግሥ
ሥት ምንትዋብ ታናሽ ወለተ እስራኤልን ፣ ወለተ እስራኤል የጐጃ
ሙን ባላባት ደጃዝማች ዮሴዴቅን አግብተው ታላቅ ራስ ኃይሉን ፣
ኃይሉ ድንቅነሽን ፣ ድንቅነሽ ደጃዝማች ጐሹን ፣ ጐሹ ደጃዝማች
ተሰማን ፣ ተሰማ አዳልን (ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን)[2] ይወልዳሉ ።
ደጃች ተሰማ አዳልን የወለዱዋቸው ወይዘሮ ምዕላድ ከሚባሉ ከነ
ዐፄ እስክንድር ከሚወለዱ የነጋሢ ዘር መሆኑን አለቃ ተክለ ሥላሴ
መዝግበውት ይገኛል ።[3] የተወለዱበትን ዓመተ ምሕረት አልጠቀ
ሱትም ። ሁኔታው ሲታይ ዐፄ ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው ቀደም ብሎ
ባለው ጊዜ (በ1830—ዓ.ም.) አካባቢ ይመስላል ።

አባታቸው ደጃች ተሰማ ፣ ባፄ ቴዎድሮስ ትእዛዝ ጭልጋ ዐርባ
እምባ ላይ ሲታሰሩ አዳልን ለደጃች ተድላ ኳሉ አደራ ሰጥተዋቸው
በዚያ ሲኖሩ ፣ በ15 ዓመት ዕድሜያቸው በዛብህን ከደጃች ተድላ ኳሉ
ቁባት ከወይዘሮ ጉዳዬ በድብቅ መውለዳቸው ስለ ተሰማ ወደ ደጋ
ዳሞት ጠለዛም ኮብልለው ሲኖሩ ፣ በኋላ ደጃች ተድላ ኳሉም ዐፄ ቴዎ
ድሮስም ሞተው ጐጃምን እነደጃች ንጉሤ ተድላ ፣ እነደጃዝማች
ደስታ ተድላ ሲገዙ ፣ አዳል በነዚሁ ውስጥ የጐልማሳነታቸውን

1 ከታላቁ ቤተ መንግሥት ከቀድሞ የጽሕፈት ሚኒስቴር ቤተ መዛግብት የተገኘ ።

2 የኢትዮጵያ ታሪክ ካፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ፣ ተ.ጻ.መ ገጽ 52
ያለውን የዘር ግንድ ተመልከት ።

3 የእጅ ጽሑፍ ፣ ገጽ 93

ጊዜ ባላምባራስ ተብለው አሳለፉ ። ከዚያ ደጃዝማች ደስታ ተድላ በቁራጭ አገርና በባላምባራስነት ስለ ወሰኑአቸው ፤ በዚሁ ተቀይመውና ሸፍተው ሲኖሩ ደጃች ደስታ ላዔ ተክለ ጊዮርጊስ አልገብርም ብለው የሸፈቱበት ሰዓት ነበርና ተክለ ጊዮርጊስ ለአዳል እህታቸውን ወይዘሮ ላቀች ገብረ መድኅንን ድረው የራስነት ማዕረግ ጨምረው በጐጃም ሾሟቸው ። ይኸም ሹመታቸው ባዔ ዮሐንስ ዘመን ከመጽደቁ በቀር በጐጃም ስማቸውን ተክለሃይማኖት አሰኝተው እንዳነገሷቸው በእምባቦ ከምኒልክ ፤ በሣር ወሀ ከደርቡሾች ጋር ያደረጉት ጦርነት ሁሉ በየታሪኩ ስለተጻፈ እዚህ መድገም አላስፈለገም ።[1]

ዐፄ ዮሐንስ እንደሞቱ ፤ ምንም ሳያንገራግሩ በ1881 ዓ.ም. ላዔ ምኒልክ ከገቡ ዠምሮ ፤ እስከሞቱ ድረስ በሁለቱ መካከል ምንም ዓይነት የቅያሜ ነቅዕ ሳይገባ ሁለቱ አዛዥና ታዛዥ ሆነው በስምምነት እንደ ወንድማማች በፍቅር ኖሩ ። ልጆቻቸው እነራስ በዛብህ ፤ እነደጃች በለው ከአባታቸው እየተጣሉ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ባባታቸው ላይ ክስና ወቀሳ ሲያቀርቡ ፤ በመጨረሻም እነራስ ደረሶም ፤ እነፊታውራሪ ውድነህ በጌታቸው ላይ "ተበደልን" እያሉ አቤቱታ ሲያቀርቡ በደብዳቤ ለማስማማትና ለማስታረቅ ከመሞከር አልፈው ምኒልክ በኃይላቸውና በንጉሠ ነገሥትነታቸው ተመክተው ፤ "ተክሰሃል ቅረብና ተነጋገር" ብለዋቸው አያውቁም ።

ይኸን ሁሉ የሚያውቁት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፤ ላዔ ምኒልክ በሚጽፉት ደብዳቤ "ጃንሆዬ ለኔ ሁልጊዜ እንደ ተመቹኝ ነው እግዚአብሔር ሁልጊዜ ያስመችዎ. . .ጃንሆይ እንደ ፈጣሪዎ እንደ ክርስቶስ ሰው አለማስቀየም ልማድዎ ነው" እያሉ ከመጻፍ ጋር ከሳሾቹንና ወቃሾቻቸውን እየተበለጡም ቢሆን ጉዳያቸውን ይፈጽሙ ነበር ። በንጉሠ ነገሥቱና በእርሳቸው መካከል የሚደረገው ጥንቃቄና መፈቃቀር አስደናቂና ሌሎች ምሳሌ ሊያደርጉት የሚገባ መግባባት ነበር ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጥር 3 ቀን 1893 ዓ.ም. በዕለተ ዓርብ በ4 ሰዓት ደብረ ወርቅ ላይ ዐርፈው ባስናዱት በመካነ ጐልጐታ በጳጳሱ በአቡነ ሉቃስ ጐን በታላቅ ሐዘን ተቀበሩ ።

ከልቅሶው ላይ ባለቤታቸው ወይዘሮ ላቀች ገብረ መድኅን

ንጉሥ አይቆጡ የቀረች መስሎዎ ፤
ዕዳዬን ከፍዬ እስትከተልዎ ።

1 የኢትዮጵያ ታሪክ ካዔ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ. ፤ ገጽ 43—44 ፡59—60 ።



ብለው ሲገጥሙ ፤ ልጃቸው ደጃዝማች ሥዩም (ወደፊት ራስ ኃይሉ) እንደዚህ አሉ ።

በተድላ በጐሹ ያልነበረ ነገር ፤
በክርሡ መቃብር ከአቡን መነጋገር ። *

አለቃ እንግዳ የዳሞት ሠዓሊ እንዲህ አሉ ።

ምን ይጠጣ ይሆን የነገው እንግዳ ፤
ጠጁ በእየራሱ በየዐይኑ ተቀዳ ።**

ተክሌ (ተክለ ሥላሴ) ደግሞ በበኩላቸው

እንግዲህ የምኔ የጌታ ወዳጅ ፤
እወሀ (እንባ) ይሰጣል ወይ እስመስሎ ጠጅ ።[1]

## ሐ. የራስ መኰንን ሞት

ባዔ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፤ በኢትዮጵያ የነበሩ መሳፍንትና መኳንንት በየራሳቸው የሕይወት ታሪካቸው ቢጻፍ ብዙ ነው ። በዚህ በ19ነኛው መቶ ዓመት መጨረሻ የሞቱትም ብዙ ናቸው ። በሸዋ በኩል እነደጃች ናደው ፤ እነደጃች ገርማሜ ፤ እነደጃች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣን ፤ እነራስ ጐበና መሞታቸው ሲታወቅ የሕይወታቸውን ታሪክ በትክክል አናውቀውም ። በትግሬም እነራስ አሉላ ፤ እነራስ ሐጐስ ፤ እነራስ ቢቶደድ ገብረ ኪዳን ፤ በቤገምድርም በላስታም ፤ በሰሜንም ፤ በአገው ምድርም እነራስ ወሌ ፤ እነራስ መንገሻ አቲከም ፤ እነዋግ ሥዩም ብሩ ፤ እነዋግ ሥዩም ጓንጉል ፤ እነራስ ወልደ ሥላሴ እንኳን ታሪካቸው የስማቸው ዝርዝር ብዙ ነው ።

በዚህ ምዕራፍ የታወቀውን የራስ መኰንንን አጭር የሕይወት ታሪክ እናወሳለን ። ባለፈው ከተጻፈው ከየታሪኩ ተለቅሞ ሲታይ እንደዚህ የሚል ነው ። አባታቸው የዶባው ባላባት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ፤ እናታቸው ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ሣህለ ሥለሴ ናቸው ። የተወለዱት ያባታቸው ግዛት በሆነው በጐላ ከተማ በደረፎ ማርያም ግንቦት 1 ቀን 1844 ዓ.ም. ነው ። ክርስትናም የተነሡትና

* አቡነ ሉቃስ ጐን ስለተቀበሩ ነው ። ደጃች ተድላና ደጃች ጐሹ ያላደረጉትን ለማለት ነው ።

** ሰው ሁሉ በዐይኑ ብዙ እንባ ማፍሰሱን ለመጥቀስ ይመስላል ።

1 የአለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፤ ገጽ 164

የመዝመሪያውን የወጣትነት ጊዜያቸውን ከወንድማቸው ከደጃዝማች
ኃይለ ማርያም ጋር ያሳለፉት በዚሁ በጎላ ነው ።

ዐሥራ ስድስት ዓመት ሲሞላቸው አባታቸው ለንጉሥ ምኒልክ
ሰጧቸው ። ከዚያ ጊዜ ዠምሮ የንጉሥ ምኒልክ የመዠመሪያ የእልፍኝ
አሽከር ፤ ከዚያም የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ ፤ ከፍ ሲሉ በጅሮንድ
ተብለው የንብረት ኃላፊና የከፍል ጦር ማዘዝ ዠመሩ ። ሐረርጌ
እንደገና በማዕከላዊው መንግሥት ሥር በዋለበት ጊዜ እነቢቶደድ
አጥናፌ ፤ እነፊታውራሪ ገበየሁ (ሻቃ አጥናፌ ፤ ሻቃ ገበየሁ)
ተብለው ሲዘምቱ ፤ እርሳቸው የዘመቱት በባላምባራስነት ማዕረግ
ነው ። ባላምባራስነት ከሻቃነት ብልጫ አለው ።

ንጉሥ ነገሥቱ ወደ ሐረር በሔዱበት ጊዜ አገሩን ለማስተዳደር
ከዚህ በፊት ጨርጨርንም ያቀኑት ትልቁ ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል*
ቢጠየቁ ፤ አለመፍቀዳቸው ታወቀ ። እርሳቸው አልፈቅድም ያሉት
ለልጃቸው ለቀኛዝማች መኰንን እንደሚሰጡላቸው ተስፋ አድርገው
ነበር ። በኋላ ግን ፤ ለባላምባራስ መኰንን የደጃዝማችነት ማዕረግ ጨም
ረው ሲሰጧቸው ፤ "የኔን መኰንን ትተው ለራሳቸው መኰንን ሰጡት
ወይ ጉድ !" አሉ ይባላል ።

የመኰንን ዕድል በገሃድ እየጐላ የሔደው ከዚህ ቀን ዠምሮ
ነው ። አገሩ ሰፊና ሀብታም ስለሆነ ከሸዋም ተወላጅ በቀር የት
ግሬ ፤ የጐጃምና የቤጌምድሩ ተወላጅ ሁሉ ቀድሞም የነበረው ከየ
አገሩም እየመጣ ገባላቸው ። ከዚህ በኋላ ለንጉሠ ነገሥቱ የወንድም
አሽከር ሆነው ከልብ ማገልገላቸው ፤ ወደ ኢጣልያ አገር ለመዠመ
ሪያ ጊዜ ተልከው መሔዳቸው ፤ ከዚያ ሲመለሱ በሐረር ላይ ጨርጨር
ተጨምሮ ራስ መባላቸው ፤ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ባለው ግንኙ
ነት በውጫሌው ውል ምክንያት ክርክር በተነሣበት ሰዓት እንደ
አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው መሥራታቸው ፤ ክርክሩ ወደ
ጦርነት በዞረበት ሰዓት በአላጌው ጦርነት ለአራት ራሶች የበላይ
አዝማች ሆነው መዋጋታቸው ፤ በመቀሌው የክቢ ጦርነት ብዙ
ጭፍራ አልቆባቸው ራሳቸው መቁሰላቸው ፤ ለመሞት ወደፊት ሲገፉ
በራስ አሉላ ጉተታ መዳናቸው ይነገራል ።ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በነበራ
ቸው ቅራኔ ፤ " ለኢጣልያኖች ያደላል ፤ ከነሱ ጋር መዋጋት አይፈል
ግም" የሚባለውን ክስና ወቀሳ ለማስተባበል መቀሌው ጦርነት ላይ

* ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣን የነቀኛዝማች መኰንን አባት የራስ ብሩ (አባ ይስ
ራው) አያት ናቸው ።



ሕይወታቸውን ለመሠዋት መቁረጣቸውን ንጉሠ ነገሥቱ እንዲያው
ቁላቸው ፈልገው ነበር ይባላል ።[1]

በመኰንን ልባዊ ታማኝነት ሳይሳካ ቀርቶ ነው እንጂ ፤ ኢጣልያ
ኖች የምኒልክን ኃይል ለማዳከም ምኒልክን ብትከዱ በሐረር ራስ መኰ
ንንን ፤ በትግሬ ራስ መንገሻን እናነግሣችኋለን በማለት ያላደረጉት ጥረት
የለም ። ከዓድዋ በፊት ራስ ወልደ ሥላሴና ልጃቸው ደጃዝማች ነጋሽ
ሸፍተው ሳለ ፤ ፊታውራሪ ዘውዴ ይዘው ወዳጄ ምኒልክ ከላኩዋቸው
ወዲህ ራስ ወልደ ሥላሴ አዲስ አበባ ሲቀሩ ፤ ነጋሽ ለራስ መኰንን ተል
ከው በሐረር ይኖሩ ነበር ። ጧት ራስ መኰንን ከቤታቸው ሲወጡ
ከፊትና ከኋላ በመኳንንት ታጅበው ቁጥሩ በበረከተ የጦር ሠራ
ዊት መካከል በበቅሎ ላይ ሲሔዱ ደጃዝማች ነጋሽ አይተው ፤ "እኔ
ነጋሽ ይኸን ያህል ጦር ይዤ ለምኒልክ አልታዘዝም ነበር" አሉ ።[2]
ይኸን ቃል በኋላም የኢጋሜው ባላባት ራስ ስብሐት ሐረር በ1896
ዓ. ም. በነበሩበት ሰዓት ደገሙት ይባላል ።[3]

በዚህ ዓይነት መተማመን ላይ እያሉ ንጉሠ ነገሥቱ የወለዱት ልጅ
ደጃዝማች ወሰን ሰገድ የልጅ ልጃቸው ደጃዝማች አስፋ ወሰን ስለ
ሞቱ ፤ ኢያሱም ሕፃን ስለሆኑ ራስ መኰንንን አልጋ ወራሽ ሊያደርጉዋ
ቸው ወስነው ነበር ይባላል ። ነገር ግን የአምላክ ፈቃድ ሳይሆን
ቀርቶ ወራሹ መኰንን ከአውራሹ ከምኒልክ አስቀድመው ታመው
በተወለዱ በ53 ዓመት ከ10 ወራት ከ12 ቀን በመጋቢት 9 ቀን
በ1898 ዓ. ም. ሐሙስ በ3 ሰዓት ቁልቢ ላይ መሞታቸውንና ሐረር
በጥምቀተ ባሕር ሚካኤል መቀበራቸውን ግራጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ
አጣርተው ማስታወሻውን አቆይተውናል ።

ከዚያ በዐፄ ምኒልክ ትእዛዝ ልጃቸው ደጃዝማች ይልማ ሐረር
ጌን ሲሾሙ ፤ ሁለተኛው ትንሹ ልጃቸው ደጃዝማች ተፈሪና መኳን
ንቱ የወጉን ዕቃ ይዘው በሚያዝያ 3 ቀን 1898 ዓ.ም. ከሐረር ተነ
ሥተው በዚሁ ወር 19 ቀን አዲስ አበባ ደረሱ ። ዐፄ ምኒልክም ፤ እቴ
ጌም ፤ መኳንንትና መሳፍንቱ ሠራዊቱ በተገኙበት በፍል ውሃ ሜዳ
ታላላቅ ድንኳን ተተክሎ ፤ ሥጋጃው ተነጥፎ ተቀምጠው ሲጠባበቁ
ከራስ መኰንን መኳንንት አንዱ የራስ መኰንንን ሥዕል ይዘው እያ
ለቀሱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን እየተራመዱ ሲጠጉ ፤ ዐፄ ምኒልክ

1 ዜናሁ ለራስ መኰንን ፤ ግራጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ ፤ገጽ 53
2 የሕይወት ታሪክ ፤ ብላታ ኅሩይ ወ.ሥ. ፤ ገጽ 46
3 ዜናሁ ለራስ መኰንን ፤ ግራጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ ፤ገጽ 70

ሳይታሰብ ከዙፋናቸው አፈፍ ብለው ተነሥተው የራስ መኰንንን ሥዕል ይዘው ከሚያለቅሱት ሰውዬ ወስደው "ወንድሜ ልጄ! ወንድሜ አገልጋዬ!" እያሉ አምርረው አለቀሱ ይባላል ።

በዚህ ጊዜ ከተገጠሙት ግጥሞች ውስጥ ፤

ዋ ዐፄ ምኒልክ እግዚአብሔር ያጥናዎ
በየበሩ ቋሚ ከልካይ ሞተብዎ ።[1]

ሲታሰር አየነው ብረቱ ሲመታ
ማን ዋስ አገኘና ሐረርጌ ተፈታ ።

ጃንሆይ ምኒልክ ጠጉራቸው ሳሳና በራ ገላጣቸው
እንግዲህ ምኒልክ ምን ራስ አላቸው ።

የሚሉ ይገኙባቸዋል ።[2]

---

1. ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 324
2. የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ. ኃ. ሥ. (9ነኛ እትም) ፤ ገጽ 137



# ምዕራፍ ሰባ

## የዓድዋ የሰባተኛው ዓመት የድል በዓል አከባበር

ከዓድዋ በፊት በተለይ ንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ከመቀዳጀታቸው አንድ ዓመት ቀደም ብሎ በ1881 ዓ. ም. ስመ ጥሩ የጦር አበጋዛቸው ራስ ጐበና ዐርፈዋል። እርሳቸውም የደቡብን ክፍለ ሀገር አብዛኛውን ያቀኑትና በ1870 ዓ.ም. የራስነት ማዕረግ ከራስ ዳርጌ ጋር የተቀዳጁትናቸው ። ከልጅነት ዠምሮ ያገለገሉዋቸው እስከ ጐንደር እስከ መቅደላ ግዞት ድረስ ያልተለዩዋቸው እነደጃዝማች ናደው ፤ እነደጃዝማች ወልዴ ገብርኤል አባ ሰይጣን ፤ እነቢቶደድ አጥናፌና ሌሎችም በሞትና በእርጅና ተገልለዋል ። ግማሾቹንም የዓድዋ የጦርነት ሜዳ አስቀርቷቸዋል ።

ዐፄ ምኒልክ ልባቸው፡ ከተንኮል ፤ ከቅናትና ከምቀኝነት ንጹሕ ስለሆነ ሰው ይዋጣላቸዋል ። አለቆችን በሙያና ባገልግሎት መምረጥ ፤ የተመረጡትን ያለ አድልዎ በሹመት ፤ በሽልማትና በማዕረግ ማሳደግ ልማዳቸው ነበረ ። ታላላቆቹ ቢሞቱ ወይም ቢያረጁ ሌሎች የሚተኩ ታላላቅ ባለሥልጣኖች በፍጹም አይገዳቸውም ። ስመ ጥሩው ራስ ጐበና ቢሞቱ ፊታውራሪ ገበየሁ ተተኩ ፤ ገበየሁ ዓድዋ ወድቀው ቢቀሩ ፤ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ተተኩ ። ምክራቸው ጽኑ እነደጃዝማች ገርማሜ ፤ እነፊታውራሪ ሀብተ ማርያም (የዝቋላው) ቢሞቱ አገው ምድሬው ራስ መንገሻ አቲከም ተተኩ ። በየሥፍራው የሚተኩ የጐደለውን የሚሞሉ በየክፍሉ በየቅርንጫፉ በቁም ነገር በታማኝነት የሚያገለግሉ ግርማ ሞገስ የተዋሐዳቸው አገር አቀፍ ባለሥልጣኖች የሞሉበት ዘመን ነበር ። የሠለጠነው የአውሮፓ ኃይል በጦርነት የተንበረከከውና ኢትዮጵያ የጥንቱን ስፋቷንና ገናንነትዋን መልሳ የተቀዳጀችው ፤ እነዚህና ሌሎችም መሰሎቻቸው በሰጡት አመራር ፤ ኅብረትና ታዛዥነት ነው ።

ከዓድዋ ጦርነት (1888 ዓ.ም.) እስከ ንጉሠ ነገሥቱ ሕመም (1900 ዓ.ም.) ድረስ ያለው የዐሥራ ሁለት ዓመት ጊዜ ኢትዮጵያ ከርስ በርስ ጦርነት የተላቀቀችበት ጊዜ ነበር ። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱና ተባባሪዎቻቸው ጊዜው በሚጠይቀው አስተዳደርና ውጣ

ውረድ ዕረፍት ሳያደርጉ አሳባቸውን ሁሉ የአውሮፓን ሥልጣኔ በኢ ትዮጵያ ወደ ማስገባት አዘነበሉ ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ የዓድዋን ሰባተኛውን ዓመት የድል በዓል በ1895 ዓ. ም. በአዲስ አበባ በደመቀ አኳኋን ለማክበር ዝግጅት ሲያደርጉ አዲስ አበባ ላሉትም ፣ ከየአውራጃው ለተሰበሰቡትም ለየመኳንንቶ ቻቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መልእክት አስተላለፉ ።

ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና እኔም ይኸንን በዓል እንዲህ አድርጌ ማክበሬ እናንተንም ማድከሜ እግዚአብሔር በቸርነቱ ሰባት ዓመት *ሙሉ በዕረፍትና በጤና ስላኖረን ፣ ስለዚህ ነገር ማክበር ይገባናል ብዬ ነው እንጂ ለጥጋብና ለትእቢት ሠራዊት በዛ ነፍጥ (የጦር መሣሪያ) በረከተ ለማለት አይደለም ። ነገር ግን በዚህ በየሥራው ነገር በእንጨት ፣ በደንጋይ የማደክማችሁን አትመልከቱ ።** ይልቁንም እኔን ስታጡ (ስሞት) ብርቱ ኀዘን ያገኛችኋል ። አሁንም ወንድሞቼ ወዳጆቼ የማናቀው መከራ እንዳያገኘን እንዳይመጣብን በዚህ ነገር ደስ አይበላችሁ ።*** እግዚአብሔር እንዳይለየን አብሮ እንዲያስበን እኔም አዝናለሁ ፤ እናንተም እዘኑ ።[1]

የመታሰቢያው በዓል እንዲከበር የተወሰነው የዓድዋ ጦርነት በዋለበት ፣ ፈረሰኛው ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስ ለድሉ ረድቷል ተብሎ በሚታመንበትና የጊዮርጊስ በዓል በሚውልበት በየካቲት 23 ቀን 1895 ዓ. ም ነበር ። በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ባለው አደ ባባይ ለንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን መቀመጫ ፣ግራና ቀኝ ለእቴጌ ጣይቱ ላቡኑ ለአቡነ ማቴዎስና ለእጨጌው ለእጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ለመ ሳፍንቱና ለመኳንንቱ ፣ ለውጭ አገር ዲፕሎማቶችና ቆንሲሎች መቀ መጫ ፣ ለባለሚሎች መቆሚያ ሲደለደልና የተደለደለውም በልዩ ልዩ ሥጋጃና ምንጣፍ ሲለብስ ስንበተ ። ለመኳንንቱ መቀመጫና ለባለሚ ሎቹ መቆሚያ የተዘጋጀው ርዝመቱ ሁለት መቶ ክንድ ፣ ስፋቱ መቶ ሃምሳ ክንድ መሆኑን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ያወሳሉ ።

ዝግጅቱ ካለቀ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በወርቅ ያጌጠ ከፋይ ካባና ላንቃ ለብሰው ፣ በወርቅ የተከፈፈ ባርኔጣ እንዳደረጉ በዚሁ በየካቲት 23 ቀን የጊዮርጊስ ዕለት ከጧቱ በአንድ ሰዓት ደርሰው በተዘጋጀው ዙፋን ተቀመጡ ። የቀሩትም በእልፍኝ አስከልካዮችና በአጋፋሪዎች አስተናባሪነት ሥፍራ ሥፍራቸውን ያዙ ።

* 1888—1895 ልዩነት ሰባት ዓመት

** ለሕንፃ ፣ ለመንገድ ፣ ለልማት ሥራ በማስጋዝና አቅርቡ በማለት

*** በዚህ ሰልፍ በመመካት ልባችሁ አይታበይ

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 306



ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የሰልፉን ቅደም ተከተል ሲጽፉ የጦሩን አለቃ ፣ የማዕረጉን ደረጃና የጦር ሠራዊቱን ቁጥር ከመጥቀስ በቀር የመሪዎቹን ስም አልጠቀሱም ። የጸሐፌ ትእዛዙን ጽሑፍ መሠረት ሳይለቁ ሌሎች የውጭ አገር ሰዎች የጠቀሱትን አሟል ተው ሙሴ ሞሪስ ደኮፔ ያሰላለፉን ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበውታል ።

፩ኛ. የገሙና የቦረና የሶዶ ፣ ያማያና የጨቦ ገዥና ዋናው የጦር አበጋዝ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የፈረስ ስማቸው አባ መቻል 30,000 ባለጠበንጃ አሰልፈው እንዳማረባቸው አለፉ ።

፪ኛ በእናርያ (ሊሙ) እና በከፋ የተሾሙት የንጉሠ ነገ ሥቱ አክስት የወይዘሮ አያህሉሽም ልጅ የራስ ወልደ ጊዮርጊስን አሰላለፍ ገብረ ሥላሴ እንደዚህ ሲሉ ገል ጠውታል ። “እናርያንና ከፋን የሚገዛው ራስ የንጉሡ (የምኒልክ) ወንድም ፈረሱን ቀንድና ቀንድ አድርጎ (ፈረሰኛውን በሰልፍ አስተካክሎ) እምቢልታው መለ ከቱ ፣ ነጋሪቱ ሆኖ ከመኳንንቱና ከአደጉ (ጀሌ) በቀር 32,000 ነፍጥ (ጠበንጃ) ያስያዘው እጅግ አምሮ በዝቶ ታየ ። ባለብሩ ባለወርቅ ጣፋ ጋሻ በፀሐዩ ፀዳል (ብርሃን) ዐይን ለማየት ያስቸግራል ። የሱ ሰው በብር ካጌጠው በወርቅ ያጌጠው ይበልጣል ። ”

፫ኛ. ጕማን የሚገዙት አፈ ንጉሥ ነሲቡ 15,000 ባለጠበንጃ አሲዘው አለፉ ።

፬ኛ. ያፈ ንጉሥ ነሲቡ ትልቁ ልጃቸው ደጃዝማች ደምሰው* የነቢቶደድ መኩንን አባት የወለጋና የጉድሩ ገዥ 30,000 ባለብረት እንዳሰለፉ አለፉ ።

* ደጃዝማች ደምስ (በኋላ ራስ) አሽከር ለማሳደግ ጦር ለማደራጀት ፣ ግብር ለማብላት ሽልማት ለመሸለም የራሳቸው ገንዘብ እያነሣቸው ከሰው ይበደሩ ነበር ይባላል ። ከሞቱ በኋላ ላርባቸው ኑዛዜ ሲፈስ ባለዕዳዎች ቢቀርቡ መኳንንቶቻቸው ጌታችን ባለዕዳ የሆኑት ለኛ ያበሉትና ያጠጡት የሸለሙበት እኮ ነው ዝም ትላላችሁ ብለው ከሥጋጃው ላይ የወረወሩት ገንዘብና ወርቅ ቢቆጠር ከዕዳው እጥፍ ሆኖ ቤተሰብ ተከፋፈለው ይባላል ።

፭ኛ. ያሩሲና የባሌው ገዥ ደጃዝማች ሉል ሰገድ የፈረስ ስማቸው አባ በላይ ፣ ሉሉ መልከ መልካም ፣ ቁመናቸው ዠርጋዳ የእቴጌ መነን ሁለተኛ ባል ፣ በዚህ ጊዜ ባሌንና አሩሲን ሲያስተዳድሩ 15,000 ጦር አሰልፈው አለፉ ።

፮ኛ. የሉሜና የከምባታው ገዥ ደጃዝማች አባተ የፈረስ ስማቸው አባ ይትረፍ 20,000 ጦር ።

፯ኛ. የሲዳሞው ገዥ ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ 10,000 ባለጠበንጃ ።

፰ኛ. የፋጅና የዲርማ ፣ የጃማ፣ የሚዳና የደራው ገዥ ራስ ወልዴ የፈረስ ስማቸው አባ ሥዩም 15,000 ጦረኛ ።

፱ኛ. የይፍራታና የግድም ፣ የቀወትና የጥሙጋ ገዥ ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ (የራስ ወለዶ ልጅ) 9,000 ወታደር ።

፲ኛ. የጉላ አገረ ገዥ ደጃዝማች ውቤ የፈረስ ስማቸው አባ ታደግ የንግሥት ዘውዲቱ ባል የነበሩት 9,000 ጦር እንደያዙ ፡

፲፩ኛ. የንጉሠ ነገሥቱና የእቴጌይቱ አዛገሮች አዛዥ ዛማኤል (ዘአማኑኤል) እና አዛዥ በዛብህ ባንድነት 10,000 ባለጠበንጃ ።

፲፪ኛ. የወሎና የወረሂመኖ ፡ የሳይንት የቦረና ገዥ ራስ ሚካኤል 70,000 ወታደር ።

፲፫ኛ. የኢሉባቦርና ገባ ከሚባለው ወንዝ ማዶ ያለውን ሁሉ የሚያስተዳድሩት ራስ ተሰማ ናደው 30,000 ።

፲፬ኛ. የጐፋና የሸንጋማ አስተዳዳሪ ደጃዝማች ለማ አቦዬ (የራስ ወልደ ጊዮርጊስና የደጃዝማች በሻህ ወንድም) 12,000 ጦር አስከትለው አለፉ ።[1]

ጸሐፌ ትእዛዙ በዚህ ታላቅ የሰልፍ ትርዒት ዘየአውራጃው ርቀት የተነሣ የሐረርና የውጋዴን ፣ ከጨጨሆ በላይ የባምብሎ እስከ

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ. 71 ገጽ 304—312. Chronique --- De Menelik 500—505



ወፍላ ፣ የትግራይ ፣ የጐጃም አስተዳዳሪዎችን አለመጨመራቸውን ካመለከቱ በኋላ ፣ በትርዒቱ ላይ የመድፍና የጠበንጃው ተኵስ ጢስ የፈረሱ አጉዳ (ኮቴ) አቧራው ባንድነት ሲነሣ ዠምበሯን እንደ ሐምሌ ጉም እንደ ሸፈናት ወታደሩም ጉራዴና ሰይፉን እየመዘዘ በፉከራ ሲጮህ በተኩስ ጢስ ጸዳል ጮራ ያረፈበት ባሕር መምሰሉን አብራርተዋል ። መደምደሚያውን ዐፄ ምኒልክ ዘበኛቸውን ይዘው በነፍጡና በመድፉ ተኵስ እጅግ በሚያስደንቅና በሚያስፈራ ግርማ ለሕዝብ ማሳየታቸው ፣ "እግዚአብሔር አያምጣብን እንጂ ፣ ሌላም ጠላት ቢመጣ እንደዚህ አድርጌ እረዳችኋለሁ አጠቃላችኋለሁ" ብለው ፣ ለሕዝባቸው ለማስረዳት መሆኑን ጠቅሰው አልፈውታል ።

# ክፍል ስድስት

## የንጉሠ ነገሥቱ መታመም

## ምዕራፍ ሰባ አንድ

### ዐፄ ምኒልክ በሕመም መውደቅ —
### የጀርመን ወኪሎችና ሐኪሞች ችግር መፍጠር

ዐፄ ምኒልክ ፥ ከ1857 እስከ 1881 ዓ.ም. የሸዋ ንጉሥ በመሆን ፥ ከ1882 እስከ 1906 ዓ.ም በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት በገዙበት ዘመን፥ ዘውስጥም ፥ በውጭም አንድም ጊዜ የመሸነፍ ውርደት ሳይገጥማቸው በሕዝብና በወታደር ዘንድ እንደ ተወደዱ ኖረዋል ። የአውሮፓን ሥልጣኔ በየዘርፉ ላገራቸው ለማስጨበጥ ብዙ ድካምና ጥረት አድ ርገዋል ። እኚህ ገናና ንጉሠ ነገሥት በ1900 ዓ.ም. መጨረሻ በሚያ ዝያ ወር ላይ ሕመም አድሮባቸው በታመሙ ጊዜ ከሁሉ በፊት የመረ መራቸው ዶክተር ቪታሊያ የሚባለው የሞሪሸስ ተወላጅ ፥ ከኩላሊት መበላሸት የተነሣ የደም እመታታቸው ልክ አለመሆኑን ተገነዘበ ። ሕመማቸው ስለጸና በዚሁ ዓመት በሰኔ ወር ላይ የሰውነታቸው አጋማሽ በድን ሆነ ። ከዶክተር ቪታሊያ ቀጥሎ ያከማቸው ዶክተር ተርሚኒዬ የሚባለው የፈረንሳይ ሐኪም ምንም የማዳን ውጤት ሳያሳይ ስለቀረ ፥ ይሻላቸው ይሆን በማለት ከግቢ ወደ እንጦጦ አዛውረው ከዚያም ወደ ደብረ ሊባኖስ ለጠበል ወስደው ቢያጠምቋቸው ፥ እንዲያውም ከቀድሞ መባሱን የተመለከተው ዶክተር ተርሚኒዬ ጠበሉን በግድ አስተወና ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በቤተ መንግሥታቸው ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱና ልጃቸው ወይዘሮ ዘውዲቱ እያስታመሟቸው ተቀመጡ ።

በዚህ ጊዜ ፥ አልፎ አልፎ ኢትዮጵያዊው ዶክተር ማርቲን (ሐኪም ወርቅነህ) ሲያከሙዋቸው ውጤት አልባ ስለሆነ ፥ አዲስ አበባ በሚ ቀመጠው በጀርመን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር በዶክተር ፍሬዲ ሪክ ሮዘን አማካይነት ለዳግማዊ ውልሄልም የጀርመን ንጉሠ ነገ ሥት ተጻጽፈው ፥ ዶክተር አልፍሬድ ሴንትግራፍ በሕክምና ላይ አማ ካሪ ለመሆን ፥ ዶክተር ማክስ ስቴንኩሀለር በተለይ ለሕክምና መጥተው ማከም ዠመሩ ።

ይኸው ስቴንኩሀለር የሚባለው ሐኪም ፥ "በንጉሥ ነገሥቱ ላይ የሥራ ሥርና የጅማት መተሳሰርና የሰውነት መጨማደድ ይታይባቸዋልና በሙቀትና በመታሸት ሊሻላቸው ይችላል" ብሎ በመዝመሪያ በእጁ እያሸ ትንሽ የመሻል ምልክት እንዳሳዩ ፥ በመጨረሻም የኤሌክትሪክ መታሻ መሣሪያ አስመጥቶ ዘዴውንም ላስታማሚዎች አሳይቶ ሳለ ፥ "የበሽታው መነሾ ልዩ ሰበብ (መርዝ በመብላት?) አለውና ያንኑ ብቻ ማከም ነው" ብለው እንደ ተቃወሙት ፥ እቴጌ ጣይቱም ፥ "ዕድሜው ከ60 ወይም ከ40 ዓመት በላይ ለሆነ ሰው የኤሌክትሪክ መታሸት እንደማይጠቅመው አንድ ሐኪም ነግሮኛል" ብለው እንደ ተቃወሙትና በመካከሉም በአሠራር አለማወቅ የማሻው ኤሌክትሪክ እንደ ተበላሸ ፤ ጥዋት በኤሌክትሪኩ መሣሪያ ታሽተው ወደ ማታ ሲያዩዋቸው ደክመውና ዝለው ዐይናቸው ጨላልሞ የደም አመታታቸው ሰንፎ ፥ እንዳገኛቸውና በጠቅላላው ሰውነታቸው ተመርዞ ስላገኘው ፥ "በጥዋት ሽንታቸው ይላክልኝ" ቢል ወደ ማታ አቆይተው እንደላኩለት ፥ ያንንም ቢመረምረው "ሲያንካሊ" በሚባል ከሁሉ በከፋ መርዝ እንደተነደፉ ፥ ይኸም የመጣው ከመጠጥና ከመብል መሆኑን በተወው ማስታወሻ ይገልጣል ። አሳቡም ወይ በቸልታ አለዚያም ሆነ ተብሎ መርዝ ያለበት መብል አብልተዋቸዋል ወደ ማለት ነው ።[1]

በዚህም ብዙ ውዝግብ በሐኪሙና በእቴጌ እንደዚሁም ፥ በእስስታማሚዎቹ መካከል ከተፈጠረ በኋላ በመጨረሻ ዘንቲግራፍና ሐኪሙ ስቴንኩሀለር ፥ "እኛ ለማዳን ስንደክም ሌሎች ሥራችንን የሚያበላሹብን አሉ ። ከነዚህም መካከል የገንዘብ ሚኒስትሩን በጅሮንድ ሙሉጌታንና የግቢ ሚኒስትሩን አዛዥ መታፈሪያን ጠርጥረናቸዋልና ከግቢ ካልተወገዱ አንሠራም" የሚል ክርክር በከንቲባ ገብሩ አስተርጓሚነት አቀረቡ ። ንጉሠ ነገሥቱም ፥ እቴጌ ጣይቱም በኅብረት ፥ "እነዚህ ሁለት ባለሥልጣኖች ከልጅነት ዠምሮ በቤተ መንግሥታችን አብረውን የኖሩ በፍጹም የማንጠረጥራቸው ታማኞቻችን ናቸውና አይወጡም" የሚል መልስ ቢሰጡም ሐኪሞቹ እምቢ አሉ ። እቴጌም "ጃንሆይ የሚመገቡት ከኔው ቤት በጥንቃቄ እየተዘጋጀ እየመጣ ነውና እነዚህ ሰዎች መዳኒት ከመብል ጋር የሚወዷቸውን ንጉሠ ነገሥት ያበላሉ ተብሎ አይጠረጠርም" ብለው ቢያባብሏቸው ፥ "እነሱ ካልወጡልን እናከምም ወዳገራችንም እንመለሳለን" ስላሉ ፥ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ንጉሠ ነገሥቱም እቴጌም ለጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት ለመጻፍ ተገደዱ ።

1. ከትልቁ ቤተ መንግሥት መዝገብ ቤት የተገኘ ሰነድ



ሞዓ አንበሳ . . . ከዳግማዊ ዊልሄም የአልማንያ (አሌማኝ)ንጉሠ ነገሥት ሰላምታ . . . የከበሩ ንጉሠ ነገሥት በቸርነትዎ ሐኪሙን ዶክተር ስኪያንክለርን ፥ ለምክር የሚረዳንን ዶክተር ዲንትግራፍን ሰደዱልን ። በመምጣታቸውም እኔንም ሠራዊቴንም ደስ ብሎን ነበር ። ነገር ግን ሐኪሙ እንኳን መድኃኒት አድርጎ ሊያድነኝ በብዙ ሁከትና በብዙ ድካም ከረምሁ ። እኔ የማምናቸውን እነሱ ካልወጡ ብለው ዶክተር ዳንቴግራፍ እኔ አልኖርም አሰናብቱኝ አለ ። ሐኪሙም እነሱ ካልወጡ መድኃኒት አላደርግም አልገባም ብሎ ሁለቱም ጻፉልኝ ። እኔም የነዚህ ሰዎች ነውራቸው ሳይገለጥ ሳይረቱ እንዴት ይወጣሉ አልኩ ። እነሱ ግን ካልወጡ አንኖርም አሉኝ ። እነዚህስ አይወጡም ብዬ እሺ ብዬ አሰናበትኩ ።

ክቡር ወዳጄ መንግሥትዎ የውነተኛ ፈራጅ መሆኑን አምናለሁና ይህ ነገር ተመርምሮ እንድሰማው ተስፋ አለኝ ። ይህንን ሁሉ ያረገና ሁከት ነገር ያመጣ የኔ ዜጋ የጀርመንን ቋንቋ የሚያውቅ ሰው ነው *

እሱንም እኔ እንዳልመረምረው በባንዲራ ወስደው ከጀርመን ሌጋሲዮን ቤት አስቀምጠውታል ። ሹሜ ነው ዜጋዬ ነው ወደኔ ስደድልኝ ብለው የጀርመን መንግሥት ሚኒስቴር ደስም አላለው ። የግድም እንዳላመጣው የጀርመንን መንግሥት ማስቀየም ይሆንብኛል ብዬ አሰብሁ ። እሱም ከሰው ጋር ይምጣና ከዚያው ከመንግሥትዎ አብሮ ይመርመር ። ይኸንን በብዙ ማፍቀርና ማመን ነገሩ ተገልጦ እንድንሰማው እለምንዎታለሁ ።

የሆነውን ነገር ሁሉ ገልጦ የሚያስረዳ ግን ፥ የእቴጌ (ጣይቱ) ደብዳቤ ነውና ከዚያ ላይ ይገኛል ። ለስም (ለርስዎ) ዕድሜና ጤና ለሕዝብዎ ሰላምና ዕረፍት እንዲሰጥ እግዚአብሔርን እለምናለሁ ። ነሐሴ 21 ቀን 1901 ዓ.ም. አዲስ አበባ ተጻፈ ።

እነዚህ ፤ አንደኛ ለተንኮመረው የልማት ሥራ እንደ ቆንሲልም ሆኖ በምክር ይረዳል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ዶክተር ሴንትግራፍ በቀጥታ ለሕክምና ከመጣው ከስቴይንኩህለር ጋር በመተባበር በጊዜው የነበሩትን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሩንም ሚስተር ሮቤርቶ ቪለር ሳይቀር ወደነሱ አሳብ በማስተባበር በሰው ቤት በማያገባቸው ጉዳይ እየገቡ ፥ "እገሌና እገሌን እንጠራጠራቸዋለን ከቤተ መንግሥት ይወገዱ ፤ እነሱም ካልተወገዱ እንሠራም ፤ እናከምም ፤ ወዳገራችን እንመለሳለን" እያሉ በውቀታቸው በመመካት ማስቸገራቸው ሚኒስትሩ ቬለርም ዜጎቹን በመግሠጽ ፈንታ መተባበሩ አሳዛኝ ነው ።

ለዚህ አድራጎት ንጉሠ ነገሥቱም ፥ እቴጌይቱም እጥፉ ያደረጉት በጀርመን ሌጋሲዮን እንደ ወዳጅና እንደ አስተርጓሚ ሆነው የሚሠሩትን

* ከንቲባ ገብሩን ማለታቸው ነው ።

ከንቲባ ገብሩን ነው ። እርሳቸውም በኋለኛው ዘመን እንደ ተገነዘብነው ምሑር ፣ ላገር አሳቢና ኢትዮጵያም እንድትሠለጥን የሚደክሙ ሆነው ሳለ ፣ ምንም ከጀርመኖቹ ጋር አብሮ ብዙ ዘመን በመኖር ቢወዳጁም ፣ በዚያን ሰዓት ከወገኖቻቸው ተለይተው ከነዚያ ጋር ያስተባበራቸው ሰበቡ በግልጥ አይታወቅም ። ምናልባት ከበጅሮንድ ሙሉጌታና ከአዛዥ መታፈሪያ ጋር በግል ጉዳይ ተጣልተው ተቀያይመው ይሆናል ።

የሆነ ሆኖ ፣ በሕመምተኛው ንጉሠ ነገሥትና በእቴጌይቱ ዘንድ አዲስ ከጀርመን ጋር የተወጠነው የወዳጅነትና የንግድ ግንኙነት እንዳይበላሽ ብዙ ጥንቃቄ እየተደረገ ጉዳዩ በራስ ቢቶደድ ተሰማና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በቢቶደድ ኃይለ ጊዮርጊስ በኩል እንዲመረመር ከታዘዘና ራስ ቢቶደዱም ፣ ቢቶደድ ኃይለ ጊዮርጊስም በደብዳቤ ጥሪ ቢያደርጉላቸው ሴንትግራፍ ፣ “ስብሰባው ወዴት ነው? ሰብሳቢው ማነው? ሰዓቱ ስንት ነው?” እያለ ከማደናበር ጋር ፣ “ከጃንሆይ ሙሉ ችሎት ላይ ካልሆነ በቀር አልነጋገርም” ብሎ ገተረ።

ከዚህ ሁሉ ውዝግብ በኋላ ነው ንጉሠ ነገሥቱም ለጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት የጻፉት ። ከዚያም የበለጠ እቴጌይቱ አብራርተው ከዚህ እንደሚከተለው ጽፈው ላኩ ።

ይድረስ ለክቡር ወዳጃችን ከዳግማዊ ዊልያም የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ፤

የተላከ ከእቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ ።

ሰላምና ጤና ለእርስዎ ይሁን ።

በብዙ ማክበርና በትሕትና ይህንን ደብዳቤ ልጽፍልዎ አሰብሁ ። ስለዚህ ይህንን የደረሰብኝን የሚያሳዝን ነገር ደፍሬ ልጽፍልዎ የግድ ሆነብኝ ልታገሠው አልተቻለኝምና ። ስለ አጤ ምኒልክ ጤና መጉደል ጌታዬን ወዳጄን እጣቸው ይሆን ብዬ አጥብቄ ተጨንቄያለሁ ። ለሴቶች ካባት ካናት ከልጅ ከወንድምም የጮኛ (ባል ) ነገር ጭንቅ እንደሆነ የታወቀ ነው ። ስለዚህ የጀርመን መንግሥት ሐኪም የጥበብ ረቂቅ ብልሃት ሰመ ጥሩነቱ እስከኔ ደርሶ ንጉሠ ነገሥቱ ተፈውሰው እንደ ቀድሟቸው ሆነው ለማየት የተቃጠለ ምኞቴ እንዲፈጸምልኝና በብርቱ አጥብቀ ለሚወዳቸውም ሕዝባችን ንጉሡ በሕይወት እንዲቆዩለት ለመፈወስ የሚያስፈልግ ነገር ሳይደረግላቸው እንዳይቀር ብለን የጀርመንን ሰመ ጥሩን የጥበብ ረቂቅ ብልሃት ረዳትነት ለመንን ። ንጉሥም በቸርነትዎ ሐኪሙንም ምክር የሚረዳንንም ይስደዱልን ያልነውን ዶክተር ዲንትግራፍን ጨምረው ሰደዱልን ።

እነሱም በመምጣታቸው እኛንም ሠራዊታችንንም እጅግ ደስ አለን ። ነገር ግን እንደ ተመኘነው ሳይሆንልን ቀረ ። አለመሆኑንም ለማስረዳት ከዚህ ቀጥሎ በሚጻፈው ቃል አስታውቃለሁ ።



ሐኪም ዶክተር እስቴንኩለር በሚያዝያ በ2 ቀን ገቡ ። ከዚያም አንሥቶ እስከ ግንቦት 15 ቀን ጠዋት ማታ እየተመላለሱ ለንጉሥ መድኃኒቱን ሲያደርጉ ሰነበቱ ። በግንቦት በ15 ቀን ግን በንጉሠ ነገሥቱ ደም የመርዝ ፍሰጋ አገኘሁ ይጠንቀቁ ብለው ለእኔ ነገሩኝ ።

እኔም ዐፄ ምኒልክ መርዝ ማን ያደርግባቸዋል ፤ ይህ ነገር አይጠረጠርም አልሁ ።

ሐኪሙም ከወጥቤት ዕቃም ከምንም ከምን ዕድፍ መጠንቀቅ ነው አለ ። የከበሩም እጮኛዬ ሕመምዎ ከጀመረዎ ቀን አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ የዛሬው ሰዓት በኔ ዘንድ የተወደደ ስለሆነብኝ ያለእረፍት በብርቱ ትጋትና ጥንቃቄ ከብቤ ጌታዬን የማስታምም እኔ ራሴ ነኝና የሐኪምን ትእዛዝ ሁሉ መፈጸሙን ተደላድዬ ማስረዳት የሚቻለኝ ስለሆነ ፣ ይህንንስ እሺ የሚሰናዳውም ምግብ ሁሉ ከኔ ቤት ነው አልሁ ።

ከዚያም ወዲህ ዳግመኛ መርዝ አገኘሁ ብለው አልነገሩኝም ። እንደ ፊተኛው መድኃኒቱን ሲያደርጉ ቆዩ ። ዶክተር ዲንትግራፍም እሳቸው ያሉትን ሁሉ አድርገን ለሳቸው የሚያመቻቸውን ማለፊያ የተሰናዳ ቤት ሰጥተን አክብረን አስመችተን አኑረናቸው ነበር ። በሐምሌ በ5 ቀን ግን ዶክተር ዲንትግራፍ ሐኪሙን ይዘው መጥተው የኛ መኳንንቶችና ሠራዊት ከተሰበሰበበት በንጉሡ ክፉ ነገር ተደርጉባቸዋልና በብርቱ የታመኑትን አገልጋዮቻችንን እጃቸውን ተይዘው ይመርመሩ ፤ ይህ ካልሆነ ሐኪሙ ገብተው መድኃኒት አያደርጉም ብለው ከለከሉ ። በበነጋውም ዶክተር ዴንትግራፍ ከንጉሥ ልገናኝ ብለው ላኩ ። እኛም እሺ ብለንና ሁሉታችንም አንድ ላይ ሁነን ጠራናቸው ። እሳቸውም እነዚህ እጃቸው ተይዘው ይመርመሩ አሉ ። የታመኑ አሽከሮቻችን ናቸው አይጠረጠሩም እጃቸው ተይዘው የሚመረመሩት ምንድነው ብንላቸው ተይዘው ካልተመረመሩ ሐኪሙ አይገቡም አሉ ።

ደግሞ በበነጋው ምኒስትሩን ሙሴ ቮሌርን ጠርተን ንገሩን ብለን ብንጠይቃቸው ፣ በንጉሥ ምግብ ውስጥ መርዝ ተገኝቷል በመብልና በመጠጥ ውስጥ ሆኖ ንጉሡን አልጐዳቸውም እንጂ ሐኪሙ አግኝተዋል ብለው ነገሩን ።

እኔም ለምኒስትሩ ንጉሥ የሚመገቡት ሁሉ የሚሰናዳ ከኔ ቤት ነው ፤ የኔ ሹሞች ናቸው የሚያሰናዱ ። እነዚህ ሰዎች ግን ከእኔ ቤት በምንም በምን አይደርሱም ብዬ አስታወቅሁ ። ንጉሡም እነዚህ ሰዎች በዚህ ነገር አይጠረጠሩም ሥራቸው አይደለም ብለው ተናገሩ ።

ሕዝቡም ዐፄ ምኒልክን እንደነፍሱ እንዲያውም ከነፍሱ አልቆ እንዲያፈቅረዎ ንጉሥም በሕዝቡ አክብሮትና አፍቅሮት መከበብዎን ተደላድዬ ዐውቃለሁና ይህንን ሥራ በሕይወታቸው ላይ ሊሠራባቸው ማንም የሚችል ሰው የለም ።

ሚኒስትሩ ግን ፣ ምንም ቢሆን እነዚህ ሰዎች ካልወጡ አይህንም ንጉሡን የሚጠብቅ ሐኪሙ ሌላ ሰው መርጠው ያግቡ አሉ ።

ሐኪሙም እንደዚሁ እነዚህ ሰዎች ካልወጡ አልገባም ብለው ቀሩ ። እኔም በዚህ ነገር እኔን የሚጠብቅ ሌላ ሹም መቀበሉ ታላቅ ሽክም ሆነብኝ ።

በገዛ ሰውነቴ ላይ መርዝ በማድረግ መጠርጠር አይቻልምና ደግሞ የዚያኑ ለት ማታ ዶክተር ዲንትግራፍ እነዚህን ሰዎች ካልተሻሩና ካልወጡ እኔ አልቀመጥም ብሰው የሰጠናቸውን ቤት ለቀው ሔዱ ።

እዚያም ከሔዱ በኋላ ፣ እነዚህ ሰዎች ካልወጡ እኔን አሰናብቱኝ ብለው ወደ ንጉሥ ወረቀት ጻፉ ። ንጉሥም አንተም ልሰናበት ያልክበት እነዚህስ ሰዎች የሚወጡበት ብልሃት ካልተገለጠ እንዴት ይሆናል አንተው ይመርመሩ ባልክበት ነገር በ20 ሐምሌ ማክሰኞ እንድትመጡ ብለው ላኩባቸው ።

በዚያው ለነሱ ባስታወቅንበት ቀን አባታችን አቡነ ማቴዎስም በከተማም ያሉት ሐኪሞች ፣ የኛም መኳንንቶች ሁሉ ተሰብስበው ከ4 እስከ 6 ሰዓት ሲጠብቁ ውሰው እነሱ ሳይመጡ ቀሩ ።

የተሰበሰበውም ሰው በየቤቱ ገባ ። ዶክተር ዲንትግራፍም ዳኛውስ ማነው ሥፍራውስ ወዴት ነው ብለው ሳይመጡ ቀሩ ። ሐኪሙም እነዚህ ሰዎች ፈጽመው ካልተከለከሉ እኔ አልገባም ። ደግሞም ስገባ እኔ የምወደውን አስተርጓሚ ይዤ ነው የምገባ ። ውሌ ይህ ነው ብለው ወረቀት ጻፉ ። በዚህ ምክንያት ወደፊትም እንዲያስታምሙልን እርዳታቸውን ለመፈለግ የማይመችን የማይመስለን ሆነብን ።

ደግሞ ሦስተኛ እነዚህ ሰዎች ከዚህ ተከልክለው ወደ ሌላ አገር ካልሔዱ እኔ አልኖርምና አሰናብቱኝ ብለው በራስ ቢቶደድ ተሰማ እጅ ወረቀት ላኩ ።

ንጉሡም እኔም በነዚህ ሰዎች በሹመት ነገር ሌላ የተመቀኛቸው ሰው ተነሥቶ አስወጡልን ያላቸው ሰው ይኖር ይሆን እነያዚም ከመጡ ጥቂት ቀን ነው አገሩን አያውቁት ፤ ሰዉን አስመዱት ፤ ከነሱም ጋር ጠብ የላቸው ፤ ይህ ነገር ምን ይሆን ብለን ገረመን ።

ከዚህ በኋላ ፤ ይህ ካልሆነ አሰናብቱኝ ብለው ሦስት ጊዜ ወረቀት ላኩ ። ከዚህማ ወዲያ አላሰናብትም አሉኝ ብለው ወደ መንግሥታቸው የላኩ እንደሆነ የከበሩ ንጉሠ ነገሥት ወዳጄ ይቀየሙኛል ብለው ለዶክተር ዲንትግራፍ ይመርመሩ ብትሉ እሺ ብለን ቀን ቆርጠን ብናስታውቃችሁ ሳትመጡ ቀራችሁ ።

እኔ የማምናቸውን ያሳደጉኋቸውን የሾሙኋቸውን ሹማምንቶቼን ከዚህ ወጥተው ወደ ሌላ አገር ካልሔዱ ከነሱ ጋር ለመኖር አይሆንልኝም ብለህ መሰናበትህን ከወደድህ እሺ አሰናብቼሃለሁ ብለው ጻፉለት ።



በዚህ በኛ ዘንድ ያሉት ምኒስትሩ ሙሴ ቮለር ግን መልካም ሰው ናቸው ። ዳሩ ግን ነገሩን መርምረው ለኛ ባለማስታወቃቸው አዘንን ። ስለሆነም ፣ የተመኘነውን ፈቃዳችንን ለመፈጸም ብለው በታላቅ ቸርነትዎ ላደረጉልን በጎ አድራጎት እኔው ራሴ በፍጹም ልቤ ግርማዊ ሰውነትዎን አመሰግናለሁ ። ይህንን ሁሉ ነገር መጻፋችን እነሱን ለማዋረድ ብለን አይደለም ። የንጉሡ ልቡና እንዳይቀየምብን ብለን ነው እንጂ ። ዳሩ ግን አንድነት የሚያዋህደንን ታላቁን ፍቅራችንን ለማሰናከል ይህ ትንሽ ነገር ምክንያት ይሆናል ተብሎ አለመጠርጠሩ ግልጥ ነገር ነው ። የንጉሡ ፈቃድም ቢሆን ከዚህ በኋላ ሁሉንም ነገር ለሚጠይቃቸው ምላሽ የሚናገሩ ከኛ ዘንድ መልክተኞች ለመስደድ እንመኛለን ።

ነገሩ ብዙ ስለሆነ በወረቀቱ አይጠቀስልምና ። ፊት ከሙሴ ሮዘን ጋር መጥተው የነበሩት ሐኪም ሐንስ ቮልብረሽት ለእኔም መድኃኒት አድርገውልኝ አድነውኝ ነበርና ዛሬም ለጥቂት ቀን እንዲመጡልን እንለምናለን ።

የከበሩም ንጉሠ ነገሥቱም በቸርነትዎ ይሰዱልናል በማለት ተስፋ እናደርጋለን ። ለእርስዎ ዕድሜና ጤና ለሕዝብዎም ሰላምና ዕረፍት እንዲሰጥልን እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

ነሐሴ 15 ቀን 1901 ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ተጻፈ ።

መቼም በዘመኑ በንጉሠ ነገሥቱ ሕመም ላይ ግማሹ ፣ ‘‘በልጅ ኢያሱ የተገዙ ሰዎች ድመት አርደው ደንቃራ ጥለው አሳመሟቸው ፤ እቴጌ ጣይቱ ሥልጣን ለመጨበጥ ሲሉ መድኃኒት አደረጉባቸው’’ ሲሉ የቀረው ደግሞ ፣ ‘‘ሁሉም ውሸት ነው ንጉሠ ነገሥቱ ያገራችን መብልና መጠጥ እንዳይበሉ ሐኪሞች ከከለከሉ በኋላ ፣ ሕመምተኛው ለባለቤታቸው የዶሮ ወጥ በእንጀራ አማረኝ ስላሉ ፣ እቴጌይቱ በርኅራኄ የንጉሠ ነገሥቱን አምሮት ለመፈጸም በእቴጌይቱ ፈቃድና ትእዛዝ የተዘጋጀውን የዶሮውን ወጥ ከበሉ በኋላ ፣ በደም ሥራቸው ውስጥ መርዝ መስሎ የታያቸው ሐኪሞች በከንቱ እቴጌይቱንም የቅርብ አስታማሚዎቹንም ጠረጠሩ’’ ማለት ነው ።

# ምዕራፍ ሰባ ሁለት

## የንጉሠ ነገሥቱ ሥጋትና ዝርዝር ምክር — የልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት የራስ ተሰማ ናደው እንደራሴነት

ንጉሠ ነገሥቱ ሕመም እንደ ጸናባቸና እርጅና እንደ ተጫናቸው በተረዱት ጊዜ ፥ አሳባቸውና ሥጋታቸው "ያስተካከልሁት የኢትዮጵያ አንድነት ይፈርስ ይሆን? በዙሪያዬ በኔ ሰበብ በንጉሠ ነገሥትነቴም ምክንያት ባንድ ሥልጣን የተሳሰሩት መሳፍንትና መኳንንት እኔ ስሞት ተከፋፍለው በመዋጋት በኢትዮጵያ አንድነት ላይ አደጋ ይመጣ ይሆን?" የሚል ነው ። ይኸን ሥጋት የጣለባቸው ከዘመነ መሳፍንት ዠምሮ ሳያቋርጥ እስከ ዘመናቸው የደረሰው የርስ በርስ ጦርነት ነው ።

ለዚህ ሁሉ ሥጋታቸው መፍትሔ ብለው ያመኑበት ፥ አንደኛ በጽሑፍ አዘጋጅተው ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ የሚያቀርቡት ዝርዝር ምክር ፤ ሁለተኛ ከርሳቸው ቀጥሎ በዙፋኑ የሚቀመጠው አልጋ ወራሻቸው ልጅ ኢያሱ መሆኑን በግልጽ ማስታወቅ ነው ። ኢያሱን የመረጡበት ምክንያት ግልጽ ነው ። ከወይዘሮ ጌጤ የተወለደ ደጃች ወሰን ሰገድ የሚባል ወንድ ልጅ ነበራቸው ። እንዲሁም ከልጃቸው ከወይዘሮ ሸዋረጋና ከደጃዝማች ወዳጆ ጐበና የተወለደ በደጃዝማችነት ማዕረግ ያከበሩት አስፋ ወሰን የሚባል በእናት የልጅ ኢያሱ ታላቅ ወንድም ነበር ። ዳሩ ግን ፥ ሁለቱም ቀደም ብለው ስለሞቱ አሁን በሕይወት ያሉት ኢያሱና ወይዘሮ ዘውዲቱ ናቸው ። ምንም እንኳን ዘውዲቱ ከወይዘሮ አብቺው የተወለዱ በቀጥታ ልጅ ቢሆኑም ፥ በጾታ በኩል ሴት ስለሆኑና በተለይ ለነጋሢነት ለወንድ ልጅ ቅድሚያ ስለሚሰጥ ፥ ዘውዲቱ ልጃቸው እያሉ ዘውዱ ለልጅ ልጃቸው ለኢያሱ እንዲተላለፍ ያደረጉት በጾታ ልዩነት ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው ።

ስለዚህ ፥ አልጋ ወራሻቸውን ከማስታወቃቸው በፊት መሳፍንቱንና መኳንንቱን በግቢ ሰብበስው ሰፋ ያለ ታሪክ ጠቀስ ሐሳብ በጽሑፍ አድርገው እንደዚህ ሲሉ አስታወቁ ።

እኔ ዳግማዊ ምኒልክ . . . ይህንን ነገር ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ሕዝብና ሠራዊት አስታውቃለሁ ። ነገሩም ለሀገራችን ጥቅምና ትርፍ አገራችንን ነጻ የሚያወጣ ኃይላችንን የሚያበረታ ፤ ሀብታችንን የሚያበዛ ዕረፍትና ጤና የሚሰጠን ፤ ጠላቶቻችንን የሚያርቅ ነውና በውል ስሙት . . . የራሶችና የጭፍራ አለቆች ፍቅር ማጣት ሕዝብና ሠራዊት ክፍለ ሸዋ ትግሬ ጐንደር ጐጃም እየራሱ ሆነ . . .* ዐፄ ቴዎድሮስ ተነሱ አቀናለሁ ብለው ዠመሩት የሠራዊቱ ክፋት አበሳጫቸው ዠምረውት ሞቱ . . . ዐፄ ዮሐንስ ተነሱ መንፈሳዊነትን ዠመሩ ሊያቀኑም አሰቡ ። . . . ነገር ግን አሳባቸው አልተፈጸመም . . .

እኔም ዳግማዊ ምኒልክ በሸዋ 24 ዘመን (ዓመት) ነገሥሁ ከነገሥሁ እስካሁን አንድ ቀን አላረፍሁም ። ግራኝ ያጠፋውን ሁሉ አቀናሁ እንጂ . . . ሐረርን ሰበርሁ** ለሕዝቡና ለመንግሥቴ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማግኘት ወለኔም የሕንድ ውቅያኖስ ሆነ . . . ውጋዴን ቆላ አሩሲ ቦረና ሲዳሞ ከምባታ ከፋ ገሙ ጅማ ጐማ ሌቃ ወለጋ ኢሉባቦር በዚህ ሁሉ ሠራዊቴ ሞላ ፤ አገሬም ነጻ ወጣ ። ችግርና መከራ ሽብርና ሁከት ጠፋለት . . . አሁንም ይኸውና በእግዚአብሔር ኃይል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሆንሁ 17 ዘመኔ (ዓመቴ) ሆነ። ድምሩ 41 ነው። ይህ ሁሉ መሆን ኢትዮጵያ ባንድ ፈቃድ ብታድርና ባንድ ትእዛዝ (ሥልጣን) ብትሆን ነው ። አንድነት ከብረት ይጠናልና ተረቱም ከአንድ ብርቱ ሁለት ሰነፍ ይሻላል ነው የሚል ። አያቶቻችን (አክሱሞች) አንድነት ቢሆኑ ባሕርን ተሻግረው (ዓረብን) ገዙ ። ቢለያዩ ግን ግራኝ 15 ዓመት በእሳት አቃጠላቸው ። . . . ኢትዮጵያ አንድነት ሆና ከቶ ለጠላት ተሸንፋ አታውቅም ፤ በታሪክም የለ ።

ስለዚህ ምክር ነው የሰበሰብኳችሁ አንድነት እንዲጠና ብዬ ። ምናልባት ያ መለያየት ከኔ በኋላ ይመጣና አገር እንዳይጠፋ ጠላት ደስ እንዳይለው አገራችን እንዳይሔድ ሕዝባችን ወደ ግዞት (ወደ መገዛት) እንዳይገባ የሠራሁት እንዳይፈርስ ያቀናሁት መልሶ እንዳይጠፋ ብዬ ብፈራ ነው ። ዳዊት አስመ አልቦ ሰብእ ዘየሐዩ ወኢይሬእያ ለሞት ይላልና ።[1]

ስለዚህ በኋላ (ከኔ ቀጥሎ) የሚነግሠውን ወራሼን ላስታውቃችሁ ከልጄ ከወይዘሮ ሸዋረጋና ከራስ ሚካኤል የተወለደው ኢያሱ ነው የአልጋዬ ወራሽ ። እርሱን ዕወቁ ፤ እርሱን ተከተሉ ።[2]

ይኸንኑ ቃል በስብሰባው ለባለሥልጣኖች ካስገነዘቡና በጽሑፍ ለውጭ መንግሥታት ወኪሎችም ካስተላለፉ በኋላ ፤ ጠቅላላው ሕዝብ ይኸንኑ እንዲሰማው ስለ አስፈለገ ፤ በግንቦት 10 ቀን 1901 ዓ.ም. በጃንሆይ ሜዳ ታላቅ ስብሰባ ተደርጎ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ፤ ራሶች ፤ ደጃዝማቾች ፤ ሚኒስትሮችና የውጭ አገር መልክተኞች ባሉበት ከዚህ ቀጥሎ ያለው በይፋ ተነገረ ።

*ያገሬ የኢትዮጵያ ሰዎች ልጆቼ ወዳጆቼ እግዚአብሔር የገለጸልኝን ምክር ልምከራችሁ ። ዐፄ ቴዎድሮስ የሞቱ ጊዜ ከርሳቸው ጋር የነበረው ሰው ሁሉ ያንዱን አገር አንዱ እደርበዋለሁ አንዱን ገድዬ እኔ ጌታ እሆናለሁ እያለ ሁሉም ሳይረባ ተላልቆ * ቀረ። ከዚህም በኋላ ያፄ ዮሐንስ ሰው የሆነውን የምታውቁት ነው ። ባገር በሽታ ሳይገባበት ሌላ ጦርነት ሳይነሣበት በምቀኝነት እርስ በርሱ እንደ ተላለቀ አይታችሁታል ።***

*አሁንም ልጆቼ ወዳጆቼ ፤ አንዱ ባንዱ ምቀኝነት ይቅር ያንዱን አገር አንዱ እደርበዋለሁ እንዳትባባሉ ። እኔ እስካሁን በፍቅር እንዳኖርኳችሁ እናንተም ተስማምታችሁ በፍቅር እንድትኖሩ እለምናችኋለሁ ። እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ በምቀኝነት እርስ በርሳችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር አገራችንን ለሌላ ባዕድ አትሰጡትም ። ከፉ ነገር አገራችንን አያገኘውም ። ነፋስ (ጠላት) እንዳይገባባችሁ ። አገራችሁን በየአላችሁበት በርትታችሁ ጠብቁ፤ወንድሜ ወንድሜ ተባባሉ።*

*ይህን ምክር መጻፌ እኔም በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህን ያህል ዘመን ገዛሁ ። ነገር ግን ሰው ነኝና እንግዲህ ምን ያህል ዘመን እኖራለሁ ስል ነው። አሁንም እኔ እንደ ተመኘሁት የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ልጄን ኢያሱን ቢያቆይላችሁ ከልጄ ጋር ሆናችሁ አገራችሁን ጠብቁ፤ አደራ ብያችኋለሁ ። አደራ የሚባል ሰው የታመነ ነውና እኔም ሁላችሁንም አምናችኋለሁ። ከዚህም ከጻፍሁት ቃል የወጣ በሰማይም በምድርም የተረገመ ይሁን ። እኔም ሳለሁ ከፈቃዱ የወጣ ልጅ ረግሜአለሁ ።[1]*

በሕይወታቸው እያሉ አልጋ ወራሻቸውን በይፋ አስቀድመው ማስታወቃቸው ፤ በኢትዮጵያ ያነጋገሥ ልማድ ንጉሥ በሕይወቱ እያለ አልጋ ወራሹን አያስታውቅም ፤ ያስታወቀ እንደሆነ ሌሎች ልጆቹ

---

* ከዘመነ መሳፍንት ዠምሮ እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ የደረሰውን ሲያወሱን ነው ።

** ሐረርን መልሼ በግዕከላዊው መንግሥት አስ ተዳደር ሥር አደረግሁ ማለታቸው ነው ።

1 የሰው ልጅ ሞትን ሳያይ የሚኖር የለም ፤ የዳዊት መዝሙር 89—49

2 የኢትዮጵያ ትእምርተ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማና ዘውዱን የጃንሆይንም ዐዋጅ የሚናገር መጽሐፍ ፤ ከኃይለማርያም ስራብዮን ፤



* ካፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ዋግሹም ጐበዜ (ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ) ከጐጃሙ ባላባት ከደጃዝማች ደስታ ተድላ ከቤጌምድር ባላባት ከራስ ወልደ ማርያም ጋር ከየጁው ከዐሊ ፋሪስ እንደዚሁም ከደጃዝማች ካሣ (ዐፄ ዮሐንስ) ጋር ያደረጉትን ጦርነት በማስታወስ ፤

** ዐፄ ዮሐንስ መተማ ከሞቱ በኋላ ወራሼ ራስ መንገሻ ነው ብለው ፤ ቢናዘዙም የቀሩት ዘመዶቻቸው እነደጃች ቦጋለ እነደጃች ደብብ እነደጃች ሥዩም አባ ጐበዝ ያደረጉትን ጦርነት ሲያወሱ ነው ።

1 ታሪክ ዘመን ዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 343—344

እኛ ለምን ቀረብን በማለት ተከታይ ይዘው ጦርነት ይቀሰቅሳሉ ። በዚህ ምክንያት የነገሥታት ልጅ ሁሉ በአምባ ግሼንና በወህኒ በግዞት እየተቀመጠ ነጋሚው ሲሞት ብቻ አለቆች ከዚያ አምጥተው የወያነግሡታል ።[1] ዐፄ ዮሐንስ እንደ ቆሰሉ ወራሽ ለማድረግ የወንድማቸውን ልጅ ራስ ኃይለ ማርያምን ጥሩልኝ ቢሉ ሞተዋል አኋቸው ። "እንግዲያው ወራሼ ልጄ ራስ መንገሻ ነው" ብለው ተናዘው ወዲያው ስለሞቱ ፣ የትልቁ ራስ አርአያ ልጆች በቅርታ ከጦርነቱ ተመልሰው የርስ በርስ ውጊያ የተዠመረው ስለዚህ ነው ።

አሁን ዐፄ ምኒልክ ፣ በግልጽ ወራሻቸውን ማስታወቃቸው የዚህን ሁሉ ታሪክ በመገምገም መኳንንቱም ነገሩን ዐውቀው ከኢያሱ ጋር ተዋውቀው እንዲለማመዱና የቀረውም ሰው ሁሉ ፣ "ማንን ወራሽ ያደርጉ ይሆን ?" እያለ የአሳብ ጭንቀት እንዳይኖርበት ሲሉ ነው ። ከራስ ጉግሣ ወሌ ባለቤት ከወይዘሮ ዘውዲቱ በቀር ከማህለ ሥላሴ የሚወለዱ እነራስ ወልደ ጊዮርጊስና እነደጃች ታዩ በያለበት ስላሉ ፣ የመኳንንቱ አሳብ ወደነዚያ እንዳይበታተን ለማድረግ ነው ።

የልጅ ኢያሱን አልጋ ወራሽነት ባስታወቁበት በ1901 ዓ.ም. አልጋ ወራሹ ዕድሜያቸው 12 ዓመት ከመንፈቅ ነው ። በዚህ ዕድሜ ኢትዮጵያን ያህል አገር ብዙ ነገድ ፣ ልዩ ልዩ ሃይማኖትና ልማድ ያለበትን አገር ለማስተዳደር እንደ ማይቻል የታወቀ ነው ። ስለዚህ ለወጣቱ አልጋ ወራሽ እንደራሴ ሆኖ አገሪቱን በጊዜያዊነት የሚያስተዳድር ሲመከር ፣ ሲዘከር ምርጫው ራስ ተሰማ ሳይ ወደቀ ። ከምርጫው ምክንያቶች አንዱ የራስ ተሰማ አባት ደጃች ናደው (ትልቁ ናደው) ላፄ ምኒልክ በወጣትነታቸው ጊዜ ሞግዚት ስለነበሩ ፣ አሁንም ልጅየው ራስ ተሰማ ለልጅ ኢያሱ ሞግዚት ሊሆኑ ይገባል ተብሎ ነው ይባላል ።

ስለዚህ ይኸንኑ የራስ ተሰማ ናደውን እንደራሴነት ሕጋዊ ለማድረግ ከዚህ ቀጥሎ ያለው በዐዋጅ መልክ በጽሑፍ ተነገረ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ። ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ያገሬ የኢትዮጵያ ሰዎች ልጆቼ ወንድሞቼ ወዳጆቼ ሆይ ። እስካሁን ድረስ ሳታስቀይሙኝ በእግዚአብሔር ቸርነት አገሬን ገዛሁ ።

እኔን በውነት በመውደዳችሁና እናንተም አንድ ልብ በመሆናችሁ አገራችንን ኢትዮጵያን እስካሁን ጠላት አላጠቃትም ።

---

1 የግራኝ አህመድ ሠረራ ፣ ምዕ 65 ፣ ገጽ 400—404



አሁንም ከዚህ ቀደም እንዳስታወቅኋችሁ ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ያልጋዬ ወራሽ ልጄ የወይዘሮ ሸዋረጋ ልጅ ከራስ ሚካኤል የተወለደው ኢያሱ ነውና ፣ ራስ ቢትወደድ ተሰማን ሞግዚት አድርጌ ሰጥቻችኋለሁ ። አልጋዬን የሚጠብቅ እሱ ነው ። ሌላ ወንድ ልጅ የለኝም ። ነገር ግን ይህንን ማድረጌ እኔ ከቤት ስውል ጊዜ እንዳትደነግጡ ብዬ ነው እንጂ ፣ እኔ ሳለሁ ልጄን ይዘን ወዲያ ወዲህ ብለን ክፉ ሥራ እንሠራለን የሚል ሰው እረግሜአለሁ ። የይሁዳ ርግመት የአርዮስ ግዝት ይድረስበት ። የኔን ቃል ያፈረሰ ሰው መሬት ይክዳው ፣ ጥቁር ውሻ ይውለድ ፣ ያሳደግኋችሁም የሾምኋችሁም መኳንንቶች ወታደሩም ትልቁም ትንሹም ከኔ ፈቃድ የወጣ ሰው ረግሜአለሁ ። ከኔም በኋላ ልጄን ያልተከተለ ሰው ረግሜአለሁ ። እሱም ከናንተ ከባቶቹ ከወንድሞቹ ፈቃድ እንዳይወጣ ያላግባብ ክፉ ነገር እንዳያደርግ ልጄንም ኢያሱን የሰጠሁትንም ሞግዚት ራስ ቢትወደድ ተሰማን ረግሜአለሁ ።[1]

ጥቅምት 20 ቀን 1902 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

---

1 ዝክረ ነገር ፣ 2ኛ እትም 1962 ዓ. ም. ገጽ 509 ።



ልጅ ኢያሱ በአልጋ ወራሽነታቸው ዘመን

ከሞሪስ ደኮፔ መጽሐፍ



ራስ ተሰማ ናደው
ከሞራስ ጎቦጌ

# ምዕራፍ ሰባ ሦስት

## የመለያየት ስሜት—የዋግሹም አባተና የደጃዝማች አብርሃ ጦርነት

"ወንድሜ ወንድሜ ተባባሉ ነፋስ በመካከላችሁ እንዳይገባ" ብለው ዐፄ ምኒልክ መሳፍንቱንና መኳንንቱን የተማጠኑት ፤ ከእርሳቸው ሕመምና ሞት በኋላ በኢትዮጵያ እንደ መጥፎ ዕድል ሆኖ የተለመደው የርስ በርስ ጦርነት እንደሚነሣ በመሥጋት ነው ። በእርግጥም ከእርሳቸው በሕመም መዳከምና ሞት ዠምሮ የቀጠለው የርስ በርስ የሥልጣን ሽኩቻ ሲታይ ግምታቸው ትክክል ነበር ማለት ይቻላል ።

ዐፄ ምኒልክ ፤ "አልጋ ወራሼ ኢያሱ ነው ። ለርሱም እንደራሴ ራስ ቢቶደድ ተሰማን አድርጌያለሁ" ብለው ሲያውጁ ፣ በርሳቸው የትዕግሥትና የመልካም አመራር መንግሥት ዙሪያ የተሰበሰበው ሁሉ ፤ "ወደፊት እኝህ ሰው ታመው እቤት ሲውሉ ጭራሹንም ሲሞቱ ምን ይደርስብን ይሆን? ከእርሳቸው በኋላ እንደ ርሳቸው የሚያስተዳድረን ማነው" የሚል የመንፈስ ሁከት በሁሉም ላይ እንደሚደርስ ይታወቃል ። የራስ ተሰማ እንደራሴነትና የልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት በራስ ሚካኤል ዘንድ አለኝታንና መተማመንን ሲያሳድር ፤ በሌሎች ዘንድ በተለይ በእቴጌ ጣይቱና በወገኖቻቸው በነራስ ወሌ ዘንድ ፤ በሸዋ መኳንንቶች ዘንድና በሰሜን በኩል በትግሬ መኳንንት ዘንድ የኢያሱ አልጋ ወራሽነት ልባዊ አቀባበል ማግኘቱ አጠያያቂ ጉዳይ ሆኖአል ።

በእርግጥም ራስ ቢቶደድ ተሰማ ፤ "እንደራሴነቱ በዐዋጅ ከተሰጠኝ ወጣቱን አልጋ ወራሽ ይዤ እሱን እየመከርሁና እያሠለጠንሁ ፤ የመንግሥቱን ሥራ እመራለሁ" ብለው ወገኖቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ይዘው ሲነሡ ፤ እቴጌ ጣይቱ ደግሞ ወገኖቻቸውን ይዘው፥ "ባለቤቴ ምንም ሕመም ቢዠምራቸውና አልጋ ወራሻቸውን ቢናገሩም ፤ እንደራሴም ቢሾም የንጉሠ ነገሥቱ ትንፋሽ እስከ አለ ድረስ ሥልጣናቸው አይሻርም ። በርሳቸውም ስም እኔ አስተዳድራለሁ፤ አልጋ ወራሹም ጊዜውን ይጠብቅ" የሚል አቋም ነበራቸው ። ሁለቱም ወገ

ኖች የየራሳቸው ደጋፊዎች አሏቸው ። የእቴጌ ወገኖች ዋነኞቹ ታናሽ ወንድማቸው ራስ ወሌና ልጃቸው ደጃዝማች ጉግሣ ፣ ሌሎችም የሩቅና የቅርብ ዘመዶች እነደጃዝማች አያሌው ብሩ ናቸው ። ሲያያዝ በመጣው አክብሮት የሸዋዎቹ ባለሥልጣኖች ንጉሠ ነገሥቱም ሕመሙ በ1901 እና በ1902 ዓ. ም. ላይ ስላልተሻላቸው የእቴጌይቱን ሥልጣን ለጊዜው ለመቃወም የደፈረ የለም ።

ከራስ ተሰማ ወገን አብዛኛው የሸዋ መኳንንት ፣ እቴጌን ማከበራቸውና መታዘዛቸው ባይቀርም ፣ በእንደራሴነት አገሪቱን ለመምራት ኃላፊነት ለራስ ተሰማ እንደተሰጠ በማመን ወደራስ ተሰማ ያዘነበሉ ይመስላል ። በትግሬም ተወላጆች እነራስ ስብሐት ፣ እነደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባሪያ ጋብር ፣ እነደጃዝማች አብርሃ አርአያ ይኸንኑ መስመር የተከተሉ ይመስላል ። ሌላው የዚህ ዘመን ቀንደኛው ባለሥልጣን የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፣ ደጃዝማች ባልቻን ጨምረው ከሁለቱም ወገን ነጻ ሆነው የዘብ አብራጅነትንና የገላጋይነትን መስመር በመያዝ እቴጌን እይዞዎ ፣ ከርስዎ ፈቃድ አንወጣም ተሰማን መታገሥ ይሻላል እያሉ የሚመክሩ ይመስላል ። በተለይ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የዚህ ዘመን ባለሥልጣንነታቸው በሁሉም ዘንድ ተፈሪነትና ተሰሚነት ያላቸው መሆኑ የታወቀ ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ በማናቸውም ረገድ ራስ ተሰማም እቴጌይቱን መግፋቱ እያስቀቃቸው ፣ የቀሩትም በመፍራትና በማክበርም በንጉሠ ነገሥቱ አጠገብ ሚስትም ፣ አስታማሚም ሆነው ከሚገኙት ከእቴጌይቱ ፈቃድ የሚወጣ ለጊዜው አልተገኘም ። እቴጌይቱም በንጉሠ ነገሥቱ ስም እያደረጉ የራሳቸው ወገን የሆኑትንና ሌሎችንም ለመሳብ ሹምሽር ማድረግን ይቀጥሉ ዠመር ። በዚሁ መሠረት ቀደም ብሎ ራስ መኰንን ስለሞቱ ልጃቸው ደጃዝማች ይልማ የሐረርን ግዛት ከያዙ በኋላ ፣ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆዩ ስለአረፉ ፣ ለደጃዝማች ባልቻ ተሰጥቶ ነበር ። በመጨረሻ በእቴጌዪቱ ፈቃድ የሐረር ግዛት በ1902 ዓ.ም ለደጃዝማች ተፈሪ ተሰጠ ። እንደዚሁም ቀደም ብሎ ራስ ስብሐትም በሐረር ከራስ መኰንን ዘንድ በግዞት ቆይተው ከተመለሱ ወዲህ አጋሜን አስመርቀው ወደ አገራቸው ተመልሰው የመንግሥቱ ታዛዥና ፈቃድ ፈጻሚ ሆነዋል ።

ቀጥሎም በትግሬ ራስ ወሌ ተሾመው እንደቆዩ ፣ አሁንም በእቴጌዪቱ ፈቃድ ቤጌምድር ለራስ ወሌ ተሰጠና ደጃዝማች አባተ ግንቦት 1 ቀን 1901 ዓ. ም. ቀኛዥም ተብለው ላስታን በማዛት ፣ ትግሬን



በቆራጭነት* ተሾሙ ። በእርሳቸው ውስጥ ደጃዝማች አብርሃ አርአያ እንደርታን ተሾሙ ።

አብርሃ የትልቁ የራስ አርአያ ልጅ ፣ የደጃዝማች ደብብና የደጃዝማች ተድላ አባ ጉበን እንዲሁም የወይዘሮ አምለሱ** ወንድም ናቸው ። ታላቅ ወንድማቸው ደብብ ካፄ ዮሐንስ ከድተው ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር ባለሟል በነበሩበት ሰዓት ለኢጣሊያኖች አመልክተው አብርሃ ወደ ኢጣልያ አገር ሔደው በቶሪኖ ከተማ የኢጣልያ ቋንቋ በጽሕፈትም ጭምር ሲማሩ ቆይተው እንደተመለሱና ። የዓድዋ ጦርነት እንዳለቀ በ1888—89 ዓ. ም. ወጣቱ አብርሃ አስተርጓሚ ሆነው ማገልገላቸው ይታወቃል ።

ከዚያ በኋላ ፣ አዲስ አበባ መጥተው ካፄ ምኒልክም ከተላመዱ ወዲህ ፣ የደጃዝማችነት ማዕረግ አግኝተው በራስ መንገሻ ሥር በትግሬ በአንዱ ክፍል በእንደርታ ቆይተዋል ። ባሁኑ ጊዜ አዲስ አበባ ሆነው ደጅ ሲጠኑ በዋግሹም አባተ ውስጥ የእንደርታ ግዛት ተሰጣቸው ። በዋግሹም አባተ ውስጥ መሆናቸው ቅርታ እንደ ፈጠረባቸው በዚህ ላይ ዋግሹም አባተ በዕድሜያቸው በሥልጣናቸውም ብልጫ ሰበብ "አንተ" እያሉ ሲያነጋግሩዋቸው ፣ "ለምን አንቱ አላሉኝም" በማለት በዚህም ቆጭቷቸው ነበር ይባላል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ቁጭታቸውን በልባቸው እንደያዙ አባተም አብርሃም በ1901 ዓ. ም. ግንቦት 1 ቀን ቢሾሙም ክረምቱ ስለ ተቃረበ ፣ የክረምቱን ወራት አዲስ አበባ አሳልፈው አብረው ወደ ግዛት አገራቸው ጉዞ ዠመሩ ። በመንገድ ላይ እያሉ አብርሃ አስቀድመው ሔደው ላዲሱ ዋግሹም መስተንግዶ እንደሚያዘጋጁ አስመስለው በመሰናበት መቀሌ ከደረሱ በኋላ ፣ መሸፈታቸውንና ፣ ለመዋጋት ጦር ማዘጋጀታቸውን አባተ ሲሰሙ ወደ አዲስ አበባ ስልክ ደውለው ለንጉሠ ነገሥቱም ፣ ለእቴጌይቱም የአብርሃን መሸፈት አስታወቁ ። ለትግሬም ሕዝብ "የአብርሃ በመንግሥት ላይ መሸፈት ከአሰል የሚገባው የጨው ግብር ገቢው የመንግሥት በመሆኑ ለኔ ለምን ቀረበኝ በማለት ነው ። አሁን በምኒልክ መንግሥት ላይ መሸፈቱ ንብረትህን ከብትህን ሚስትና ልጅህን ለማስጠፋት

* ይኸም ማለት በቀጥታ ትግሬን በበላይነት እንዲያስተዳድሩ ማለት ነው ።

** አምለሱ የራስ አሉላ ባለቤት ናቸው ።

ነው እንጂ የሚረባው ነገር የለም ። ለመንግሥት ታማኝ የሆንክ ወደኔ ና'' የሚል ዓዋጅ አናገሩ ።

ስለዚህም መልስ ደጃዝማች አብርሃ ፣ ''እኔ በምኒልክ መንግሥት ላይ አልሸፈትሁም ፤ እስካሁንም ድረስ 12 ዓመት (1888 1900 ዓ. ም.) ሙሉ በቅንነት እያገለገልሁ ከግዛቴም ያገባሁት ግብር 160,000 የማሪያ ትሬዛ ብር ይሆናል ። ባገልግሎቴም ሌላ ግዛት ይጨመርልኛል ስል የራሴ የሆነው ቀረ ። በዚህም ላይ እኔ አንተ መባልን አልለመድሁም'' የሚል መልስ ሰጥተው የጦር ዝግጅታቸውን ይቀጥሉ ዠመር ።

ካርሎ አናራቶሬ የሚባል የኢጣልያ ተወላጅ እንደ ቆንሲልም እንደ ሐኪምም ሆኖ በዚህ ወቅት በመቀሌም በዓድዋም በመቀመጥ ከነደጃዝማች ሥዩም መንገሻና ከነራስ ስብሐት ፣ ወደ ደሴም እየመጣ ከራስ ሚካኤል ጋር ተላምዶ ነበር ። በዚህ የመቃቃር ጊዜም እዚያው ነበርና ስለ ተቀሰቀሰው ጦርነት አዠማመርና ፍጻሜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በመጽሐፉ አስፍሯል ።

. . . ከውጊያው በፊት የሁለቱ ወገን ጦር ሠራዊት ከተቀራረበ በኋላ አባተ ለአብርሃም ፣ በዚህ በትንሽ ነገር በሥላሴ ይገርሃለሁ የክርስቲያን ደም አይፍሰስ ፣ የሚገባህን እንድታገኝ እኔ ስለአንተ ለንጉሡ እነግርሃለሁ' ብለው ቢልኩ አብርሃ ፣ የነበረውን ሙሉውን ግዛቴን ይመልሱልኝ ፤ በግዛቴም ራሴ ለማስተዳደር ነጻነት ይስጠኝ ፤ ቢፈልጉ አክሱምን ያስቀሩ ፤ ከዚህ በኋላ ምሕረት እንዲያደርጉልኝ ይሁን' የሚል መልስ ሰጡ ። አባተ ሁኔታውን ወደ አዲስ አበባ ስልክ ደውለው ከእቴጌም ከንጉሡ ነገሥቱም ተነጋግረው ነበረ ። ከእቴጌዪቱም ፣ 'የጠየቅኸው ቀላል ነገር ነው የሚቸግር ነገር የለም' የሚል ቃል ለአብርሃ ቢመጣም ፣ እርስ በርስ ባለመተማመን ሁለቱ ወገኖች ለውጊያ ዝግጅታቸውን ቀጠሉ ። ከደጃች አብርሃ ወገን ሦስት የበታች ሹማምንት 200 ጭፍራ እንደያዙ ከድተው መጥተው ለዋግሹም አባተ ገቡላቸው ። በአብርሃ ጎን ወንድማቸው (ዘመዳቸው) ደጃች ረዳ ከሁለት መቶ ወታደር ጋር ሲገኙ ፣ ዋግሹም አባተን ለመርዳት የትግሬ መሆኔው ገዥ ደጃዝማች አበራና የራስ ወሌ የጦር መኰንን ፊታውራሪ አበዬ ከየጁ የዞብልን ጦር ይዘው ገቡ ። ራስ ስብሐትም ከአጋሜ ወደ አባተ መደረባቸውን. . .

የኢጣልያኑ ጸሐፊ ካወሳ በኋላ ስለ ውጊያው እንደዚህ ሲል ይቀጥላል ።

እ.ኤ.አ. በጥቅምት 8 ቀን 1909 (መስከረም 29 ቀን 1902 ዓ.ም.) አብርሃ ከነሰዋቸው ከአሸንጌ ሐይቅ በስተደቡብ ባለው ጉብታ ላይ እንደ ሰፈሩ አባተ በኮረምና በወፍላ ምሥራቅ መካከል እየመሸጉና



እየተደራጁ ሲጠባበቁ ፣ አብርሃ ሌሊቱን ተጠግተው ሳይታሰብ በአባተ ጦር ላይ ሊነጋጋ ሲል ጦርነት ከፈቱ ። ከዚያ አባተ በጥድፊያ ወደ ጦሩ ግንባር ሔደው በ200 ሜትር ርቀት በመትረየስና በጠመንጃ ሲዋጉ ቆይተው ፣ በመጨረሻም የጨበጣ ጦርነት አድርገው ከተዋጉ በኋላ ፣ ደጃች አብርሃ ከመጀመሪያው ላይ ያሸነፉ መስሏቸው ምርኮኛ መቀበል ዠምረው

እንደነበረ ያመለክታል ።*

ዳሩ ግን ፣ የራስ አባተ ወገኖች መልሰው በኃይል በማጥቃታቸው ከሦስት ሰዓት ውጊያ በኋላ የደጃች አብርሃ ጦር ተሸንፎ ወደ ራያና አዘቦ ሽሽት ሲጀምር የቀረውም ተማረከ ። አብርሃና መኳንንቶቻቸውም አብረው ተማረኩ ።

ጸሐፊው በሁለቱ መካከል የተደረገው የጠመንጃ ፣ የመትረየስና የጨበጣ ጦርነት ያስከተለው የሬሳና የቁስለኛ ብዛት ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ የውስጥ ጦርነት መሰል የሌለው መሆኑን አውስቶአል ። በጸሐፊው ግምት ከጠቅላላው ተዋጊ ወታደር 31% እጦርነቱ ሜዳ ላይ መቅረቱን ያመለክታል ። ከዚሁ አያይዞ ጸሐፊው በራስ ሚካኤልና በራስ አባተ የችኮላ ልመና በቶሎ ወደ ጦርነቱ ሥፍራ ለሕክምና መሔዱንና ከመንግሥት ወገን የቆሰሉትን ወታደርና ሹማምንት ለማከም ከቁስለኛው ብዛትና ከመድኃኒቱ ማነስ የተነሣ መቸገሩን በዝርዝር ያወሳል ።[1]

የሆነ ሆኖ ፣ ዋግሹም አባተ ደጃዝማች አብርሃን ይዘው ወደ አዲስ አበባ እንደ መጡ ትንሽ ቆይተው የራስነት ማዕረግ አገኙ ። ደጃዝማች አብርሃም ሰላሌ በሸንኩርት ዋሻ ታስረው ተቀመጡ ።

አብርሃም በዋግሹም አባተ የበላይነት የትግሬ ግዛት ሲሰጣቸው ቅርታቸውን እንደያዙ እሺ ብለው በመሔድና በኋላ በመሸፈትፈንታ ከጦርነቱ ትንሽ ቀደም ብለው ለአባተ የገለጡትን ቅርታ እዚሁ አዲስ አበባ ለእቴጌ ጣይቱ ወይም ለእንደራሴው ለራስ ተሰማ ገልጠው የማይለወጥም ሁኔታ ከገጠመ ፣ እዚሁ እቤተ መንግሥቱ ደጅ እየጠኑ ቢቆዩ ኖሮ ሰው ሳያልቅ ለችግሩ አንድ መፍትሔ ሊገኝ በቻለ ነበር ። መቼም በዕድሜም በሥልጣንም አባተ እንደሚበልጡ ቢታወቅም ፣ አባተ አንተ ብለው ሊያነጋግሩአቸው ከደፈሩ እሳቸውም አንተ ብለው ማነጋገር ነበር እንጂ ይኸ ሰበብ ሆኖ ለብዙ ሰው ሕይወት መጥፊያ ምክንያት ሊሆን ባልተገባ ነበር ።

---

* በዚህ ጊዜ ከተማረኩት ውስጥ በኋላ ራስ የተባሉት አድፍርሰው ነበሩ ይባላል ።
1. In Abyssinia- Carlo Annaratore, PP.99-114.

በዚሁ ዘመን ደግሞ ፡ ይኸን በመሳሰለ ወይም በሌላ ምክንያት
አንዱ ቀንደኛ ሲሸፍት በርሱና በመንግሥቱ ወታደር መካከል ጦር
ነት ተደርጎ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወታደሮች ሕይወታቸው ሲጠ
ፋና አካላቸው ሲጐድል ፡ ጥፋተኛው አለቃ ይኸን በማድረጉ የሚገባ
ውን የሞት ቅጣት ወይም ረዘም ያለ የእስራት ዘመን አያገኘውም ።
ይኸም ሁኔታ ሌሎቹን በሸፍትነት እንደሚጋብዝ ግልጽ ነው ።

ዳሩ ግን ፡ በቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች ዘንድ ከምኒልክ አቅ
ዋም የተወረሰው ያስተዳደር ዘዴ በኃይል ሳይሆን በትዕግሥት ችግ
ርን ማሳለፍ ስለሆነ ፡ በቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች ዘንድ ፡ "እገሌ
አጠፋህ ብለን በሞት ብንቀጣው ወገኖቹ እነገሌ ይሸፍታሉ ። እነር
ሱን ለመቅጣት ጦር ሲላክ ሌላው ክፍለ ሀገር ይሸፍታል ። ይኸም
ሲሆን ፡ የአገሪቱ ጠቅላላ ጸጥታ ይናጋና የውጭ ጠላት ባገራችን
ይገባል " የሚለው ሥጋት በምኒልክና በመኳንንቱ ዘንድ እያንዣ
በበ ፡ በዳዩ ሁሉ የሚገባውን የሞት ወይም ለጥፋቱ ተመሳሳይ የሆነ
የረዥም ዘመን እስራት ሳያገኝ ይቀራል ። ምስኪን ባላገር በዘረፋ
ተጐድቶና የዋሁ ወታደር በውጊያ ላይ አልቆ ሳለ ፡ ሰውዬው ከጥ
ቂት የግዞት ዘመን በኋላ እንደ ሁኔታው በአጋጣሚ ሌላ ባለሥልጣን
ሲነሣ እሱም አብሮ ሊነሣና ሊሾም ፡የቀድሞ አጥቂውንም መልሶ
ሊያጠቃ ይችላል ።

ደጃዝማች አብርሃ ፡ ከላይ ዘራቸውን ከዓድዋው ከራስ ስሑል ሚካ
ኤል ፡ ከእንደርታው ከራስ ወልደ ሥላሴ ፡ ከተስፋ ኢየሱስና ከሹም
አጋሜ ወልዱ የሚቆጥሩ ናቸው ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከነበሩት
ካሤ ዮሐንስ ጋር የታናሽና የታላቅ ልጆች ናቸው ። ከዚህ የተነሣ በአ
ጋሜ ፡ በእንደርታና በተምቤን ባላባትነታቸው ግልጽ ነው ። ስለዚህ
እንደዚህ ያሉትን ባላባቶች በጥፋታቸው መጠን አግባብ የሆነ
ቅጣት መስጠት በዚህ ዘመን ላሉት አስተዳዳሪዎች አሥጊ ነው ።
"ሺ አውል ከሚሞት ፡ ሺ ይሙት" የሚባለውን ያስተዳደር ፍል
ስፍና ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና ራስ ስሑል ሚካኤል ብቻ ሽረው ነፍስ
ቢገድሉ በልጆቻቸው ላይ የሞት ፍርድ ፈርደዋል የሚባለው ፡ ለዚያን
ዘመን ኢትዮጵያውያን ብዙ ነገድ የተደባለቀበትን ሰፋ አድርገው
ለያዙ አዲስ ያገር አስተዳደር ጐጂ ወጭዎች አያገለግልም ።

በዚህ ምክንያት ፡ አብርሃ ያን ሁሉ ሰው አስጨርሰው እጃ
ቸውን ለአባተ ከሰጡ ወዲህ ከፍ ያለ ቅጣት ሳያገኛቸው ለላሌ
በሸንኩርት ዋሻ በግዞት ጥቂት ጊዜ ቆዩ ። በኋላም ንጉሠ ነገሥቱ
ፀርፈው በራስ አባተና በልጅ ኢያሱ መካከል በ1906 ዓ. ም. ጠብ
ተነሥቶ አባተ በራስ ሚካኤል እጅ ወደ አፍቀራ ተልከው ሲታሰሩ



አብርሃ ከሁለት ዓመት ግዞት በኋላ ተፈትተው ያገር ግዛት ሚኒስትር
ሆኑ ። ያንጊዜ ነው " ከትከት ብላ ሳቀች መሬት ጥርስ አውጥታ ፤
አባተ ሲታሰር አብርሃ ሲፈታ " የተባለው ። ከዚያ ደግሞ በ1909
ዓ.ም. በሰገሌ ጦርነት ኢያሱና ሚካኤል ሲወድቁ ለአብርሃ አዲስ
የመውደቂያ ፡ ለራስ አባተ የትንሣኤ ሁኔታ ተጠፈረ ።

# ምዕራፍ ሰባ አራት

## የራስ ቢትወደድ ተሰማና የእቴጌ ጣይቱ የሥልጣን ፍልሚያ
## የእቴጌይቱ ከሥልጣን መወገድና የራስ ተሰማ ዕረፍት

ጣይቱ በነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም. ሲወለዱ በነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም. የተወለዱትን ምኒልክን እራት ዓመት ይበልጧቸዋል ማለት ነው ። ምኒልክ የሸዋና የወሎ ንጉሥ ሆነው በነበሩበት ሰዓት ከአምባጫራ በጐጃም በኩል ሲያልፉ ደብረ መዊዕ ላይ ተገናኝተው ፣ ጣይቱ ወደ ሸዋ ከመጡ ወዲህ አንኮበር መድኃኔ ዓለም ቆርበው በ1875 ዓ.ም. ከምኒልክ ጋር ከተጋቡ በኋላ ፣ ንጉሥ ምኒልክ በ1882 ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥት ሲሆኑ ፣ ወይዘሮ ሲባሉ የቆዩት ጣይቱም ሥርዓተ መንግሥት ተደርጎላቸው እቴጌ መባላቸው ባለፈው ተጽፏል ።

ካፄ ምኒልክ ከተጋቡ ገዞምሮ በፖለቲካው ፣ ባስተዳደሩም እየገቡ ችግሩንም ፣ ደስታውንም አብረው እየተካፈሉ እስከዚህ ደርሰዋል ። ጣይቱ የቤት ጾታ ቢሆኑም ፣ የጦርነትም ፣ የፖለቲካም ፣ ያስተዳደርም እስተያየታቸው ከወንድ ቢበልጥ እንጂ አያንስም ።

ባልና ሚስቱ ተከባብረው ፣ ሥልጣን ተካፍለው ፣ በጭፍሮቻቸው ዘንድ ተፈርተው ፣ ተከብረውና ተወደው ሁለቱም የተሻለ እዱኛ አሳልፈው በደስታ ኖሩ ። አሁን ንጉሠ ነገሥቱ በሕመም ተዳከመው ራስ ተሰማ እንደራሴ ከተባሉ በኋላ ፣ "የአገሪቱ አስተዳደር በኔ በእንደራሴው መመራት አለበት " በሚሉበት ሰዓት ፣ እቴጌይቱ ደግሞ "ባለቤቴ ምንም ሕመም ቢያድርባቸው ፣ አልጋ ወራሻቸውን ቢያስታውቁም ፣ እንደራሴ ቢሾሙም ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ትንፋሽ አለ ድረስ በርሳቸው ስም አስተዳዳሪነቱ ከኔ እጅ አይወጣም ፤ አልጋ ወራሹም ጊዜውን ይጠብቅ " የሚል ስሜት አደረባቸው ።

በዚህ ምክንያት ፣ ቀድሞ ቤተ ዘመዶቻቸውን ከሸዋም ከሌላም መኳንንት ጋር እያጋቡ ወገን ከማበርከታቸው በቀር አሁንም ንጉሠ ነገሥቱ በታመሙበት ሰዓት ደጃዝማች ተፈሪ ሐረርን የተሾሙትና የወንድማቸው የራስ ወሌ ልጅ ደጃዝማች ጉግሣ ራስ ተብለው ቤጌምድርን የተሾሙት ፣ ዐዋጁ በታማሚው ንጉሠ ነገሥት ስም ቢሆንም ፣ ትክክለኛው አሿሿም ግን በእቴጌ ጣይቱ ፈቃድ ነው ። የጐጃሙን

የደጃዝማች ሥዩምንም ወገንነት ለማግኘት ሲሉ ሥዩም ሲመ
ኙት የኖሩትን ዳሞትንና አገው ምድርን ከራስ መንገሻ አቲከም ላይ
ወስደው የራስነት ማዕረግ ጨምረው ሰጡዋቸው ። ስማቸውም ከዚህ
ጊዜ ዠምሮ ሥዩም መሆኑ ቀርቶ ራስ ኃይሉ እየተባሉ ይጠሩ ዠመር።
በዚህ ጊዜም እቴጌይቱን ለማስደሰት ራስ ኃይሉ የራስ ቢቶደድ መን
ገሻን ልጅ ወይዘሮ አስካለ ማርያምን ፈትተው የእቴጌ ጣይቱን
ዘመድ ወይዘሮ አሰለፈች ወንዴን አገቡ ።ራስ ቢቶደድ መንገሻ ባጼ
ምኒልክ ቤተ መንግሥት እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው በሁሉም
እየገቡ የሚሠሩና ምክራቸውም ተደማጭ ነበር ። በመጨረሻም በን
ጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ አገራቸውን አገው ምድርን ተሾመው ሔደው
ነበር ።

ራስ ቢቶደድ መንገሻ ፡ በዚህ ጊዜ እርጅና ተጭኖአቸው በቤታ
ቸው እንዳሉ ግዛታቸው ለራስ ኃይሉ የመሰጠቱን ወሬ ሲሰሙ ፤
"በውነት ጌታዬ ምኒልክ ነፍሱ እያለ እንደዚህ አይደረግም ሞቷል
እንጂ" ብለው እንዳለቀሱ[1] ተክለ ሥላሴ መዝግበውታል ።

የሆነ ሆኖ ፡ እቴጌ ጣይቱ ይኸን ሁሉ ሹም ሽር ሲያደርጉ ፡ በፓ
ለበት ወገኖቻቸውን ሲያጠናክሩ ፡ ለጊዜው ራስ ተሰማም እነፊታው
ራሪ ሀብተ ጊርጊስም ከቀድሞ ዠምሮ በመጣው አከብሮትና ፍ
ሐት የተነሣ እቴጌይቱ የሚያደርጉትን በቅርታም ቢሆን ከመቀ
በቀር ፊት ለፊት ለመቃወም የደፈረ አልነበረም ። በኋላ ግን ፡ ወ
አድሮ መቀያየማቸው አልቀረም ።በመካከሉ የእቴጌ ወንድም ራ
ወሌና የአልጋ ወራሹ አባት ራስ ሚካኤል ፡ አምባሰል ላይ ለሰ
ርነት በተሰለፉበት ሰዓት እቴጌይቱና ራስ ተሰማ የየራሳቸውን ጠብ
ወደ ጐን አድርገው ፡ እቴጌም ራስ ወሌን እንዲቆጡ ራስ ተሰማም
ራስ ሚካኤልን እንዲያስታግሡ ደብዳቤ ይጻጻፉ ዠመር ።

የራስ ወሌ ልጅ ራስ ጉግሣ ፡ ከአዲስ አበባ ወደ ቤጌምድር የተ
ላከ አንድ ሰው ስለ ገደሉ ፡ "ባለ ደሞቹ ክስ አቅርበዋልና መጥተሀ
ተነጋገር" የሚል ከነራስ ተሰማ ቢላክ ፡ ጉግሣም አከስታቸውን በመ
ተማመን "አልመጣም" ብለው እምቢ አሉ ። ይኸም ራሱ በእቴጌ
ይቱና በነራስ ተሰማ መካከል ትልቅ ውዝግብ ፈጠረ ። ተሰማ "ተከ
ሳሹ ጉግሣ ቀርቦ መልስ ይሰጥ" ሲሉ ፡ እቴጌይቱ "አይመጣም"
በማለት የሁለቱ ልብ መሻከር ዠመረ ።

1. የእጅ ጽሑፍ ፡ ገጽ 196—197



በዚህ መካከል ደግሞ ፡ "እቴጌይቱ ወገኖቻቸውን ይዘው መንግ
ሥት ከአዲስ አበባ ወደ ጐንደር አዛውረው ለመንገሥ ወጥነዋል ፤
በአዲስ አበባ ያሉትን የውጭ አገር መንግሥትታት ወኪሎች 'ደግ
ፉኝ' የሚል ደብዳቤ ጽፈዋል" የሚለው ወሬ እየገነነ ሲሔድ ፡ ራስ
ተሰማ በአሉበት በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቤት መጋቢት 11
ቀን 1902 ዓ.ም ስብሰባ ተደርጎ ብዙ ውይይትና የአሳብ መለዋወጥ
ከተደረገ በኋላ ፡ በመጨረሻ እቴጌ ጣይቱ ከአስተዳደር ውጭ ሆነው
በግቢ ተቀምጠው ጃንሆይን በማስታመም ይወሰኑ ተብሎ ተቆረጠ ።

ይኸንንም ውሳኔ ሔደው የሚነግሩ ራሳቸው ራስ ቢቶደድ ተሰማ
ሆነው ሌሎችም ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባሪያ ጋብር ፡ ፊታውራሪ
ወሰኔ ትርፌ (ደጃዝማች) ፡ ደጃዝማች ብርቄ ጫጫ ፡ ደጃዝማች መን
ገሻ ተደልድለው ወደ እቴጌ ተልከው ይኸንኑ ውሳኔ መጋቢት 12
ቀን በግልጽ ነገሩዋቸው ። በዚያን ጊዜ እቴጌይቱ በንዴት ፊታቸ
ውን ወደ ራስ ቢቶደድ ተሰማ አዙረው ፡ "ይህን ነገር ሁሉ ያበብ
ከውና ያደረግኸው አንተ ነህ ...ሁሉንም ነገር በእርግጥ ሰምቼዋ
ለሁ ... ግና አስቀድሜ እኔ ጃንሆይን አስታምማለሁ ፤ የመንግሥቱ
ሥራ ይቅርብኝ ብልህ .. የመንግሥቱን ሥራ እየሠሩ እርስዎ ካላ
ሳመኑን እኛ ምኑን እናውቀዋለን . .ብትለኝ ሠርቼ የምጠቅም ከሆነ
በሚቻለኝ እረዳለሁ አላልኩሆም . ..ላንተስ ሳላማክር ምን የሠራ
ሁት ሥራ አለ ?" ብለው ወረፏቸው ።አብረው የቆሙትንም መኳን
ንት ግግሹን በመልኩና በአለባበሱ ፡ የቀረውንም ባለፈው በጠባዩ
ያሳየውንና የሠራውን እየጠቀሱ የስድብ ናዳ አወረዱባቸው ።

የሆነ ሆኖ ፡ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የእቴጌ ሥልጣን ቆሞ የራስ
ተሰማ ሥልጣን ተረጋገጠ ። በዚያን ዘመን ያሉት ታላላቆቹ እነ
ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ፡ እነራስ አባተ ፡ እነ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮር
ጊስ ፡ ጳጳሱም ፡ እጨጌውም ከራስ ተሰማ ጋር ተባበሩ ። እቴጌይቱም
ከግኖቸውም ሥልጣን ተወግደው ከእንጀራ ልጃቸው ከወይዘሮ ዘው
ዲቱ ጋር ሆነው ትርታና ቁጭታቸውን በልባቸው እንደያዙ ንጉሠ
ነገሥቱን በማስታመም ተወሰኑ ።

ነገር ግን ፡ ራስ ቢቶደድ ተሰማ በዚህ ሁኔታ ጊዜያዊ ደስታ
አግኝተው እንደ ልባቸው በመሾም በመሻር ሥልጣናቸው የተ
ጋላ ቢሆንም ፡ ሙሉ ደስታ ለማግኘት አልቻሉም ።ልጅ ኢያሱ አልጋ
ወራሽ እንደ መሆናቸው መጠን ፡ በርሳቸው ሥልጣን ለመጠቀም የፈ
ለጉ ብዙዎቹ ዙሪያቸው ተሰበሰቡ ።በዚህም ላይ ራስ ተሰማ ኢያ
ሱን ፡ "ይኸን ልብስ ይኸኛው ባንተ ላይ እያምርም ፤ በፍርድ ሸንጎ
ረግተህ ተቀመጥ ፡ ሥነ ሥርዓትና ፍርድ ተማር" በማለት ከኢያሱም

ከወገኖቻቸውም ጋር በየዕለቱ ጠብና ክርክር ሆነ ። “ወደፊት የሚነግሠውም ያው ኢያሱ ነው ። ተሰማም በዕድሜ ገፍተዋል ። እሳቸውም ሲሞቱ እኛ እንደራሴ እንሆናለን ”በሚል ተስፋ ወደ ልጅ ኢያሱ እየተደረቡ ነገርና ተንኮል በመሥራት ራስ ተሰማን ጤና ነሷቸው ። በምኒልክና በጣይቱ የተገነባውም ጠንካራ መንግሥት በዚህ ጊዜ መዋዠቁ ስለተሰማ ተመልካችን ሁሉ ሁኔታው አሳዘነ ። ሁሉም “አዬ ጉድ ! የተወዳጁ ንጉሣችን የምኒልክ መንግሥት እንዲህ ይሁን” እያለ መጸጸት ዠመረ ።

ስለዚህ እቴጌ ጣይቱ ፣ በመጋቢት ወር 1902 ዓ.ም. ከሥልጣን እንደ ተወገዱ ራስ ተሰማም በሚቀጥለው ዓመት 1903 ዓ.ም. በመጋቢት ወር ሥጋቱም ፣ ብስጭቱም እንዳደረባቸው ታመው ባጭር ጊዜ ውስጥ በሚያዝያ 3 ቀን ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት ተኩል ዐርፈው ደብረ ሊባኖስ ወስደው ቀበሩዋቸው ።[1] በርሳቸውም ሞት ኢያሱና ወገኖቻቸውም ፣ “ከሞግዚት ነጻ ሆነን የልባችንን እንሠራለን ” በማለት ለብዙ ጊዜ የማይቆይ ደስታ አደረባቸው ። ለአማሟታቸውም ብዙ ትርጉም ተሰጠው ። ከዚህም መካከል አንዱ ፣ “በልጅ ኢያሱ ተገፍተው ባለቤታቸው ወይዘሮ በለጥሻቸው በመድኃኒት ገደሏቸው” የሚለው ሐሜት ይገኝበታል ።

1. መልካም ቤተሰቦች ቢቶደድ መኰንን እንዳልካቸው ምዕ 5—6 ሕይወቱና የኢትዮጵያ እርምጃ ተ.ኃ.ሥ. ገጽ 16—18



# ምዕራፍ ሰባ አምስት

## በየግዛታቸው ያሉት ባለሥልጣኖች — የወጣቱ የልጅ ኢያሱ ሥልጣን አያያዝ— የራስ አባተ ተቃውሞና እሰራት — ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ቀኛዝማች ደቻሳ

የልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት እንደ ታወጀ ፣ ባፄ ምኒልክ የመጨረሻ ዘመነ መንግሥት በየአውራጃው ያሉትን አስተዳዳሪዎች ስንመለከት ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ በትግራይ ከራስ መንገሻ እሰራትና ከራስ መኰንን ሹመት ወዲህ ፣ በኮረም ዋግሹም አባተና ደጃዝማች አብርሃ ከተዋጉ በኋላ ፣ የደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ዕድገት እየጨመረ ሔዷል ።

ገብረ ሥላሴ አባታቸው ደጃዝማች ባሪያ ጋብር ይባላሉ ።ገብረ ሥላሴ ምንም እንኳ ትውልዳቸው ከመረብ ወዲህ በትግራይ ቢሆንም ፣ ከዓድዋ ጦርነት ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ጣልያኖች ኤርትራ ብለው ወደ ያዙት ክፍል የኢጣልያ ቋንቋ ከነጽሕፈቱ ተምረው በወታደርነት ደረጃ እስከ ዩዝባሽነት ደርሰዋል ። ስለርሻቸውም በሰሜን ኢትዮጵያ ከመረብ ባሻገርና ከወዲህም ብዙ ዘመን ያሳለፈው አናራቶሬ እንደዚህ ይላል ።

> . . ገብረ ሥላሴ የኛ ዩዝባሽ ነበረ ። በ1896 ዓ ም በተደረገው የጦርነት ዘመን 100 ወታደር እንደያዘ በደብረ ኃይላ ጦርነት በታማኝነት አገልግሎናል ። ከራስ መንገሻ በኩል ከኢጣልያ እንዲሸፍት የቀረበለትን ሐሳብ አልተቀበለም ። . . . በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ከራስ አሉላ ተቀበለ ። በራስ ወሌ ዘንድ ሲጠላ በራስ መኰንን ዘንድ በጣም የተወደደ ነበር ። ከትልቅ ጦርነት በኋላ ደጃዝማች አብርሃን ማርኮ ለንጉሡ አቅርቧል ። መልከ መልካም የ38 ዓመት ሰው ነው ።* ከሁሉም ጋር ሰምምና በሁሉም ዘንድ ተወዳጅ ነው ።[1]

በውነትም በራስ መኰንን አማካይነት ፣ ካፄ ምኒልክ ጋር ተዋውቀው በብዙ ረገድ ታማኝነታቸውን ከገለጹ በኋላ ንጉሡ ነጋሪቱ ባለሟል አድርገው በዓድዋ ሾሙዋቸዋል ። በአክሱም ንቡረዕድ

* በየትኛው ዓመተ ምሕረት መሆኑን አይገልጽም ። 1890—95 ዓመተ ምሕረት መካከል ይሆናል ።

1 In Abyssinia, C. Annaratore, PP.71-73.

ተብለው የራስ ወርቅ እስከ ማሰር ደርሰዋል ። ራስ መንገሻ እጃቸውን ለራስ መኰንን ሰጥተው ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ጊዜ የደጃዝማችነት ማዕረግ አግኝተዋል ። የራስ መንገሻ ልጅ ደጃዝማች ሥዩምና የወንድማቸው የራስ አርአያ ልጅ ደጃዝማች ጉግሣ ሸፍተው በዚያው በትግራይ የቆዩትን በማስፈራራትም ፣ በማባበልም በየተራ ወደ አዲስ አበባ አምጥተው ላፄ ምኒልክ ያስገቡ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ስለሆኑ ባፄ ምኒልክ ዘንድ ተወደው ራስ ሊባሉ ሲሉ ፣ በእቴጌዪቱ ተቃውሞ ቀረ ይባላል ።

ካፄ ምኒልክም ጋር ያላቸው ግንኙነት እየጠበቀ ሲሔድ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ የሚወለዱትን የቅርብ ዘመዳቸውን ወይዘሮ አማረች ዋለሉን ዳሩላቸው ። አሁንም ንጉሠ ነገሥቱ በታመሙበት ሰዓት የእቴጌይቱ ሥልጣን ባለቤታቸውን በማስታመም እንዲወሰን ሲደረግ ፣ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ከራስ ተሰማ ጐን በመቆም ከእቴጌይቱ ጋር ጠብ ከማብቀል ደርሰው ነበር ። በዚህ ምክንያት በአሁኑ ሰዓት በትግሬ መሆኔ ደጃዝማች አበራ ተድላ ፣ በአጋሜ ራስ ስብሐት ፣ በዓድዋና በአካባቢው ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ አስተዳዳሪነት ሲሰጣቸው በተምቤን ደጃዝማች ሥዩም መንገሻ ፣ በሽሬ ደጃዝማች ጉግሣ አርአያ ያስተዳድራሉ ።

በሌላም በኩል ፣ ቤጌምድር ለራስ ጉግሣ ወሌ ፣ የጁ ለራስ ወሌ ፣ ጐጃም ከአገውና ከዳሞት ጋር ለራስ ኃይሉ ፣ ወልቃይትና ስሜን ለፊታውራሪ ኪዳነ ማርያም ፣ በደቡብ በኩል ሐረርጌ ለደጃዝማች ተፈሪ ተሰጥቷል ። ከጨቦና ከአመያ ዝምሮ የጉራጌ አገርን ይዞ እስከ ቦረና ድረስ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቢነግዱ ፣ በከፋና በአካባቢው ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ፣ በከምባታ ራስ አባተ ፣ በሲዳሞ ደጃዝማች ባልቻ ፣ በወሎ ራስ ሚካኤል ፣ በጃማ ራስ ልዑልሰገድ ፣ በሚዳና በደራ ራስ ወልዴ ፣ በኤፍራታ ፣ በግድም ፣ በቀወትና በጥሙጋ ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ፣ በጐላ ደጃዝማች ውቤ አጥናፍ ሰገድ በሰላሌ ፣ ደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ ፣ አጋማሹ ወለጋ ደጃዝማች ደምሰው ነሲቡ ፣ አጋማሹ ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔርና ሌሎችም ይኖራሉ ። በመካከሉ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ቀደም ብለው ከፋን ተሽረው ወደ ጐንደር ተዛውረው ፣ በጌምድርንና ስሜንን ጠቅልለው በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ ። ከእቴጌ ጋር ያድጋሉ ተብለው ወንድማቸው ራስ ወሌም በመጨረሻ በግዞት ወደ አንኮበር ሲላኩ ልጆቻቸው እነ ራስ ጉግሣ ደግሞ ታስረዋል ።

በ1903 ዓ.ም. የልጅ ኢያሱ ሞግዚት ራስ ተሰማ ናደው ሲሞቱ ፣ ለልጅ ኢያሱና ለወገኖቻቸው ትልቅ ልጓም እንደ ወለቀላቸው ተቆጠረ።



ባንድ ወገን ዋናዋ የሥልጣን ባላንጣ እቴጌይቱ ባለቤታቸውን በማስታመም ብቻ ስለ ተወሰኑ ፣ ለልጅ ኢያሱ ሰፊ የሥልጣን ሜዳ ተከፈተላቸው ። ታላላቆቹ መሳፍንትና መኳንንት ለጌታቸው ሕመም በማሰብ ፣ "ወደፊትስ ምን ይደርስ ይሆን በዚህ አገር" እያሉ በማሰላሰል ገርበብ ቢሉም ፣ ሹመትና ሽልማት ፈልጎ የወደፊት ትዳሩን ለማቃናት የተመኘውና በተለይ እንደ ወጣት ያለው በኢያሱ ዙሪያ ተሰበሰበ ።

ኢያሱ በዚህ ወቅት (በ1903 — 04 ዓ. ም.) ዕድሜአቸው 15 ዓመት ስለደረሰ ፣ ጊዜያቸውን በፈረስ ግልቢያና በጉግስ ጨዋታ ማሳለፋቸው ሌላም ሌላም የልጅነት ሥራ መሥራታቸው ፣ ያፄ ምኒልክንም ሽማግሌ መኳንንት እየነቀፉ ማንጓጠጣቸው ፣ የብዙ መኳንንት ሴቶችን ማማገጣቸው ወይም ለማማገጥ መሞከራቸው ውስጥ ውስጡን በርከቶ ይወራ ዠመር ።

በዚህ ምክንያት ፣ ራስ አባተ ቧያለው እነደጃዝማች ይገዙን ፣ እነንቡረዕድ ገብረ ሥላሴንና ሌሎቹንም ጨምረው በመሰብሰብ ፣ "ራስ ተሰማ ከሞቱ ወዲህ ልጅ ኢያሱ ልቅ ወጣ ። ብዙም የማይገባ ሥራ መሥራት ዠመረ ። ስለዚህ ይዘን በምክር በሥነ ሥርዓት በማስተማር እናሳድገው ። የመንግሥቱ ሥራ ግን ፣ በአንድ ሥርዓት ዐዋቂ ሞግዚት ይመራ" የሚል ሐሳብ አቀረቡ ። ልጅ ኢያሱም ነገሩን ሰምተው በመደንገጥ ወደ ስብሰባው ሔደው ፣ "ከፈቃዳችሁ አልወጣም" ብለው የመለማመጥ መልክ አሳይተው ነበር ።

በኋላ ግን ውሎ አድሮ ፣ " የራስ አባተ አሳብ ወይዘሮ ዘውዲቱን ለማንገሥና ራሱ የእንደራሴነት ሥልጣን ለመያዝ ነው" የሚለው ወሬ በርክቶ ስለተወራ ፣ የዚህን ሁኔታ ያልደገፉት እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ፣ እነራስ ሉልሰገድ ኢያሱ ራሳቸውን ችለው እንደ ኑዛዜው ቃል ቢገዙ ይሻላል ብለው በመወሰን አቤቶ ኢያሱን ስለደገፉ የራስ አባተ ሐሳብ ውድቅ ሆነ ። ቢሆንም ግንቦት 21 ቀን 1903 ዓ.ም. "የራስ አባተና የልጅ ኢያሱ ጦር ሊዋጋ ነው ፤ ከተማውም ሊሸበር ነው" ተብሎ ሰው ሁሉ ሲሠጋ ውሎ ነበር ። ነገር ግን ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ወደ ሁለቱም ወገኖች ተመላልሰው ጦርነቱን ወደ ሰላም መለሱት ። ራስ አባተም በነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ተጽዕኖ አዲስ አበባን ፣ ለቀው በግማሽ ግዞት ወደ ግዛታቸው ወደ ከምባታ ሔዱ ።

ከዚህ በኋላ፣ የልጅ ኢያሱ አባት ራስ ሚካኤል ፣ "ልጅዎን ከሥልጣን ሊገለብጡ እነራስ አባተ ተነሥተዋል" የሚለትን ወሬ ሰምተው

ነበርና ሲገሠግሡ ከወሎ መጥተው አዲስ አበባ ገብተው ፣ ከነፊ
ታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ጋር ተገናኝተው ፣ የነራስ አባተ ሐሳብ መከ
ሸፋንም ፣ ራስ አባተም ወደ ግዛታቸው ሔደው ነገሩ መረጋጋቱን
ሰሙ ። ቢሆንም "አሁንስ ራስ አባተ ይኸን ምኞቱን ትቶ ሰላማዊ
ሆኗል ወይ ? አንድ ሰላይ ሔዶ ሁኔታውን መርምሮ ይመለስ "
ብለው ራስ ሚካኤል ስለተጫኑ ፣ አንድ ሰው ወደ ከንባታ ሔዶ
ሁኔታውን መርምሮ እንዲመለስ ተላከ ። ሰውዬው ደርሶ ሲመለስ ፣
"ራስ አባተ ሥራዬ ብለው የያዙት ወታደር ማብላትና ማጠጣት ፣
ማስፎከር ነው አሳባቸው አልበረደም "የሚል ሐሳብ አቀረበ ።

እንግዲያውስ ይጠሩ ተብሎ በ1904 ዓ. ም. በመስከረም ወር
የጥሪ ወረቀት ቢደርሳቸው አባተ "አሞኛል" ብለው ሳይመጡ ቀሩ ።
በዚህ ጊዜ አሁንም በራስ ሚካኤል ተጽዕኖ የከምባታ ግዛት
ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በዐዋጅ መሰጠቱ ተነገረና ወዲያው
የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ምስለኔ (እንደራሴ) ከምባታ ሲደርስ
በራስ አባተ ውስጥ የነበረው የቁጥር* ጦርና ከአሽከሮችም ውስጥ እየ
ከዱ ወደ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ እንደራሴ ዞሩና በራስ አባተ
ውስጥ የቤት አሽከር ብቻ ቀረ ።

ከዚህ በኋላ ከሹማምንቶቻቸው አንዱ ፣ "የራሳችን ሰው ከድቶ
እጃችንን ይዞ ሳይሰጠን እኛው በፈቃዳችን ወደ አዲስ አበባ ብን
ሔድ ይሻላል" ብሎ ስለመከረ ፣ አባተም "እውነትህ ነው" ብለው
አሳቡን ተቀብለው በታኅሣሥ 19 ቀን ወደ አዲስ አበባ መጡ ። እን
ደመጡም ያለብዙ ማንገራገር ራስ ሚካኤል እጃቸውን ተረከበው
ይዘዋቸው ወደ ወሎ ሲሔዱ አፍቀራ ላይ አሰሩዋቸው ።

ልጅ ኢያሱ ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ መቀመጫ ቤታቸው በራስ
ተሰማ ቤት ነበር ። የራስ ተሰማ ባለቤት የነበሩት ወይዘሮ በለጥሻ
ቸው አባጀቢርም ፣ በመልካም አያያዝ ወጣቱን መስፍን ያስተናግዳሉ
ሲባል ፣ ሌላው የበለጠ ፍቅራቸውን እማውራት ደረሰ ። ኢያሱ ግን
መቀመጫቸውን ከራስ ተሰማ ቤት አዛውረው በአባታቸው በራስ
ሚካኤል ቤት አደረጉ ። አንዳንድ ጊዜም ወደ ደሴ እየሔዱ አባታቸው
ዘንድ ይሰነብታሉ ። በዚህ መካከልም "የጊሚራ ሕዝብ ባገረ ገዥው

* የቁጥር ጦር ማለት አሽከር ሳይሆን በራስ አባተ ሥር ቢታዘዝም ደንበኛ የመንግ
ሥት ወታደር ነው ።



በደጃዝማች ሙሉጌታ ላይ አምጧል" ስለተባለ ፣ በግንቦት ወር
1904 ዓ.ም. ከደሴ ተነሥተው ወደ ጊሚራ ሔደው አምጠዋል የተባሉ
ትን ቀጥተው አገሩን ካረጋጉ በኋላ ፣ የክረምቱን ወራት በዚያው አሳ
ልፈው በጥር ወር አዲስ አበባ ገብተው ሹም ሽር አደረጉ ።

በዚህ ጊዜ ፣ "ልጅ ኢያሱ አያታቸውን ዐፄ ምኒልክን ከቤተ
መንግሥት አስወጥተው ወደ አንኮበር ሊሰዱዋቸውና እርሳቸው ቤተ
መንግሥቱን መቀመጫ ሊያደርጉ ነው" የሚል ወሬ በከተማው
ተነዛ ። መቼም አንዱ ሰው ምንም ስመጥር ንጉሥ ቢሆን ፣ በጣም በዘ
መኑ የተወደደና የሕዝብ አባት ቢባልም ፣ እርሱ በሕመም ወድቆ
የመዳን ተስፋ ሲያጣ ፣ እንደ ኢያሱ ያለ አፍላ ወጣት አለሁ አለሁ
ሲል ፣ "ይኸን አድርግ ፣ ይኸን አታድርግ አይዞህ እኛ አለንልህ" እያለ
በዙሪያው በማነብነብ ርስትና ጉልት ፣ ሹመትና ማዕረግ ፈላጊው
ብዙ ነው ። ስለዚህ ያዬ ምኒልክ ሕመምተኛነት ጊዜው ሲቀጥል ለሥ
ልጣን የቸኰሉ ሰዎች ፣ "እርሳቸው አንኮበር ሔደው ይተኙ ፣ ቤተ መን
ግሥቱን ለኛ ይልቀቁልን " የሚል መካር ይጠፋል ማለት አይቻ
ልም ። በዚህ ጊዜ 17ኛውን ዓመት ዕድሜ የያዙት ኢያሱ ይኸን
የመሰለው አሳብ ለወጣትነትና ለሥልጣን አምሮታቸው ሳይጥም
አይቀርም ።

ነገር ግን ፣ የግቢ ዘበኞች አለቃ ፊታውራሪ ገብረ ማርያምና ምክ
ትላቸው ቀኛዝማች ደቻሳ ፣ "ከንዳችንን ሳንንተራስ ጌታችንን ከቤቱ
የሚያስወጣው የለም " እያሉ ይፎክሩ ዠመር ። ከውጭም ወገን የልጅ
ኢያሱ ወገኖች እነፊታውራሪ አሸናፊ ጥሰው ወደ ግቢ ለመግባት
ተደራጅተው ምቹ ጊዜ ሲያማርጡ ፣ ከነርሱ ወገን የካቲት 1 ቀን
1905 ዓ.ም. ቅዳሜ ወደ ማታ ያንድ ጥይት ተኩስ ተሰማ ። በዚህ ጊዜ
እነፊታውራሪ ገብረ ማርያም በቋፍ ነበሩና እየተፏከሩ ከሁለቱም
ወገን ተኩሱ እስከ ሌሊቱ 5 ሰዓት ድረስ ከቆየ በኋላ በረደ ። የሆነ
ሆኖ ፣ በዚህ ግጭትና በተባራሪ ጥይት ከዐሥር እስከ ዐሥራ አምስት
ሰዎች ሞቱ ይባላል ።

በማግሥቱ እሑድ ጳጳሱና እጨጌው ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ
ነገሩ በስምምነት አለቀና ልጅ ኢያሱን በመፍራት ፊታውራሪ ገብረ ማር
ያምና ቀኛዝማች ደቻሳ አቡኑ ቤት ሔደው እንደቆዩ በመጨረሻ ፊታ
ውራሪ ገብረ ማርያም ወደ ጐንደር ለራስ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ቀኛዝማች
ደቻሳ ወደ ጐጃም ለራስ ኃይሉ በግዞት ተልከው እስከ ሰገሌ ዘመቻ
ድረስ በዚያው ቆዩ ። የግቢውን የዘበኝነት እልቅና ፊታውራሪ
ተሰማ ገዝሙ ደጃዝማች ተብለው ተሾሙ ። ወዲያውም ሕዝቡን
ለማረጋጋት ሲባል ፣ "ንጉሠ ነገሥቱን ከግቢ ለማስወጣት በፍጹም

አልታሰበም" የሚል በሚኒስትሮች ስም አንድ መግለጫ ታትሞ ወጣ ። በረኸመ ተጽፎና ታትሞ ከተበተነው ውስጥ እንደዚህ የሚል ይገኝበታል ።

> የሚኒስትሮች የምክር ቃል ... የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ከጥንት ዠምሮ ራሱን የቻለ ቢሆን ጭራሽ በዓለም ሁሉ የታወቀው በ፪ ምኒልክ ነው ።...ዐ፪ ምኒልክ ሕመማቸው በርትቶ አቤት በመዋላቸው አዝነን ሳለን እረኛ እንደ ሌለው በጐች እንዳንበተን ያልጋ ወራሽ ልጃቸውን ልጅ ኢያሱን በመስጠታቸው እጅግ ደስ አለን... እኛ ግን ...እየተስማማን መንግሥታችንን እየጠበቅን በፍቅር መኖራችንን ትተን እርስ በርሳችን እየተጣላን ለባእድ መሣለቂያ እንዳንሆን ጃንሆይ የመከሩንን ምክር ጠንክረን ማጽናት ይገባናል ።... መንግሥቱን ወዶ በአንድነት ተስማምቶ የሚኖረውን ሕዝቡን አለያይቶ ለማፋጀት ደም ለማፍሰስ ጃንሆይን አንኮበር ሊያወርዷቸው ነው የሚል የሐሰት ወሬ ተወራ ። ጠላትን አጥፍተው ከትንሽ እስከ ትልቅ ሁሉንም በየማዕረጉ ሹመው ፣ ሸልመው ኢትዮጵያን አልምተው ያቆዩንን አባታችንን ጌታችንን ጃንሆይን በዚህ በነቀስ አይውጡብን ብለን ስንጨነቅ እንዴት ያለ ክርስቲያን አንኮበር ይውረዱ ብሎ ይመክራል? ወይስ እንዴት ያለ ልጅ አባቱን አስወጥቶ እልግባ ይላል?...እሁንም ይኸ ሁሉ ክፉ አሳብ በልጅ ኢያሱም ፣ በእኛም ልብ እንዳልታሰበ ያው መሐላና ግዝት ይድረስብን ።...ይኸም የሐሰት ወሬ መንግሥቱና ሀገሩን ከሚወድ ሰው እንዳልወጣ የታወቀ ነው ። እሁንም ይህ ወሬ ከምቀኛ የመጣ ነውና ይህን ወሬ ያወራ ቢገኝ የመንግሥት በደለኛ መሆኑ ይታወቅ ። እሱ ግን ተሰውሮ ይኸን የእንክርዳድ ዘሩን እየዘራ ስንዴ ልባችንን በእረም ሊያበላሽ ያሰበ ነው ። ይኸንን ያወራ ምቀኛ ...ከመካከላችን ነው ። በመሐላ በግዝት እውጥተን እንለየው ...ወደፊት ጃንሆይ እንደመከሩን ነቀስ እንዳይገባብን አንድ ልብ ሁነን በፍቅር መንግሥታችንን ብንጠብቅ መልካም ነው ። ታኅሣሥ 11 ቀን 1905 ዓ ም. አዲስ አበባ ከተማ 1

በልጅ ኢያሱና በወገኖቻቸው ዘንድ ያፄ ምኒልክ ሞት መዘግየት ለሥልጣን እያያዘ በመጠኑ እንቅፋት በመሆኑ ፣ አንኮበር ይዛወሩ የሚባለው ሤራ ሳይጠነሰስ እንዳልቀረ የታወቀ ነው ። የነፊታውራሪ ገብረ ማርያም ተቃውሞ ግርግር ባያስነሣና ሰሚውንም እንዴት ተደርጎ ባያሰኘው ኖሮ አሳቡ በቀላሉ ሊፈጸም በቻለ ነበር ። ነገር ግን ፣ ጉዳዩ እስከ መቃኰስ ከተማ እስከ ማሸበር ሲያደርስ ወደኋላ እፈግፍጎ ፣ "እንዲያውም አልታሰበም" ማለት ዐውቆ የመሸንፍ ዘዴኛነት ነው ። በዚህ ዘመን ያሉት ሚኒስትሮችም ተሰብስበው ኃላፊነት በመስጠት የንጉሡ ነገሥቱን ምክር በመገምገም የሕዝቡንም ትርታ በማጤን ፣ ሕዝቡን ለማረጋጋት ይኸን ማስታወቂያ ማውጣታቸው የተገባ ነው ።

1. An Amharic Reader, Major J. I. Eadie, P. 79





ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቢነግዴ

ከሐድሰን መጽሐፍ

አልታሰበም'' የሚል በሚኒስትሮች ስም አንድ መግለጫ ታትሞ ወጣ ። በረኸርሙ ተጽፎና ታትሞ ከተበተነው ውስጥ እንደዚህ የሚል ይገኝበታል ።

የሚኒስትሮች የምክር ቃል . የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ከጥንት ዠምሮ ራሱን የቻለ ቢሆን ጭራሽ በዓለም ሁሉ የታወቀው ባፄ ምኒልክ ነው ።...ዐፄ ምኒልክ ሕመማቸው በርትቶ እቤት በመዋላቸው አዝነን ሳለን እረኛ እንደ ሌለው በጐች እንዳንበተን ያልጋ ወራሽ ልጃቸውን ልጅ ኢያሱን በመስጠታቸው እጅግ ደስ አለን... እኛ ግን ...እየተስማማን መንግሥታችንን እየጠበቅን በፍቅር መኖራችንን ትተን እርስ በርሳችን እየተጣላን ለባእድ መጫለቂያ እንዳን ሆን ጃንሆይ የመከሩንን ምክር ጠንክረን ማጽናት ይገባናል ።... መንግሥቱን ወዶ በአንድነት ተስማምቶ የሚኖረውን ሕዝቡን አለያይቶ ለማፋጀት ደም ለማፍሰስ ጃንሆይን አንኮበር ሊያወርዱቸው ነው የሚል የሐሰት ወሬ ተወራ ። ጠላትን አጥፍተው ከትንሽ እስከ ትልቅ ሁሉንም በየማዕረጉ ሹመው ፣ ሸልመው ኢትዮጵያን አልምተው ያቆዩንን አባታችንን ጌታችንን ጃንሆይን በዚህ በነፋስ አይውጡብን ብለን ስንጨነቅ እንዴት ያለ ክርስቲያን አንኮበር ይውረዱ ብሎ ይመክራል? ወይስ እንዴት ያለ ልጅ አባቱን አስወጥቶ እኔ ልግባ ይላል?...አሁንም ይኸ ሁሉ ክፉ አሳብ በልጅ ኢያሱም ፣ በእኛም ልብ እንዳልታሰበ ያው መሐላና ግዝት ይድረስብን ።...ይኸም የሐስት ወሬ መንግሥቱና ሀገሩን ከሚወድ ሰው እንዳልወጣ የታወቀ ነው ። አሁንም ይህ ወሬ ከምቀኛ የወጣ ነውና ይህን ወሬ ያወራ ቢገኝ የመንግሥት በደለኛ መሆኑ ይታወቅ ። እሱ ግን ተሰውሮ ይኸን የእንክርዳድ ዘሩን እየዘራ ስንዴ ልባችንን በአረም ሊያበላሽ ያሰበ ነው ። ይኸንን ያወራ ምቀኛ ...ከመካከላችን ነው ። በመሐላ በግዝት አውጥተን እንለየው ...ወደፊት ጃንሆይ እንደመከሩን ነፋስ እንዳይገባብን አንድ ልብ ሁነን በፍቅር መንግሥታችንን ብንጠብቅ መልካም ነው ። ታኅሣሥ 11 ቀን 1905 ዓ ም. አዲስ አበባ ከተማ 1

በልጅ ኢያሱና በወገኖቻቸው ዘንድ ያፄ ምኒልክ ሞት መዘግየት ለሥልጣን አያያዝ በመጡኑ እንቅፋት በመሆኑ ፣ አንኮበር ይዛወሩ የሚባለው ሤራ ሳይጠነሰስ እንዳልቀረ የታወቀ ነው ። የነፊታውራሪ ገብረ ማርያም ተቃውሞ ግርግር ባያስነሣና ሰሚውንም እንዴት ተደርጎ ባያስኘው ኖሮ አሳቡ በቀላሉ ሊፈጸም በቻለ ነበር ። ነገር ግን ፤ ጉዳዩ እስከ መታኮስ ከተማ እስከ ማሸበር ሲያደርስ ወደኋላ አፈግፍጎ ፤ "እንዲያውም አልታሰበም'' ማለት ዐውቆ የመሸነፍ ዘዴኛነት ነው ። በዚህ ዘመን ያሉት ሚኒስትሮችም ተሰብስበው ኃላፊነት በመሰማት የንጉሡ ነገሥቱን ምክር በመገምገም የሕዝቡንም ቅሬታ በማጤን ፤ ሕዝቡን ለማረጋጋት ይኸን ማስታወቂያ ማውጣታቸው የተገባ ነው ።

1. An Amharic Reader, Major J. I. Eadie, P. 79





ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቢነግዴ

ከሐድሰን መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሰባ ስድስት

## የደጃዝማች ሥዩምና የራስ ቢቶደድ መንገሻ አቲከም ጠብ

ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት ፣ በዚህ በሸዋ የንጉሠ ነገሥቱ ሕመም ብዙ ነገር እንዳናጋ በጐጃም የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሞት ብዙ ጠብ ፣ ብዙ መለያየት ፈጥሯል ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በወጣትነታቸው ዘመን ራስ በዛብህን ፣ ቀጥሎም ደጃዝማች በለውን ከዚያም ወደፊት ራስ ኃይሉ የተባሉትን ደጃዝማች ሥዩምን ከተለያዩ ሴቶች ወልደዋል ። በመጽሐፍ ከምናውቀው ከአቤሴሎም ዝምድ ያደገ ልጅ ብዙ ምኞት ስለሚያደርበት ከወላጅ አባቱ ጋር አይስማማም ። ለም ሳሌ ደጃዝማች አስፋው ዙፋን እየተመኙ ስለ አስቸገሩ ፣ አባታቸው ራስ ዳርጌ አስረው ወደ ዐፄ ምኒልክ ላኩላቸው ። ምኒልክ ግን ፣ "ምንም እንኳን እርሳቸው ልጃቸውን አስረው ቢልኩልኝ አላስርም" ብለው አስፋውን ፈትተው ወደ ባሌ ልከዋቸው ነበር ። በቅርቡም ራስ ሥዩም መንገሻ ልጃቸውን ደጃች ካሣን በንግሥት ዘውዲቱ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ የላኩበት ሁኔታ ተመሳሳይ ነው ።

እንደዚሁም ራስ በዛብህና ደጃዝማች በለው ፣ በየምክንያቱ ካባታቸው ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ስምምነት አጥተው አዲስ አበባ መጥተው ለነርሱ ለሰዋቸውም ድርጎ እየተቀበሉ በደጅ ጥናት መቀመጣቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ በ1893 ዓ. ም. ሲሞቱ የኑዛዜው ቃል ትክክል አለመሆኑ ፣ በሦስቱ ወንድማማቾችና በባለቤታቸው በወይዘሮ ላቀች ገብረ መድኅን መካከል ብዙ ውዝግብ ፈጥሮ ነበር ።

አለቃ ተክለ ሥላሴ የዚህን ሁኔታ ሲዘረዝሩ ፣ ከዐርባው በኋላ ራስ ወርቄና* ደጃች ሥዩም የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ዘውድና መጣሪያ (የወግ ዕቃ) ይዘው ፣ አዲስ አበባ መጥተው ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበው ደጃዝማች ሥዩም እስከ ሙት ዓመት ድረስ ቁርባን እያስቀረቡ የመቆየትን ፣ ይኸውም ማለት የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን

---

* ከራስ ደረሶ በኋላ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደራሴ የነበሩ ።

ንብረትና ቤት ይዘው ለጊዜው እንዲያስተዳድሩ መጠየቃቸውን አመልክተዋል ። ይኸም የሆነበት ምክንያት ሁለቱ ታላላቅ ወንድማማቾች ከአባታቸው ተጣልተው አዲስ አበባ በቆዩበት ሰዓት ፣ ትንሹ ደጃዝማች ሥዩም ከአባታቸው ሳይለዩ አስታመው በመቅበራቸው ነው ።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ በሕመም በደከሙበት ሰዓት "የአልጋዬ ወራሽ ራስ በዛብህ ነው" የሚል በመልእክ ገንት አሥራት እጅ አጽፈው ማኅተም አሳትመው ላፄ ምኒልክ ሲልኩ ፣ ሚስትዩዋ ወይዘሮ ላቀች ደግሞ ከንስሐ አባትየው ጋር ተመሳጥረው ፣ "ልጆቼን ይዛ በአልጋዬ (በሥልጣኔ) ላቀች ትቀመጥ" የሚል ማኅተም አቀረቡ ።በበኩላቸው ደጃዝማች ሥዩም "ወራሼ እሱ ይሁን" የሚል ማኅተም አትመው ከጐጃም ላኩ ። ታላላቆቹ ልጆች ራስ በዛብህና ደጃዝማች በለው "የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጆች ትልልቆቹ እኛ ነንና ለእኛ ይሰጠን ኑዛዜውም ለኛ ነው የሚፈቅደው" የሚል አቤቱታ አቀረቡ ። ደጃዝማች ሥዩም ፣ "አባታችሁን በድላችሁ ፣ ተክዳችሁ አድራችኋል ፤ አይገባችሁም ። ኑዛዜውም ለኔ ነው" የሚል መልስ ስለሰጡ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በነገሩ ተቸግረውበት ቆይተው በመጨረሻ ፣ "ስለ ኑዛዜው ጉዳይ ንስሐ አባቱን እስክመረምርና የመጨረሻ ውሳኔ እስካደርስ ድረስ ደጃዝማች ሥዩም አባቱን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን አስታሞ ስለ ቀበረና የሙት ዓመት ተዝካር ለማውጣት ስለሰመነ ሔዶ ያውጣ ። ወደፊት ክርስቶስ ለፈቀደለትና ለእኔ ለሚመቸው አስቤ መክሬ እሾማለሁ" ብለው መወሰናቸውን አለቃ ተክሌ ሥላሴ መዝግበዋል ።

ከዚህ በኋላ ፣ በዓመቱ በአዲስ አበባ ተመክሮ ተዘክሮ ንጉሠ ነገሥቱ ሰፊውን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ግዛት የነበረውን ከሦስት ላይ ክፍለው ጐጃምን ለደጃዝማች ሥዩም ፣ ጉድሩንና የወለጋን ሰሜናዊውን ክፍል ለደጃዝማች ደምሰው ነሲቡ ፣ ከጐጃም ምዕራብ የሚገኘውን የዳሞትና የአገው ምድርን ግዛት ለራስ ቢቶደድ መንገሻ አቲከም ሰጡ ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ የንጉሥ ተክለሃይማኖትን ጠቅላላ ግዛት ላንዱ ልጅ ወይም ለሦስቱም ሳያከፋፍሉ በመቅረታቸው የጐጃም ሰው ቅሬታ ገብቶት ነበረ ። በዚህም ጊዜ አቅራሪ፦

እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ጐበኘው ፤
የአባጠናን አገር ማነው የተመኘው ።

ምን ያለ ንጉሥ ነው ቂሙን የማይረሳ ፤
የአባ ጠናን አገር ሰጠው ለኮሳሳ ።



ጋሻውን ውሰዱት ጐራዴውን ውሰዱት ነፍጡንም ውሰዱት . . . እንዲሆን ለምስል ፤

የዚህ ቤት እዚያ ቤት አይገባ አይመስል ።

በስተቦረና በስተበላያ በስተደንገል በር ያቀናውን አገር ፤
እስረከቦት መጣ አወይ የልጅ ነገር ።

ተብሎ እንደ ተገጠመ ተክለ ሥላሴ ያስረዱናል ።*

ነገር ግን ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ጐጃምን ለሦስቱ ልጆች ቢያከፋፍሉ ከሦስት አንዱ በተለይ ትልቁ ቅር በመሰኘት የርስ በርሱ ጦርነት አይቀርም ነበር ። መቼም በሸዋም ፣ በጐንደርም ዘመነ መንግሥት (15—19 መቶ ዓመታት) ዳሞትና አገው ምድር ከጐጃም እየተለየ ይሾምበታል ። በነኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመነ መንግሥት ጐጃምን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የዘር አባቶች እነ ታላቅ ራስ ኃይሉ ፣ ያስተዳድሩት ነበር ። በዘመነ መሳፍንትም በዳሞት እነደጃዝማች ዘውዱ ሲገዙ በጐጃም እነራስ መርድ ነበሩ ። ነገር ግን አንዱ ኃይል ሲሰማው ሌላውን መደረቡ ፣ የዳሞት ባላባት የንጉሠ ነገሥቱ ባለሟል ሲሆን ፣ ጐጃምን ወይም የጐጃሙ ዳሞትን በውስጡ ማድረጉ የተለመደ ነው ።

ራስ አዳል ፣ በፊት ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ቀጥሎም ያፄ ዮሐንስ ባለሟል በነበሩበት ሰዓት ፣ ዐፄ ዮሐንስ በጐጃም ላይ ዳሞትንና አገው ምድርን አክለው ስማቸውን ተክለ ሃይማኖት ብለው ሲያነግሷቸው ራስ ቢቶወደድ መንገሻ የዳሞትና የአገው ባላባትነት የኔ ነው በማለት ቅርተኛ ነበሩ ።

ይኸም ሲሆን ደጃዝማች ሥዩም ፤ ለራስ ቢቶደድ መንገሻ አቲከም ፍጹም ታማኝ በመምሰል ፡ " . . ዛሬ ከራስ መንገሻ ብንሆን ልባችን ካንተ ነው ፤ ናልን እንውጋው ያለው ጦር ያባትህ (የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት) ጦር ነው እያሉ ይልኩብኛል ። እኔ ግን አባቴን እርስዎን አልወጋም እያልሁ ዝም ብዬ ተቀምጫለሁ ። በነአፈንጉሥ ይግዛው ተንኮል ይንቁባቸው" የሚል ደብዳቤ ጽፈው ለራስ መንገሻ ላኩ ። ራስ መንገሻም ይኸ መልእክት ሲደርሳቸው ፣ "በውነት ይኸ ነገር መሆኑን የማውቀው ፣ ያንተንም ልጅነት የምረዳው እንውጋው ናልን

*እባ ጠና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የፈረስ ስም ነው ። ቂሙን የማይረሳ የተባሉት ንጉሠ ነገሥቱ ምኒልክ ናቸው ። ቂሙ የእምባቦ ጦርነት ይሆን ? እንደውነቱ በዚህ ምንም ዓይነት ቂም አልነበረም ። «የዚህ ቤት እዚያ ቤት አይገባ ይመስል» የተባለው በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ላይ የደረሰው ሞት ባፄ ምኒልክም እንደሚደርስ ለማለት ነው ። አወይ የልጅ ነገር የተባሉት ሥዩም ናቸው ።

ብለው የላኩብህን ደብዳቤ ስታሳየኝ ነው ። ደብዳቤውን ካላሳየኸኝ
በውነትም ልትወጋኝ ከጅለሃል ማለት ነው" ብለው መለሱ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ደጃዝማች ሥዩም አለቃ ተክሌና አለቃ ተገኝ በሚ
ባሉ ሠዓሊዎችና ጥበበኞች አማካይነት በአፈ ንጉሥ ይግዛው ስም
አዲስ ማኅተም አመሳስለው አስቀርፀው ፣ "ናልን መንገሻን እንውጋ"
ብለው እነርሱ እንደ ላኩባቸው አስመስለው አስተኛውን ማኅተም
አትመው ለራስ መንገሻ ላኩላቸው ። መንገሻም እውነተኛ ማኅተም
መስሏቸው ለካ ያለሁት የኔን ሞት ከሚፈልጉ ጠላቶቼ ጋር ነውና"
ብለው ሁሉንም አስረው ዝርዝር ሁኔታውን ጨምረው በ1894
ዓ. ም. አዲስ አበባ ወዳፄ ምኒልክ ላኩዋቸው ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ደጃዝማች ሥዩምንና አዲስ ማኅተም አስመስ
ለው ቀርፀዋል የተባሉትን አለቃ ተገኝንና አለቃ ተክሌን ወደ አዲስ
አበባ አስመጥተው ጉዳዩ በጉባዔ በሚታይበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ
አፈ ንጉሥ ይግዛውን ራስ መስፍንን ፣ ፊታውራሪ ጎሉንና ፊታውራሪ
መሸሻን እንደ ተያዙ ፣ "ይኸ የናንተ ደብዳቤና ማኅተም አይደለምን?"
ብለው አሳይተው ቢጠይቋቸው ፣ "ማኅተሙ ይመስላል ፤ እኛ ግን
እንደዚህ ያለውን ሥራ አልሠራነውም ። ነገር ግን ጠላትን አጥፍቶ
አገር አስፍቶ ያነገሠዎ የጃንሆይ አምላክ እውነተኛ ፍርዱን አይነሣዎ
ምና እንደ ገለጸልዎ ይመርምሩልን " ብለው መለሱ ። በዚህ ጊዜ
በጉባዔው ያለው መኳንንት ግማሹ ፣ "ከማኅተም ወዲያ ምን ምስክር
አለ ? ይቀጡ ?" ሲል ፣ ሌላው "ማኅተም የያዘውን አሽከር በገንዘብ
ገዝቶ ቢያሳትመውስ ?" ሲባባል ንጉሠ ነገሥቱ የተያዙትን የመኳ
ንንቱን እውነተኛ ማኅተምና ደጃዝማች ሥዩም ያሠሩትን ሐሰተኛ
ውን ማኅተም አቅርበው በማስተያየትና በመመርመር ፣ ትንሽ ልዩነት
ስለታየ ንጉሠ ነገሥቱ ፊታቸውን ወደ ደጃዝማች ሥዩም አዙረው
"እውነቱን ንገረኝ ። በኋላ ከደህ የተገለጸብህ እንደሆነ ቅጣቱ ይከብ
ድብሃልና እውነቱን ብትነግረኝ ይሻልሃል" ብለው ቢጠይቋቸው
" . . . እንዲህ ያለውን እግዚአብሔር ከገለጸልዎ በኋላ እንደ ምሕረ
ትዎና እንደ ቸርነትዎ ያድርጉ እንጂ ምን እሰውርዎ አለሁ" ብለው
አመኑ ።

በዚህ ጊዜ ተይዘው የነበሩት መኳንንት ፡ ከእስራት ነጻ ሆነው
"ይቀጣልን" ብለው ጮሁ ። በጉባዔው የተገኙት መሳፍንትና መኳ
ንንት ሁሉ ባንድ ቃል "ያስቀጣዋል" ብለው ስለፈረዱ ፣ ደጃዝማች
ሥዩም እጃቸው ተይዞ ወደ እፍቀራ ለመላክ ከጉባዔ ሲወጡ ከጐጃም
"ደጃዝማች ሥዩም በድለውናል" ብለው ወደ አዲስ አበባ ላቤቱታ
መጥተው የነበሩ የወንድ መኳንንትም ፣ የሴት ወይዛዝርትም ብዙ
ነበሩና ተይዘው ባጠገባቸው ሲያልፉ ዕልልታቸውን አቀለጡት ።



ደጃዝማች ሥዩም እንደተያዙ ፣ "ወንድሞቼ ይገዙሻል እንጂ አንቺ
አትገዥም" የሚል ቃል ለሴቶቹ ወርውረው ወደ ግዞት ቦታቸው ወደ
አፍቀራ ሔዱ ።

እንደ ተባለውም ፣ ለታላቅ ወንድማቸው ለራስ በዛብህ በጐጃም
ላይ ሙሉ ሽልማት አድርገው ሾመው ወዲያውም ዝምድና እንዲጠ
ነክር በማለት ንጉሠ ነገሥቱ ከራስ ሚካኤልና ከወይዘሮ ሸዋረጋ
የተወለደችውን ወይዘሮ ዘነበወርቅ የምትባለዋን የልጅ ልጃቸውን
ዳሩላቸው ። ዳሩ ግን አሁንም ራስ በዛብህ ፣ "በርሷ ሰበብ ዳሞትን አገ
ኛለሁ ፤ ራስ ቢቶደደ መንገሻም አርጅተው ይሞታሉ" የሚል ምኞት
አድሮባቸው ሳለ በመካከሉ ሴትዮዋ ቀድማ ሞተች ። የሞተችውም
ተደብድባ ነው ይባላል ። ቀጥሎም ደጃዝማች ወዳጄ የሚባሉ ሚስ
ታቸውን በቅንዓት ደብድበው ገድለው ሸፍተው ሳለ ፣ የሚች ዘመዶች
"አዲስ አበባ መጥተው እንፋረዳለንና ይቅረቡልን" ብለው አመለ
ከቱ ። እንዲቀርቡም ተደጋግሞ ለራስ በዛብህ ቢላክ ውስጠ ስምም
ነት ኖሮ ሳይልኳቸው ቀሩ ። በኋላ ግን ፣ በሌሎቹ በራስ በዛብህ መኳ
ንንቶች ግፊት ወዳጄን በወታደር አሲይዘው ወደ አዲስ አበባ ራሳ
ቸው ይዘዋቸው መጡ ። ሲመጡም ወዳጄ መንገድ ለመንገድ ፣ "ብቻ
ዬን አልሞትም " ብለው ዝተው ነበርና አሁን በራስ በዛብህ አቅራ
ቢነት ሲፈረድባቸው ፣ "እኔና ራስ በዛብህ ጃንሆይን ከድተን ራስ መን
ገሻ አቲከምን ልንወጋ ተስማምተናል" በማለት ራስ በዛብህ ስለ
ዚሁ በወዳጅነታቸው ጊዜ የጻፉላቸውን ደብዳቤ አቀረቡ ። ሰነዱም
የራስ በዛብህን ውስጠ ክዳት ስላጋለጠ ራስ በዛብህ ወዲያው ተይ
ዘው ወደአፍቀራ ሲላኩ ፣ ደጃዝማች ሥዩም ከአቀፍራ መጥተው ጐጃ
ምን ለሁለተኛ ጊዜ ተሾሙ ።[1]

እርስ በርስ መዋጋት በሁሉም አገር ይደርሳል ። ነገር ግን በኢትዮ
ጵያ ከደረሰው ጋር ሲያመዛዝኑት የኛው የከፋ ይመስላል ። ሕዝቡ
መሳፍንቱን ወዳድ ሲሆን ፣ መሳፍንቱ በየራሱ የሥልጣን ምኞት
እየተዋጠ በግዴታ ካልሆነ በቀር ለሌላው መታዘዙን የማይወድ
ነው ። ለጊዜው ታማኝ ቢመስልም ጊዜና ወቅት አማርጦ የሚሸፍት ፣
እስራትም ግዞትም የማይበግረው ስለሆነ ፣ ጠቅላላው ሕዝብ የጸጥ
ጥታና የሰላም ጊዜ ያገኘበት ዘመን በጣም አጭር ነው ። የኢትዮጵያ
ንም ከጠቅላላ ታሪኩ ሰባ በመቶውን የያዘው የጦርነት ታሪክ መሆኑ
አሳዛኝ ነው ። አገራችንንም በልማት ወደኋላ ያስቀረ ይኸው
ሁኔታ ነው ።

1 የአለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፣ ምዕራፍ 51—54 ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ
ምኒልክ ፣ ምዕራፍ 70 ።

ብለው የላኩብህን ደብዳቤ ስታሳየኝ ነው ። ደብዳቤውን ካላሳየኸኝ በውነትም ልትወጋኝ ከጅለሃል ማለት ነው” ብለው መለሱ ።

በዚህ ጊዜ ፥ ደጃዝማች ሥዩም አለቃ ተክሌና አለቃ ተገኝ በሚባሉ ሠዓሊዎችና ጥበበኞች አማካይነት በአፈ ንጉሥ ይግዛው ስም አዲስ ማኅተም አመሳስለው አስቀርፀው ፥ “ናልን መንገሻን እንውጋ” ብለው እነርሱ እንደ ላኩባቸው አስመስለው አስተኛውን ማኅተም አትመው ለራስ መንገሻ ላኩላቸው ። መንገሻም እውነተኛ ማኅተም መስሏቸው ለካ ያለሁት የኔን ሞት ከሚፈልጉ ጠላቶቼ ጋር ነውና” ብለው ሁሉንም አስረው ዝርዝር ሁኔታውን ጨምረው በ1894 ዓ. ም. አዲስ አበባ ወዳፄ ምኒልክ ላከዋቸው ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፥ ደጃዝማች ሥዩምንና አዲስ ማኅተም አስመስለው ቀርፀዋል የተባሉትን አለቃ ቱገኝንና አለቃ ተክሌን ወደ አዲስ አበባ አስመጥተው ጉዳዩ በጉባዔ በሚታይበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ አፈ ንጉሥ ይግዛውን ራስ መስፍንን ፥ ፊታውራሪ ኃሉንና ፊታውራሪ መሸሻን እንደ ተያዙ ፥ “ይኽ የናንተ ደብዳቤና ማኅተም አይደለምን?” ብለው አሳይተው ቢጠይቋቸው ፥ “ማኅተሙ ይመስላል ፤ እኛ ግን እንደዚህ ያለውን ሥራ አልሠራነውም ። ነገር ግን ጠላትን አጥፍቶ አገር አስፍቶ ያነገሠዎ የጃንሆይ አምላክ እውነተኛ ፍርዱን አይነሣዎ ምና እንደ ገለጸልዎ ይመርምሩልን ” ብለው መለሱ ። በዚህ ጊዜ በጉባዔው ያለው መኳንንት ግማሹ ፥ “ከማኅተም ወዲያ ምን ምስክር አለ ? ይቀጡ ?” ሲል ፥ ሌላው “ማኅተም የያዘውን አሽከር በገንዘብ ገዝቶ ቢያሳትመውስ ?” ሲባባል ንጉሠ ነገሥቱ የተያዙትን የመኳንንቱን እውነተኛ ማኅተምና ደጃዝማች ሥዩም ያሠሩትን ሐሰተኛውን ማኅተም አቅርበው በማስተያየትና በመመርመር ፥ ትንሽ ልዩነት ስለታየ ንጉሠ ነገሥቱ ፊታቸውን ወደ ደጃዝማች ሥዩም አዙረው ፥ “እውነቱን ንገረኝ ። በኋላ ከደህ የተገለጸብህ እንደሆነ ቅጣቱ ይከብድብሃልና እውነቱን ብትነግረኝ ይሻልሃል” ብለው ቢጠይቋቸው ፥ “ . . . እንዲህ ያለውን እግዚአብሔር ከገለጸልዎ በኋላ እንደ ምሕረትዎና እንደ ቸርነትዎ ያድርጉ እንጂ ምን እሰውርዎ አለሁ” ብለው አመኑ ።

በዚህ ጊዜ ተይዘው የነበሩት መኳንንት ፡ ከእስራት ነጻ ሆነው “ይቀጣልን” ብለው ጮሁ ። በጉባዔው የተገኙት መሳፍንትና መኳንንት ሁሉ ባንድ ቃል “ያስቀጣዋል” ብለው ስለፈረዱ ፥ ደጃዝማች ሥዩም እጃቸው ተይዞ ወደ አፍቀራ ለመላክ ከጉባዔ ሲወጡ ከጐጃም “ደጃዝማች ሥዩም በድለውናል” ብለው ወደ አዲስ አበባ ላቤቱታ መጥተው የነበሩ የወንድ መኳንንትም ፥ የሴት ወይዛዝርትም ብዙ ነበሩና ተይዘው ባጠገባቸው ሲያልፉ ዕልልታቸውን አቀሰጡት ።



ደጃዝማች ሥዩም እንደተያዙ ፥ “ወንድሞቼ ይገዙሻል እንጂ አንቺ አትገዥም” የሚል ቃል ለሴቶቹ ወርውረው ወደ ግዞት ቦታቸው ወደ አፍቀራ ሔዱ ።

እንደ ተባለውም ፥ ለታላቅ ወንድማቸው ለራስ በዛብህ በጐጃም ላይ ሙሉ ሽልማት አድርገው ሾመው ወዲያውም ዝምድና እንዲጠነክር በማለት ንጉሠ ነገሥቱ ከራስ ሚካኤልና ከወይዘሮ ሸዋረጋ የተወለደችውን ወይዘሮ ዘነበወርቅ የምትባለዋን የልጅ ልጃቸውን ዳሩላቸው ። ዳሩ ግን አሁንም ራስ በዛብህ ፥ “በርሷ ሰበብ ዳሞትን አገኛለሁ ፤ ራስ ቢቶደድ መንገሻም አርጅተው ይሞታሉ” የሚል ምኞት አድሮባቸው ሳለ በመካከሉ ሴትዮዋ ቀድማ ሞተች ። የሞተችውም ተደብድባ ነው ይባላል ። ቀጥሎም ደጃዝማች ወዳጆ የሚባሉ ሚስታቸውን በቅንዓት ደብድበው ገድለው ሸፍተው ሳለ ፥ የሟች ዘመዶች “አዲስ አበባ መጥተው እንፋረዳለንና ይቅረቡልን” ብለው አመለከቱ ። እንዲቀርቡም ተደጋግሞ ለራስ በዛብህ ቢላክ ውስጠ ስምምነት ኖሮ ሳይልኳቸው ቀሩ ። በኋላ ግን ፥ በሌሎቹ በራስ በዛብህ መኳንንቶች ግፊት ወዳጆን ዘወታደር አሲይዘው ወደ አዲስ አበባ ራሳቸው ይዘዋቸው መጡ ። ሲመጡም ወዳጆ መንገድ ለመንገድ ፥ “ብቻዬን አልሞትም” ብለው ዝተው ነበርና አሁን በራስ በዛብህ አቅራቢነት ሲፈረድባቸው ፥ “እኔና ራስ በዛብህ ጃንሆይን ከድተን ራስ መንገሻ አቲከምን ልንወጋ ተስማምተናል” በማለት ራስ በዛብህ ስለዚሁ በወዳጅነታቸው ጊዜ የጻፉላቸውን ደብዳቤ አቀረቡ ። ሰነዱም ራስ በዛብህን ውስጠ ክዳት ስላጋለጠ ራስ በዛብህ ወዲያው ተይዘው ወደአፍቀራ ሲላኩ ፥ ደጃዝማች ሥዩም ከአቀፍራ መጥተው ጐጃምን ለሁለተኛ ጊዜ ተሾሙ ።[1]

እርስ በርስ መዋጋት በሁሉም አገር ይደርሳል ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ከደረሰው ጋር ሲያመዛዝኑት የኛው የከፋ ይመስላል ። ሕዝቡ መሳፍንቱን ወዳድ ሲሆን ፡ መሳፍንቱ በየራሱ የሥልጣን ምኞት የተዋጠ በግድታ ካልሆነ በቀር ለሌላው መታዘዙን የማይወድ ነው ። ለጊዜው ታማኝ ቢመስልም ጊዜና ወቅት አማርጦ የሚሸፍት ፡ እስራትም ግዞትም የማይበግረው ስለሆነ ፥ ጠቅላላው ሕዝብ የጸጥታና የሰላም ጊዜ ያገኘበት ዘመን በጣም አጭር ነው ። የኢትዮጵያም ከጠቅላላ ታሪኩ ሰባ በመቶውን የያዘው የጦርነት ታሪክ መሆኑ አሳዛኝ ነው ። አገራችንንም በልማት ወደኋላ ያስቀረ ይኸው ሁኔታ ነው ።

1 የአለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፥ ምዕራፍ 51—54 ፥ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፥ ምዕራፍ 70 ።

# ምዕራፍ ሰባ ሰባት

## የንጉሠ ነገሥቱ ዳግማዊ ምኒልክ ዕረፍት ።

ገናናው ንጉሠ ነገሥት ፣ በ1900 ዓ.ም. የገርመራቸው በሽታ እየጸና ሔዶ በመጨረሻ ሰውነታቸው ዝሎ እንደበታቸው ተዘግቶ እንደቆየ በታኅሣሥ 3 ቀን 1906 ዓ. ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ። የሸዋ ንጉሥ ፣ በኋላም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በነበሩበት ዘመን ሁሉ ክፉውን በክፉ ሳይሆን ፣ ክፉውን በደግነት እየመለሱ ፣ ጥፋትን ሁሉ በትዕግሥት እያሸነፉ ፣ አገር የሚሰፋበትን ፣ ልማት የሚዳብር በትን ፣ ሕዝብ ዕረፍትና ሰላም የሚያገኝበትን ከማሰብና ከመፈጸም አልተቆጠቡም ። የአውሮፓን ኃያል መንግሥት በጦር ሜዳ በማሸ ነፍ ኢትዮጵያን በዓለም እንድትደነቅ አድርገዋል ። ስለዚህ ሥርዓተ ቀብራቸው በታላቅ ሥነ በዓል መሳፍንትና መኳንንት ፣ የውጭ መላክ ተኞች በተሰበሰቡበት በወግ በማዕረግ ሊፈጸም በተገባ ነበር ።

ዳሩ ግን ፣ ባልሠለጠኑና በሕገ መንግሥት መተዳደርን ባልለመዱ አገሮችና በኢትዮጵያ በወግ በማዕረግ የሚቀበር ንጉሥ ፣ በዙፋን በሰላም የሚተካ አልጋ ወራሽ ማግኘት ብርቅ ነው ። በዚህ ምክን ያት ፣ የሞተን ንጉሥ ግርግር እንዳይነሣ አቻኩሎ በድብቅ መቅበርና ከዚያ ምቹ ወቅት ጠብቆ "የሞትንም እኛ ፣ ያለንም እኛ" ብሎ ዐውጆ ተወላጁን ማንገሥ የኢትዮጵያ ዓይነተኛ መልክ ነው ። አልፎ አልፎ ንጉሥ ታመመ ሲባል ፣ ሹክሹክታውና መታመሱ ወደ ግርግ ርታ ፣ ሲሞት ደግሞ ግርግታው ወደ ረብሻ ፣ ረብሻው ወደ ጦርነት ይለወጣል ። ባለፈው በኢትዮጵያ ታሪክ ፣ ንጉሥ በታመመና ከሕ መም ወደሞት በተሻገረ ቁጥር ወራሹ በዙፋኑ እስኪረጋጋ ድረስ ያለው የቤተ መንግሥታችን ደንበኛ ሁኔታው ይህ ነው ። በዚህም ሰበብ የሚሞተው ፣ የሚሰደደውና ንብረቱ የሚባክነው ብዙ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ሲሞቱ ፣ ተፋጠ የተቀመጠው የኢያሱ ወገን በአንድ በኩል ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ እስከ መጨረሻ የታመነው ፣ የእቴጌ ተከታይና የራስ አባተ አሰራት የቆጨው ፣ በሌላው በኩል እያሉ ፣ ሁሉም

በአንድነት ተሰብስቦ የሚወዳቸውን ንጉሠ ነገሥት በወግና በሥርዓት ፥ በሰላምና በጸጥታ ለመቅበር አዳጋች መሆኑን ታላላቆቹ እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ተገንዝበዋል ። ሞታቸው ራሱ የተሰማ እንደሆነ ቀደም ብሎ የተቀያየመው በዚህ ጊዜ ገንፍሎ እርስ በርሱ ተዋግቶ አገር ይሸበራል በማለት ታላቁንና ስመ ጥሩውን ንጉሠ ነገሥት በዝምታና በሹልክታ እዚያው ቤተ መንግሥቱ ግቢ ባለው ሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ቀበሩዋቸው ። ወጣቱ ኢያሱም በዚህ ቀን ጃንሜዳ የፈረስ ጉግሥ ይጫወቱ ነበር ይባላል ። ይኸንንም ፥ "የሚወዳቸው ሕዝብ በንጉሠ ነገሥቱ ሞት እንዳይገነግን ሆነ ብለው ነው" ብሎ ግማሹ ሲያሳብብላቸው ፤ የቀረው ደግሞ "አሳድጎ ለዚህ መንግሥት ያበቃ አባትና አያት ሲሞት ጉግሥ መጫወት ውለታ ቢስነት ነው" ብሏል ። ይሁን እንጂ ፥ ምንም ለመደበቅ ቢሞከር ወሬው ካንዱ ወደሌላው እየተላለፈ ነገሩን የተረዳው ሁሉ "እምዬ ጌታዬ ! እምዬ አባቴ !" እያለ በየቤቱ ያለቅስ ነበር ። ከአልቃሾቹ አንዱ ፤

"ፈረስ በቅሎ ስጠኝ ብዬ አለምንህም
እምና ነበር እንጂ ዘንድሮ የለህም" አለ ይባላል ።

በንጉሠ ነገሥቱም ሞት ዋናዎቹ ሐዘንተኞች ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ፥ ልጃቸው ወይዘሮ ዘውዲቱና ብዙ መኳንንት አሉ ። በልቅሶውም ጊዜ እቴጌ ጣይቱ እንደዚህ ብለው ገጠሙ ይባላል ።

ነጋሪት ማስመታት ፥ እምቢልታ ማስነፋት ነበረ ሥራችን ፥
ሰው መሆን አይቀርም ደረሰ ተራችን ።[1]

ወይዘሮ ዘውዲቱ በበኩላቸው ደግሞ እንደዚህ አሉ ።

እልፍ ነፍጥ በኋላው እልፍ ነፍጥ በፊት ፥ ባለወርቅ
መጣብር እያሔው ፈረስ ፤
ይመስለኝ ነበረ ይኸ የማይፈርስ ።

33 ዘመን የበላንበቱ የጠጣንበቱ ፥
የትሣሥ ባታ ለት ተፈታ ወይ ቤቱ ።

ብትታመም ልጅህ እጅግ ጨነቀኝ ፥
ብትሞትስ አልሞትም እኔ ብልጥ ነኝ ።

1 ጣይቱ ብጡል አጭር የሕይወት ታሪክ ፥ ቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ ገጽ 59



ወልደውኛል እንጂ እኔ አልወለድሁዎ ፥
እንዠቴን ተብትበው ምነው መሔድዎ ።

አሳዳጊ አላንተ አላውቅም እናት ፥
ምነዋ ሞግዚቴ እንዲህ ያል ክዳት ።

ቀድሞ የምናየው የለመድነው ቀርቶ ፥
እንግዳ ሞት አየሁ ካባቴ ቤት ገብቶ ።

እጅግ አዝኛለሁ አላቅሽኝ አገሬ ፥
የሁሉ አባት ሞቶ ተጐዳችሁ ዛሬ ።

ትንሽ ትልቅ አይል ለሁሉ መስጠት ፥
ከጧት እስከ ማታ ያለመሰልቸት ።

ድርቅ ሆኗል አሉ ዘንድሮ አገራችሁ ፥
ዝናሙ ሲጠፋ ምነው ዝም አላችሁ ።

አሻግሬ ሳየው እንዲያ በሰው ላይ ፥
መከራም እንደሰው ይለመዳል ወይ ።[1]

የገናናው ንጉሠ ነገሥት አስከሬን በሥረገላ ሆኖ ፥ ጉንጉን አበባ ተረብርቦ ፥ በመሳፍንትና በመኳንንት ታጅቦ ፥ በነጋሪትና በእንቢልታ እየተሸኘ ፥ "እምዬ ጌታዬ" እየተባለ ፍትሐት እየተፈታ ፥ በይፋ በማልቀስ ወግና ሥርዓት ያለው አቀባበር አይደረግ እንጂ ፥ ብዙ መሳፍንትና መኳንንት በየቤታቸው አልቅሰዋል ።

ከነዚህም አንዱ ያፄ ምኒልክ ታማኝ አሽከር ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ የሚባሉት ፥ "ሣህለ ማርያም የሚባል ወንድሜ ሞቶ መርዶው መጣልኝ" ብለው ምክንያት በመስጠት ፥ በሐዘን እያለቀሱ እቤታቸው ሰንብተው በኋላም ለዐርባው አዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ድግስ ደግሰው ያፄ ምኒልክን ተዝካራቸውን አወጡ ። ሣህለ ማርያም ያፄ ምኒልክ የክርስትና ስማቸው ስለሆነ ፥ በወንድማቸው አመካኝተው ላፄ ምኒልክ ነው ሐዘኑም ተዝካሩም የተፈጸመው ።[2]

1. ያለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ ፥ ገጽ 202—203
2. አለቃ ገብረ እግዚአብሔር ኤልያስ የጽሑፍ ማስታወሻ ፥ ገጽ 44



ዓፄ ምኒልክ

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ
እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
ይድረስ ከኮንት ፔትሮ አንቶኔሊ ። ከመጣህ እስከ
ዛሬ ድረስ ስለ ተነጋገርነው ነገር ሁሉ ውሉ
እንደ በአዋሳ ሚያዝያ በ፲፱ በ፲፰፻፹፩ በተጻፈው ውል
እንደ ሆነ ፲፯ ቍጥር ክፍል ተስማምተን ይሰረዝ ስላ
ለ ከኝ ነገር ጣን ለኢትዮጵያ ለኢጣልያ መንግሥ
ት የማይስማማ ምላሽ ይስጡን ብለህ ስለ ለመን
ኸ ፲፯ ቍጥር ውን ክፍል ስማሪያ ምን በኢጣልያ ም
ት ጻፈውን ሰው ዘነዋል ይቀርም ስላልነ የሁሉ
ችንን መንግሥት ያስማማናት ይገባልና ለን
ጉሥ ሆምበርቶ የዚህን ፲፯ ቍጥር ክፍል ምላሽ
ሰዩ ፲ ልዋለሁና ከንጉሥ ሆምበርቶ ፊት
ደረሰ በኋላ ቀር የማላት ውን እንደለ ምላሹን
ተቀብለህ ማሉ እንድትልከው ተስፋ አደርጋለሁ ።
ጥር ፡ በሐቀን ፡ በ፲ ጥር ፲፰፻፹፪ ዓመተ ምሕረት በአዲስ አበባ ከ
ተማ ተጻፈ ።

ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አርኪቪዮ ስቶሪኮ

ሞዓ፡ አንበሳ፡ ዘእምነገደ፡ ይሁዳ፡ ዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ሥዩመ፡ እግዚአብሔ
፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ።

ይድረስ፡ ወደ፡ ክቡሩ፡ ወደ፡ ተቀዳሱ፡ የሮም፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ሊዎን፡ ፲፫ኛ።

ሰላም፡ ለርስዎ፡ ይሁን። የከበረው፡ ያባትነትዎ፡ ደብዳቤዎ፡ በቡነ፡ መቃር
ስ፡ እጅ፡ ደረሰልኝ። በዚህም፡ ደብዳቤዎ፡ የቀድሞው፡ መላላካችንን፡ አሳምሮ፡
ደያስታውስ፡ እግዚአብሔር፡ ከኔ፡ እጅ፡ የጣሳቸውን፡ ስለ፡ ኢጣልያ፡ ምርኮኞች፡
ርነት፡ ሥራ፡ እንዲሰራ፡ የሚያመለክት፡ መሆኑን፡ በጣም፡ አየሁ። ዳግመም፡
በሩ፡ ቅዱስነትዎ፡ ከአቡነ፡ መቃርስ፡ የበለጠ፡ መልክተኛ፡ ነገሩን፡ በጣም፡ አስረ
፡ አጣፍጦ፡ ሀሳብዎን፡ የሚናገር፡ መላክ፡ እንዳይቻልዎ፡ አወቅን። የክርስ
ን፡ ሁሉ፡ አባት፡ የላከው፡ እጅጋ፡ የሚያስደንቅ፡ ደብዳቤዎን፡ ባነበብሁ፡ ጊዜ፡
ን፡ መታው። ዳግመኛም፡ የከበረውን፡ የመልክተኛዎን፡ የቃል፡ ንግግር፡ በሰ
፡ ጊዜ፡ ልቤ፡ ቅዱስነትዎ፡ በማክበር፡ ስለመኑኝ፡ ጉዳይ፡ ለመፈጸም፡ ጨከነ፡ ነበ
ኔ፡ ሣልፈልገው፡ በዚህ፡ በክፉ፡ ጦር፡ የሞቸው፡ ለፈሰሰ፡ በከንቱ፡ ላለቁት፡
ጆሮች፡ እጅጋ፡ አለቀስሁ። ነገር፡ ግን፡ ቅዱስነትዎ፡ የተመኙትን፡ ለመፈጸም፡ የኢ
ያ፡ መንግሥት፡ ያልታሰበው፡ የዛሬ፡ ሥራቸው፡ የማያስፈቅድ መኝ፡ ሆነ። ይህ
፡ ማለቱ፡ የእርቅ፡ ፈቃድና፡ በጸሀይ፡ ለመላላክ፡ መመኘታቸውን፡ ካሳዩኝ፡ በ
ሥራቸው፡ በጦርነት፡ እንደአለን፡ አድርገው፡ ይዤ፡ ዝመር። አሁንም፡
ብኝ፡ ንጉሥነቴና፡ የሕዝብ፡ አባትነቴን፡ ይህን፡ አውቆ፡ በእጄ፡ ያለውን፡ የ
፡ መያዣ፡ መልቀቅ፡ የማይቻለኝ፡ ሆነ። ቅዱስነትዎ፡ ያሰበውን፡ ሀሳብ፡ ያለ፡

**ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**


**አርኪቭ ኢቲዮፒክ**

ለማስገኘት፡የኒኝም፡መልካሙን፡ሀሳብ፡ለመፈጸም፡ከለከለኝ። በክርስቲያንነቴና፡
በንጉሠነቴ፡ልብ፡አውሮፓ፡አውርጂ፡ሰበቃ፡የፍቅረን፡ምልክትና፡ብዙ፡ማክበ
ሬን፡በሌላ፡ቀን፡እደርግልሀ፡ማለቱ፡ለለሆነብኝ፡ዛሬ፡ሳይሆንልኝ፡በመቀረቱ፡አ
ጅግ፡ያሳዝነኛል። እግዚአብሔር፡እዳራ፡የሰጠኝ፡መንግሥቴን፡የሕዝቤን፡ነፃ
ነት፡የምፈልግ፡ስለሆንሁ፡በክርስቲያኖች፡ሁሉ፡በማክበር፡የሚሰማውን፡የቀ
ድስናም፡ቋምዐ፡ለኛ፡ብሰው፡እንዲያሰሙልኝ፡ተስፋ፡አለኝ። ይህ፡የሆነ፡እንዲሆ
ን፡ከዘመዶቻቸውም፡ለተለዩ፡ምርኮኞች፡በቀርቡ፡ለመመለስ፡እንዲመቸን፡
ዋድሬዓም፡ነው። ነገር፡ግን፡ይህ፡ነገር፡እስኪፈጸም፡ድረስ፡ከኔ፡ዘንድ፡ያሉትን፡
ምርኮኞች፡እንደ፡ክርስቲያን፡ሥራ፡ከዚህ፡ቀደም፡ጠብቄ፡በመልካም፡እድ
ጊ፡እንዲኖርኗቸው፡ይልቁንም፡ከእንግዲህ፡ወዲህ፡ስለር ሰዎ፡ፍቅር፡በ
ሙን፡ጠብቄ፡በደህና፡እሣምሬ፡እንዲኖሩቸው፡በዚህ፡አይጠርጥሩኝ።
መስከረም፡በ፳፩፡ቀን፡በደ.ሰ፡አበባ፡ከተማ፡ተጻፈ።
፲፰፻፷፱ ዓመተ፡ምሕረት።

የተላከ፡ ከእቴጌ፡ ጣይቱ፡ ብርሃን፡ ዘኢትዮጵያ።
ይድረስ፡ ከመጆር፡ ሲዘር፡ ኔራዚኒ፡ የኢጣሊያ፡ መ
ንግሥቱ፡ በለሙሉ፡ ሥልጣን፡ መልክተኛ።

ሰላም፡ ለንተ፡ ይሁን።

ስለፍቅር፡ የተደረገውን፡ ውል፡ የኢጣሊያ፡ ንጉሥ፡
ተቀብለው፡ እሃሙ፡ ብለዘ፡ የላከሽው፡ ደብዳቤ፡ ደረ
ሰልኝ። እጅግ፡ ደስ፡ አለኝ። ደግሞ፡ እግዚአብሔ
ር፡ ፍቅራችንን፡ ለዘለዓለም፡ እንዲያጸና፡ እስከ፡ ምጽአ
ት፡ ድረስ፡ የማይፈርስ፡ ይድርገው። በመጋቢት፡ በ
፲፰ ቀን፡ በደሴ፡ ከበባ፡ ከተማ፡ ተጻፈ።
በ፲፰፻፹፩ ዓመተ፡ ምሕረት።



ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አርኪቭዮ ኢቲዮፒኮ

የቱላስ፡ከራስ፡ዳርጌ፡ጋ፡ድረስ፡ከሐኪም፡ነራዚኒ፡እንዴት፡አለ
ህ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡ይመስገን፡ደህና፡ነኝ።
ወረቀትህም፡ደረሰልኝ።እኔ፡ከዚህ፡ቀደም፡አላውቅህም፡ነበ
ር።አሁን፡በወረቀትህ፡ነው፡ማወቄ።ከዚህ፡ቀደም፡ደህን፡
ደህል፡ቀን፡ሳላውቅህ፡መቅረቴ፡ምንኛ፡ተጎዳቻለሁ።አሁን
ም፡የልጅን፡የልጅ፡ጉዳዩን፡ነገር፡ወደ፡ኢጣልያኖች፡መግባ
ቱን፡የላክህብኝን፡ሰማሁ።ይኸማ፡ከሆነ፡መልካም፡ነው፡እን
ጂ፡ምን፡ነገር፡አለ፡ያጠ፡ምኒልክን፡አልጋ፡መቀበል፡ነው፡ሌ
ንጂ።እኔም፡ለባቱ፡አደባባይ፡አልጋውን፡ይዤ፡ተቀምጫ
ለሁ፡ምን፡የሚቀየር፡ነገር፡አለ።ዳሩ፡ግን፡ያንተ፡ደብዳቤ፡
ብቻ፡ነው፡እንጂ፡የመጣው፡የሌላ፡ደብዳቤ፡አልመጣልኝ
ም።ይህ፡ነገር፡አሰቱ፡ውሸት፡የሆነ፡እንደሆነ፡አንተ፡ንም፡ነ
ራዚኒ፡የተባልከውን፡የዚራ፡እባብ፡የለመርዝ፡ያስመስል
ሃል።ኢጣልያኖችንም፡ጉልበቱ፡ቢያንሣቸው፡የሃበሻን፡
ጉልበት፡የፈለጉ፡ያስመስላቸዋል። ያንተንም፡ሐኪምነት፡
የመልካም፡የደግ፡የነበርከውን፡የውሸትና፡የቀጥረት፡
ሐኪም፡ያስመስልህ፡ይመስላል።— ዳሩ፡ግን፡ሐሰቱን
ም፡እውነቱንም፡የሚያውቅ፡መለኮት፡ይመልከት።—
ባጥር፡በ፳ቀን፡ተጻፈ።ባዲስ፡አበባ፡ከተማ።በ፲ወ፰፻
ወ፹ዓመተ፡ምሕረት።




ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አርኪቪዮ ኢቲዮፒኮ

ዘተሰከ፡ከሌስ፡መከሥገግ ዘሐረየ ዐ
ውሬ፡ዲዋ፡ግቯ፡፡ ዉዓ፡ሪስ፡ከወዓ፡ን፡ነ
ዷከዋር፡ኔሌ፡ዣኔ፡፡—

ሰዓፃ፡ታየ፡ዓገቱ፡የዠዓ፡፡
በሰኤ፡በፂዋጓ፡የተዒሌ፡ወረቀትበ ዒረ
ሰሬኝ፡፡ የኔዓ፡አዩ፡፤፡የፏዓሆዉ፡ገፃበ ሳ
ክሁ፡፡ ጸ.ሃ፡ወረፋቱ፡ወዋ፡ዓ፡ዓጋከ፡ኒ
ስኒ፡ወመ፡ዒረስ፡ኦዚጸወ፡ዘሂዓ፡ኣ
ገዊቱ፡ቀዐ፡ዉሁዓ፡፡ ከፎዓሆዉ፡ፍቀዲ፡
ካፊወበግ፡ኔኔ፡ፍቃዴ፡ልሰዋሀ፡አዩቻ
ሰነፃዘ፡፡ እኔፃ፡በሂዩ፡ኩበኑ፡መዓገዲ
ኒዷ፡ግ፡ዒሉ፡በሎኝ፡ተጣዓት፡ኦቢቴ፡
፡ነሀ፡፡— ኔዎዜኔ፡በሐር፡ጫ.ር፡ዌ.ኮዋ
ህ፡፡ ተዓሌ፡ሰረር፡ሰኤ፡ፀተዋግ፡ፀየዘ

ከርማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አርኪቭና ኤቲዮፒያ

ደ፡ ሂ፡ ረስ፡ ንበ፡ ሥዩ ወ ንግዚአብሔር ዳግማዊ፡ ምኒልክ
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘኢትዮጵያ። ጂንሆዬ፡ የሬስ፡ ዲርገ
ን፡ ለማረፍ፡ የላኩብኝ፡ ከሁር፡ ለግሬትምዕዕ፡ ዊሬስኛ
አጅግ፡ አዘንሁ። እኔስ፡ ፈትም፡ የሕልግምዎኝ፡ ብርታ
ት፡ ስም ቸ፡ አዛጋር፡ አምበሩን፡ ለዴቀህሌኝ፡ ነ፡ ብዬ፡ ስ
ሂ፡ ጀ ው፡ ነበር። ዱርስ፡ ለሠጣ፡ ይካለግቸውን፡ ነግረኝ፡
አስገዜዋ፡ ነፍስ፡ አትለይምእንጂ፡ ለጸነፋቸውን፡ አ
ከዚኋም፡ ቀደም፡ ለለግሁ፡ አጠነት፡ ነጠ፡ አሁን ም፡
ጂንሆዬ፡ ምንም፡ የሁላችን፡ አባት፡ ቢሆኑ፡ የል
ለግን እግዚአብሔር ዋናውን እነስ፡ ጂንሆዬ፡ አ
ትምበጣ፡ ብለው፡ ቢልኩብኝ፡ ነው፡ እንጂ፡ ስንኳን፡
እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ ሲሆን፡ እንዲያው፡ም፡ ጂንሆዬ፡
ናፍቀውኝ፡ አለጣለሁ፡ ብዬ፡ ነበር። አሁንም፡ የ
ጓዘን፡ ደርቻ፡ ያጀርጣልን። የተላከ፡ ከጎንሥ፡ ተክ
ለ፡ ሃይማኖት፡ ሮቱዓ፡ ሃይማኖት፡ ወልደ፡ ለቅዱ
ስ፡ ማርቆስ፡ ወንጌላዊ፡ ሐዋርያ፡ አበ፡ ነጋሢ፡ ለዐይኑ
ኔ፡ ሳለም፡ ጠነ፡ ይ፡ አጥሌኝ፡ ብዬ፡ ፲፲፯ ዘ፡ እጅ፡ እነሣ
ለሁ፡ በመጋቢት፡ በ፳፯ቀን፡ በ፲፰፻፺፪ ዓመተ፡ ምሕ
ሕረት፡ በጉድሩ፡ ሰፈር፡ ተጻፈ። ፨ ፩



ክሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አርኪቪዮ ኢቲዮፒኮ

# UMBERTO I.

Per grazia di Dio e per volontà della Nazione

# Re d'Italia

A tutti coloro che le presenti vedranno, salute.

Un Trattato di

Commercio essendo stato concluso fra il Regno

የንግድ፡ውል።

[illegible]

## Traité de Commerce.

Sa Majesté Humbert I Roi [illegible] et Sa Majesté Menilek II Roi des Rois d'Éthiopie, pris dans l'intention de régler les rapports commerciaux, de les développer [illegible] rendre de plus en plus avantageux aux deux puissances contractantes, Sa Majesté Humbert I ayant envoyé et désigné ses pleins pouvoirs Monsieur le Major César Nerazzini, Grand officier de la Couronne d'Italie et chevalier des Saints Maurice et Lazare, S. M. Menilek II Roi des Rois d'Éthiopie en son propre nom et Monsieur le Major Nerazzini au nom de Sa Majesté le Roi Humbert ont convenu et stipulé ce qui suit.

### Article I.

Les sujets de chacune des deux parties contractantes auront pleine liberté d'entrer, de sortir et d'exercer leur commerce dans les territoires de l'autre, jouissant de la protection du gouvernement sous la juridiction duquel ils se trouvent.

### Article II.

Il est convenu que les deux parties contractantes feront de leur mieux

pour

[illegible]

፫ተኛ፡ክፍል

[illegible]

፬ተኛ፡ክፍል

[illegible]

፭ተኛ፡ክፍል

[illegible]

pour développer les routes de commerce entre leurs possessions et garantir aussi la sûreté des négociants et de leurs marchandises.

Article III.

Les sujets éthiopiens dans les États de l'Italie et les sujets italiens dans les États éthiopiens jouiront en ce qui concerne les droits de douane, les impôts intérieurs et le traitement général dans les avantages qui seront accordés par les deux gouvernements aux sujets d'autres nations.

Article IV.

Le transit des armes et munitions de guerre destinées à S. M. le Roi des Rois d'Éthiopie est autorisé à travers les territoires dépendants du gouvernement italien à la demande de Sa Majesté sous les conditions prescrites par l'acte général de la Conférence de Bruxelles, signé le 2 juillet 1890.

Article V.

Tout matériel destiné au service de l'État éthiopien aura le droit de passer en Éthiopie par les ports et territoires italiens en franchise de douane sur demande de S. M. le Roi des Rois d'Éthiopie, de

même

[illegible]

፮ተኛ፡ክፍል፡

[illegible]

፯ተኛ፡ክፍል፡

[illegible]

፰ተኛ፡ክፍል።

[illegible]

même tout le matériel destiné au service du gouvernement italien passera en franchise de douane par les portes et territoires éthiopiens.

## Article VI.

Dans le but de favoriser les rapports commerciaux entre les possessions italiennes du côté de l'Océan indien et le Sud de l'Empire d'Ethiopie, les deux gouvernements s'engagent d'étudier d'un commun accord l'établissement de routes commerciales nouvelles et sûres.

## Article VII.

Pour bien surveiller et garantir les rapports amicaux entre l'Italie et l'Ethiopie, les deux parties contractantes ont convenu de s'envoyer mutuellement des représentants agréés et choisis par chacun des deux gouvernements, et il est entendu qu'en cas qu'un représentant ne conviendrait pas, qu'il sera remplacé.

## Article VIII.

Le présent traité pourra être modifié et renouvelé d'un commun accord en tout ou en partie après trois ans à partir

[illegible]



partir de la date de sa signature. Dans ce cas les modifications devront être notifiées par la partie contractante qui les propose à l'autre partie six mois avant ce délai de trois ans.

## Article II.

Le présent traité devra être ratifié par le gouvernement de S. Majesté le Roi Humbert dans le délai de six mois à partir d'aujourd'hui et entrera en vigueur dès que la Ratification sera notifiée à S. Majesté l'Empereur d'Éthiopie.

En foi de quoi S. M. Ménélik II Roi des Rois d'Éthiopie en son propre nom et Monsieur le Major Nerazzini au nom de S. M. Humbert I Roi d'Italie ont signé le présent traité fait en deux exemplaires, écrit en amharique et en français identiquement, les deux textes étant considérés comme officiels et y ont apposé leurs sceaux.

Fait à Addis-Abeba le 24 juin 1897.



# በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የነበሩ መሳፍንትና መኳንንት

## ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ

አቤቶ ዳርጌ ፡ የፈረስ ስማቸው አባ ግርሻ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴና ከወይዘሮ ወሪኔ (የሥልጤ ባላባት ልጅ) ይወለዳሉ ።

ከዐፄ ቴዎድሮስ ዕረፍት በኋላ በእንግሊዝ የጦር አለቆች ፈቃድ እንደሌሎቹ ተፈትተው ፣ ወደ ሸዋ እንደመጡ በደጃዝማችነት ማዕረግ ቆይተው ፣ በ1871 ዓ.ም የራስነት ማዕረግ አግኝተው የራስ ወርቅ አሰሩ ።

በዓድዋ ዘመቻ ጊዜ (1888 ዓ.ም) ራስ ዳርጌ በአዲስ አበባ ተቀምጠው በእንደራሴነት ያገሪቱን ጸጥታ እየጠበቁ በደንብ አስተዳድረዋል ። ይኸም በዚያን ዘመን የምኒልክንና የእርሳቸውን መተማመን የሚያስረዳ ነው ።

ራስ ዳርጌ ፡ በጦርነትና በአስተዳደርም ኢትዮጵያን አገልግለው ዕድሜ ጠግበው ፡ ብዙ ዘር አትርፈው በ1892 ዓ.ም በመጋቢት 15 ቀን ዐርፈው ደብረ ሊባኖስ ገዳም በክብር ተቀበሩ ።

## ራስ ጐበና ዳጬ

ጐበና ያባታቸው ስም ዳጬ ፡ የእናታቸው ስም ጉራጊት ፡ የፈረስ ስማቸው አባ ጥጉ ፤ የትውልድ አገራቸው አብቹ ነው ።

ደጃዝማች ምኒልክ ፡ ከመቅደላ አምልጠው ከበዛብህ ጋር ጋዲሎ (ግድም) ላይ የተዋጉለት የሸዋ ተወላጅ ሁሉ ለምኒልክ ማድላቱን በመረዳት ፡ የበዛብህ አጋፋሪ የነበሩት ጐበናም የጋዲሎውን ጦርነት ከበዛብህ ጋር ሆነው ሳይካፈሉ ወደ ምኒልክ ስለዞሩ ፡ ወዲያው የደጃዝማችነት ማዕረግ አገኙ ። ቀጥሎም በ1871 ዓ.ም ከደጃዝማች ዳርጌ ጋር ሁለቱ ራስ ወርቅ አስረው የራስነት ማዕረግ ተቀበሉ ። እነዚህም የመጀመሪያዎቹ ያፄ ምኒልክ ራሶች መሆናቸው ነው ።

የደቡብ ክፍል አውራጃዎችን በማዕከላዊው መንግሥት ሥር ለማጽናት በተካሔደው ትግል ራስ ጐበና በአብዛኛው ዋና ተካፋይና የአፄ ምኒልክ ዋና የጦር መሪ ነበሩ ። በዝምንነትም ስመጥር ናቸው ። በዚያም ዘመን የዝምንነት ነገር በተነሣ ቁጥር "በትግሬ አሉላ ፤ በሸዋ ጐበና ፤ በጐጃም ደረሶ" እየተባለ የሦስቱ ዝነኛነት ጐልቶ ሲወራ ይኖራል ። ባፄ ምኒልክ መንግሥት ተከብረው

ተፈርተው ሲኖሩ ሰኔ 27 ቀን 1881 ዓ.ም. ሞተው ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ ።

## ደጃዝማች ናደው

ደጃዝማች ናደው ፤ የፈረስ ስማቸው አባ ባሕር ከንጉሥ ኃይለ መለኮት መኳንንት አንዱ ናቸው ። በዚህ ምክንያት ለምኒልክ ከልጅነት ጀምሮ ሞግዚት ነበሩ ።

ዐፄ ዮሐንስ ፤ ከእንግሊዞች በስጦታ ፤ ከግብጾችም በጦርነት ማር ከው ባገኙት በብዙ የጦር መሣሪያ ወታደራቸውን አስታጥቀው ወደ ሸዋ በዘመቱ ጊዜ ፤ እርሳቸውንና ምኒልክን ፤ ለማስማማት በተደረገው ግልግል ደጃዝማች ናደው ዋንኛው መላክተኛና ገላጋይ እንደነበሩ ይታወሳል ። እርሳቸውም የራስ ተሰማ አባት መሆናቸው ነው ። የሞቱበት ጊዜ አይታወቅም ።

## ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ

ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ ፤ የፈረስ ስማቸው አባ ጉራች የወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ሣህለ ሥላሴ ባለቤት ፤ የራስ መኰንን ፤ የደጃ ዝማች ኃይለማርያምና የወይዘሮ እህተ ማርያም አባት ናቸው ። ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፤ ከንጉሥ ኃይለ መለኮትና ከንጉሥ ምኒልክ ታላ ላቅ መኳንንት አንዱ ናቸው ። ግዛታቸው አንኮበር አጠገብ ጎላ የሚባለው ነበር ።

## ደጃዝማች ገርማሜ

ደጃዝማች ገርማሜ ወልደ ሐዋርያት ፤ የፈረስ ስማቸው አባ መላ የንጉሥ ኃይለመለኮት አሽከር ነበሩ ። ኃይለ መለኮት ከሞቱ ወዲህ ወጣቱን ምኒልክን ተከትለው አብረው ጐንደር ሔደው በዚያው ተቀ መጡ ። ወይዘሮ ቀጠሮን በሚስትነት አግብተው ታላቅ የወዳጅነት ግብዣ በማድረግ የምኒልክን ጠባቂዎች በመጠጥ አስክረው ምኒልክን ከመቅደላ እንዲያመልጡ ያደረጉ ገርማሜ ናቸው ።

ምኒልክ ሸዋ ገብተው ከነገሡ ወዲህ ፤ ከምኒልክ መኳንንት ከዋ ነኞቹ አንዱ ናቸው ። ዐፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ምኒልክ ከሸዋና ከወሎ አልፈው ቤጌምድርንና ጐጃምን አስገብራለሁ ብለው በ1869 ዓ.ም የዘመቱ ጊዜ በሸዋ የንጉሡ እንደራሴ የነበሩት ደጃዝማች ገርማሜ ነበሩ ።



ደጃዝማች ገርማሜ ምክር ዐዋቂና ለሞኛ ዘር ሁሉ እንደ በላይ አባት ሆነው ላፄ ምኒልክ ዋና አማካሪ ነበሩ ።

## ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣን

ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል ፤ ከመዠመሪያዎቹ ያፄ ምኒልክ ታላላቅ መኳንንት አንዱ ናቸው ። በጐንደሩም የግዞት ዘመን ከምኒልክ አል ተለዩም ።

ምኒልክ ወደሸዋ ተመልሰው ከነገሡ በኋላ ፤ ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል የሐረርጌን ዙሪያ ኢቱንና ጩርጩርን ያስተደደሩ ናቸው ። ዐፄ ምኒልክ ራሳቸው ወደ ሐረርጌ በዘመቱበት ጊዜ የሐረርን ግዛት ልሹምህ ቢሏቸው ለልጃቸው ለቀኛዝማች መኰንን ይስጡልኛል ብለው እምቢ አሉ ። ዐፄ ምኒልክ ለባላምባራስ መኰንን ወልደ ሚካኤል የደጃዝማችነት ማዕረግ ጨምረው ሐረርን ሰጧቸው ።

ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል የዚህን ወሬ ሲሰሙ ፤ "እዩጉድ ለኔ መኰንን ቀርቶ ለራሳቸው መኰንን ሰጡት" ብለው በጸጸት ተናገሩ ይባላል ። እርሳቸውም የራስ ብሩ አያት መሆናቸው ነው ። ብሩ በአባ ታቸው በሀብተ ማርያም በመጠራት ፈንታ በአያታቸው ብሩ ወልደ ገብርኤል ይባሉ ነበር ።

## ራስ መንገሻ አቲከም

መንገሻ አቲከም ፤ በአገው ምድር የባላባቱ የከንቲባ አቲከም ልጅ ናቸው ። በጐንደር ኑሮ ከምኒልክ ጋር ተዋውቀውና ተላምደው ነበ ርና ከቤጌምድር መጥተው ላፄ ምኔልክ አደሩ ። ጥቂት ጊዜ እንደቆዩ ደጃዝማች ተብለው ኤፍራታን ይገዙ ነበር ። ዐፄ ምኒልክ በዋሉበት በአብዛኛው አገር የማቅናት ጉዳይ በጦርነቱም በምክሩም አልተለዩም።

ዐፄ ዮሐንስ ፡ በ1881 ዓ.ም. ዐርፈው ምኒልክ የንጉሠ ነገሥትነቱን ሥልጣን እንደያዙ ፡ የራስነት ማዕረግ አግኝተው ዋና አማካሪ ሆነው የግል ጦራቸውን ይዘው የዓድዋን ዘመቻ ተካፍለዋል ። በመጨረሻም ራስ ቢቶደድ መንገሻ እየተባሉ እንደ ሙሉ እንደራሴ ሆነው ያፄ ምኒልክ ዋና አማካሪና ባለሟል ነዘሩ ። እርሳቸውም የራስ ከበደና የወይዘሮ ወሰንየለሽ አባት ፡ መሆናቸው ነው ።

## ራስ ወሌ ብጡል

ራስ ወሌ ብጡል ፡ ወሌ አባ ጠጣው ፡ በጐንደር ከደጃዝማች ምኒልክ ጋር ተዋውቀው በዚያው ሰበብ ወደሸዋ ከወንድማቸው ከአሉላ ጋር መጥተው ስለነበረ ወሌ የደጃዝማችነት ፡ አሉላ የፊታውራሪነት ማዕረግ አገኙ ። ቀጥሎም ታላቅ እህታቸው ወይዘሮ ጣይቱ ብጡል ከንጉሠ ምኒልክ ከተጋቡ ወዲህ ወሌ በአገልግሎትም ፡ በአማችነትም ስለ አስደሰቱ ፡ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ ወዲህ የራስነት ማዕረግ አግኝተው ባለሟል ሆኑ ። የዓድዋንም ጦርነት ተካፍለዋል ። በግዛትም ቤጌምድርን ፡ ከዚያም ለብዙ ጊዜያት የጁን እየተሾሙ በግዛት ወሰን ብዙ ጊዜ ከወሎው ከራስ ሚካኤል ጋር ይጣሉ ነበር ።

ራስ ወሌ በገጣሚነትም ስመጥር ከመሆን የተነሣ ፡ “ዐሥር ፊታውራሪ ሰባት ደጃዝማች የጠመቀውን ፡ የወሌ ፈረስ ጠጣው ብቻውን ” ተብሎ ተገጥሞላቸዋል ።

ወሌ የንግሥት ዘውዲቱን ባል ራስ ጉግሣን ፡ የራስ መንገሻ ዮሐንስን ባለቤት ወይዘሮ ከፈይንና ደጃች ዓመዴን ይወልዳሉ ።

## ራስ መኰንን ወልደ ሚካኤል

ራስ መኰንን አባ ቃኘው ፡ የንጉሠ ሣህለሥላሴ የልጅ ልጅ ፡ የወይዘሮ ተናኘ ወርቅና የደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ልጅ ናቸው ።

ከልጅነታቸው ጀምሮ ያፄ ምኒልክ የእልፍኝ አሽከር ሆነው ሲያገለግሉ ኖረው በብዙ የጦርነት ቦታም ውለው የራስነት ማዕርግ አገኝቶ ዋል ።

እንደ በኩር ልጅ የሚያዩዋቸው ምኒልክ አልጋ ወራሽ ሊያደርጉዋቸው ነው እየተባለ ሲወራ ፡ ወራሹ ከአውራሹ ቀድመው በ1898 ዓ. ም. መጋቢት 9 ቀን ዐርፈው ሐረርጌ በጥምቀተ ባሕር ሚካኤል ተቀበሩ ።

## አፈ ንጉሥ ነሲቡ

አፈ ንጉሥ ነሲቡ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ዳማ በንጉሠ ሣህለ ሥላሴና በንጉሥ ኃይለ መለኮት ጊዜ ባገራቸው በአልዩ አምባ ጠበቃ ሆነው አንኮበር ይሟገቱ ነበር ይባላል ። በ1890 ዓ . ም. በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚኒስትሮች ካቢኔ ሲቋቋም ፡ አፈ ንጉሥ ነሲቡ የፍርድ ሚኒስትር ሆነው እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሁሉም ተቀዳሚ ፣ በሁሉም ዘንድ ተፈሪና ተከባሪ እንደ ነበሩ ይነገራል ።



## ራስ ወልዴ አባ ሥዩም

የግድምና የኤፍራታ ባላባት ናቸው ። ላፄ ምኒልክ በፊት ደጃዝማች ወልዴ እየተባሉ ለረጅም ዘመን በወታደርነትም በአስተዳደርም አገልግለዋል ። በኋላም የራስነት ማዕረግ አግኝተዋል ። ወደ መስኮብና ወደ ፈረንሳይ አገር በመልእክት ሔደው የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማየት ችለዋል ።

## ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ

ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ሰጉድ ነው ። የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ፣ ያፄ ምኒልክ አክስት የወይዘሮ አያህሉሽም ልጅ ናቸው ።

በደቡብ ኢትዮጵያ አውራጃዎችን በማዕከላዊ መንግሥት ሥር ለማጽናት በተደረገው ጥረት የከፋውን ንጉሥ አሳምነው ላፄ ምኒልክ ያቀረቡ እርሳቸው ናቸው ። ቀጥሎም ወደ ጐንደር ተዛውረው ቤጌምድርንና ስሜንን አንድ አድርገው በራስነት ማዕረግ ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል ። ንግሥት ዘውዲቱ በ1909 ዓ . ም የነገሡ ጊዜ ፣ እርሳቸውንም በየካቲት ወር የጐንደር ንጉሥ ብለው ሾሟቸው ። ከዚያ ምንም ያህል ሳይቆዩ በየካቲት 24 ቀን 1910 ዓ . ም ሞተው በደብረ ታቦር ተቀበሩ ።

## ራስ ቢቶደድ ተሰማ ናደው

ራስ ተሰማ አባ ቀማው ፣ ያፄ ምኒልክ ሞግዚት የነበሩት የደጃዝማች ናደው ልጅ ናቸው ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንዳሉት በኢሉባቦር (ጐሬ) እስከ ነጭ አባይ ድረስ ያለውን አገር አቅንተዋል ።

ዐፄ ምኒልክ ከ1901 ዓ.ም. ጀምሮ ሕመም በተሰማቸውና ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሻቸው መሆኑን ባወጁ ጊዜ ለወጣቱ ለልጅ ኢያሱ ሞግዚትና የመንግሥቱ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነው ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል ። ነገር ግን ሳይታሰብ በድንገት ታመው በ1903 ዓ.ም. ሞተው በደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ ።

## ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ

መሸሻ ወርቄ ፣ የቤጌምድሩ ያፈ ንጉሥ ወርቄ ልጅ ናቸው ። ከቤጌምድር ወደ ሸዋ መጥተው ካፄ ምኒልክ መኳንንት አንዱ በመሆን አገልግለዋል ።

ሁለት ጊዜ በመልእክት ወደ አውሮፓ ሔደው ተመልሰዋል ። ከዓድዋ ጦርነት ወዲህ እርጅናም ሕመምም ተጭኗቸው ሞቱ ።

## አዛዥ ወልደ ጻድቅ

አዛዥ ወልደ ጻድቅ የፈረስ ስማቸው አባ መንዝር ፣ በጐንደር ዐሥር ዓመት ለምኒልክ ሲያገለግሉ ኖረው ምኒልክ ካፄ ቴዎድሮስ አምልጠው ሲመጡ ባንድነት መጡ ። ከዚህ በኋላ የወህኒ አዛዥ ተብለው የግህሰ ሥላሴንና የኃይለ መለኮትን ከተማ አንኮበርን ተሾመዋል ። ዳፄ ምኒልክ የታመኑና በቤተመንግሥቱም የታፈሩ ሆነው ሲኖሩ እዚያው አንኮበር ዐረፉ ።

## ነጋድራስ እግደው

ከጐንደር መጥተው ያፄ ምኒልክ ባለሟል ሆኑ ። በአዲስ አበባ ነጋድራስ እግደው እየተባሉ የከተማውን ፣ የገበያውን ሥርዓትና ንግዱን በመዠመሪያ ጊዜ ያስፋፉ ፣ መንግሥቱን በቀረጥ ያከበሩ እርሳቸው ናቸው ። የመንግሥት ጉምሩክ በአዲስ አበባ በርሳቸው ጊዜ በደንብ መቋቋሙን በቸርነትና በጌትነት የታወቁም እንደነበሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ይጠቁማሉ ።

እርሳቸውም ከኢጣልያ ወረራ ከ1928ዓ.ም በፊት ባለው ጊዜ የገንዘብ ሚኒስትር የነበሩት የበጅሮንድ ዘለቀ አባት መሆናቸው ነው ።

## ቢቶደድ አጥናፌ

ግብጾች ከሐረርጌ ሲባረሩ እርሳቸውና ፊታውራሪ ገበየሁ የሻቃነት ማዕረግ ነበራቸው ። ገበየሁ የጦር አበጋዝ ከሆኑ በኋላ ፣ አጥናፌ ወደ ቢቶደድነት ማዕረግ ከፍ ብለዋል ።

ቢቶደድ አጥናፌ ፣ በጣም የታወቁና በዓድዋ ዘመቻ ጊዜ እርሳቸው መደበኛ መሥሪያ ቤታቸውን ወረይሉ ከተማ አድርገው ከሸዋም ከያለበትም የሚመጣውን ስንቅ ተቀብለው እያደራጁ ለዘማች ወደ መቀሌ ፡ ወደ ዓድዋ በመላክ በጣም ተመስግነዋል ። በዚህም ከዓድዋ በኋላ ከምስጋና ጋር ከንጉሠ ነገሥቱ ኒሻን ተሸልመዋል ።

## ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቢነግዴ

ሀብተ ጊዮርጊስ ፡ የፈረስ ስማቸው አባ መቻል ነው ። በወሊሶና በአምቦ መካከል ባለው ጥቁር በሚባል ስፍራ ተወላጅ የሆኑት ሀብተ



ጊዮርጊስ ምኒልክ አካባቢውን ባቀኑበት ጊዜ አንድ ወታደር ማርኮ በኋላ በትእዛዝ ለመንግሥት አስረከባቸው ።

ባፄ ምኒልክ ፈቃድ አንኮበር ሔደው ባዛዥ ወልደ ጻድቅ ውስጥ ሆነው የመንግሥት ሥነ ሥርዓት እያጠኑ ቆዩ ። በኋላ ወደ ቤተመንግሥት መጥተው ባሽከርነት ሁሉንም እየተማሩ በማደግ የታወቁ ሆኑ ። ከዚያም ላፄ ምኒልክ ዕቁባት ለደጃዝማች አስፋወሰን እናት ለወይዘሮ ጌጤ እንደ እንደራሴ ሆነው የወሊሶንና የአመያ አውራጃን ያስተዳድሩ ነበር ። በመካከሉ የዓድዋ ጦርነት ስለ ተነሣ ሀብተ ጊዮርጊስ በዚያ አውራጃ ያለውን ጦር ይዘው ዘመቱ ።

በዓድዋ ጦርነት ላይ የጦር አበጋዝ የነበሩት ፊታውራሪ ገበየሁ በውጊያው ላይ በዠግንነት እንደሞቱ ወደ አዲስ አበባ መልስ ሆኖ የርሳቸውን የጦር አበጋዝ አዛዥነት ብዙ የጦር አለቆች በተለይ እነሊቀ መኳስ አባተ ሲመኙት ፣ ባፄ ምኒልክ ፈቃድ የራስ ወርቅ ጨምረው የጦር አበጋዝነቱን ሥልጣን ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሰጧቸው ። የተሾሙለት ባፄ ምኒልክ የጭን በቅሎ በቡሊት እንደ ተቀመጡና ንጉሠ ነገሥቱም እቤታቸው ድረስ ሔደው ግብር አብልተው እንዳከበሩዋቸው ይነገራል ።

ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በታኅሣሥ 3 ቀን 1919 ዓ.ም. ሞተው በታላቅ ክብር በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቀበሩ ።

## ራስ ናደው

ራስ ናደው ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ሙብረቅ ነው ። አባ ወሎ የሚሉዋቸውም አሉ ። ባፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ሊቀመኳስ ናደው እየተባሉ ዓድዋም ዘምተዋል ።

ከዚህ ወዲህ የራስነት ማዕረግ ይዘው ኢሉባቦርን ያስተዳድሩ ነበር ። በመልክት ወደ አውሮፓም ፣ ወደ አሜሪካም ፣ ወደ ኢየሩሳሌምም እየተላኩ የውጭ አገርን ሥልጣኔ ተመልክተዋል ።

## ራስ አባተ ቧ ያለው

ራስ አባተ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ይትረፍ ሲሆን በሸዋ የቤዛ ዘር ናቸው ። አባታቸው ደጃዝማች ቧያለው ይባላሉ ። ከልጅነታቸው ዠምሮ ባፄ ምኒልክ ቤተ መንግግሥት ያደጉ ናቸው ።

በዓድዋ ጦርነት በዠግንነት ተዋግተው አዲስ አበባ እንደተመለሱ የደጃዝማችነት ማዕረግ ተቀብለዋል ። ቀጥሎም ዋግሹም

ተብለው በዋግ ላይ የትግሬን የበላይነት ተሾሙ ። በኋላም ራስ ተብለው የንጉሥ ሚካኤልን ግዛት ወሎን ተሾመው እንደቆዩ ሞተው ደብረ ሊባኖስ በታላቅ ክብር ተቀበሩ ።

## ደጃዝማች ባልቻ

ባልቻ ፤ የፈረስ ስማቸው አባ ነፍሶ ነው ። በልጅነታቸው ከጦርነት ላይ ተማርከው ባፄ ምኒልክ ቤት ያደጉ ታማኝ የጦር መኰንን ነበሩ ። ብዙ ጊዜ በጅሮንድ ተብለው የንብረት ኃላፊ ሆነው ሠርተዋል ። አዲስ ዓለም ማርያም ስትሠራ ኃላፊው እርሳቸው ነበሩ ይባላል ።

የበለጠ እንደራስ አባተ የሚታወቁት በወታደራዊ መስክ ነው። በመቀሌውና በዓድዋው ጦርነት በዠግንነት ተዋግተው ስመጥርነት አግኝተዋል ።

ከዓድዋ መልስ በደጃዝማችነት ማዕረግ ሲዳሞን ሌላ ጊዜ ሐረርጌን ተሾመው አስተዳድረዋል ። በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን በክብርና በታላቅ ማዕረግ ሲኖሩ ፤ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር ስምምነት ስለ አልነበራቸው ፤ ብዙውን ጊዜያቸውን በግዞት አሳልፈዋል ።

በ1928 ዓ.ም የኢጣልያ ፋሺስት የዓድዋውን ብድር ለመመለስ በተዋጋበትና አዲስ አበባን በያዘበት ጊዜ በ80 ዓመት ዕድሜያቸው በአርበኝነት ዘመቱ ። "ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያልቻሉትን ጠላት እርስዎ ሊመልሱት አይችሉምና ለጣልያን ቢገቡ ይሻላል" ብለው ቢመክሩዋቸው ፤ "ሽምግያለሁ መሞት እንደሆን አይቀር ፤ በሰማይ ላይ ጌታዬ ምኒልክ በኢትዮጵያ ዙፋኔ ላይ ማነው የተቀመጠው ብለው ቢጠይቁኝ ምን ብዬ እመልሳለሁ" የሚል ቃል ወርውረው ሽማግሌው እንደ ወጣት በወጨጫ ከጠላት ጋር ተዋግተው ሞቱ ።

## ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ

ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ፤ የደጃዝማች ባርያ ጋብር ልጅ ናቸው። ከዓድዋ ጦርነት ወዲህ በራስ አሉላ ውስጥ ሆነው ሠርተዋል ። መዠመሪያ የደጃዝማችነት ማዕረግ እንደያዙ ዓድዋን ቀጥሎ ፤ በንቡረ ዕድነት የራስ ወርቅ አስረው አክሱምን ጭምር ያስተዳድሩ ነበር ።

ዐፄ ምኒልክ ከሞቱ ወዲህ ፤ ደጃዝማች ገብረሥላሴ ከልጅ ኢያሱም ሆነ በርሳቸው ፈቃድ የወሎና የትግራይ ንጉሥ ከተባሉት አባታቸው ከራስ ሚካኤል ጋር ስምምነት ስለ አልነበራቸው ፤ ንጉሥ ሚካኤልን



ከደገፉት ከራስ ስብሐት እንደዚሁም ከራስ ሥዩም ጋር ጦርነት ገጥመው ራስ ስብሐት በጦርነት ሞቱ ።

ከዚህ በኋላ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ከቤጌምድር ጦር ይዘው ወደ ዓድዋ ሲዘምቱ ገብረ ሥላሴ እሥመራ ሔደው ተቀመጡ ። የልጅ ኢያሱ መንግሥት ወድቆ ንግሥት ዘውዲቱ ሲነግሡ ከእሥመራ በመልእክት ተላልከው ይቅርታ ተደርጎላቸው ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከንግሥት ባለሟሎች አንዱ ነበሩ ።

በኋላ ግን ፤ ከአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ጋር ብዙም ስምምነት ስላልነበራቸው በሜጫ ተግዘው እንዳሉ ለጠበል ሚጣቅ አማኑኤል ሔደው በዚያው ዐርፈው ሬሳቸው አክሱም ሔዶ ተቀበረ ።

## ሌሎች መኳንንት

ባፄ ምኒልክ ዘመን ፤ በወጣትነታቸው ጊዜ የእልፍኝ አሽከር በመሆን ወደ መጨረሻው እስከ ሚኒስትርነት ወይም እስከ ከፍተኛ የሹመት ደረጃ የደረሱት ብዙ ናቸው ። ታሪካቸውን በዝርዝር የማናውቀው ስለሆነና በጣም የበረከቱ ስለሆኑ ፤ ስማቸውን ብቻ ከነማዕርጋቸው ከዚህ ቀጥሎ እናመለከታለን ።

ቱርክ ባሻ ታምሬ ፤ ደጃዝማች አስፋው ዳርጌ ፤ ደጃዝማች ገሠሠ ብጡል ፤ ራስ ሉል ሰገድ ፤ ራስ ብሩ ወልደ ገብርኤል ፤ራስ ጌታቸው አባተ ፤ ቢቶደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደሚካኤል ፤ ቢቶደድ ወልደ ጻድቅ ጐሹ ፤ ቢቶደድ ወልደ ገብርኤል ፤ ራስ ሙሉ ጌታ ፤ ደጃዝማች መኰንን ተወንድ በላይ ፤ ሊጋባ ሠራዊቱ ፤ ቀኛዝማች በየነ ይመር ፤ ደጃዝማች ብሩ ኃይለ ማርያም ፤ ደጃዝማች ለማ አቦዬ ፤ ደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ ፤ አዛዥ ደግፌ ፤ አዛዥ ወሰኔ ፤ አዛዥ ግዛው ፤ ደጃዝማች መታፈሪያ መልከጼዴቅ ፤ ፊታውራሪ ወልደ ገብርኤል ከተሬ ፤ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፤ ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ ፤ አፈንጉሥ እስጢፋኖስ አፈንጉሥ ከተማ ፤ ደጃዝማች ገነሜ ፤ አዛዥ አባ ተምሳስ አዛዥ ስንቄ አዛዥ በዛበህ አዛዥ ኃይለ ሥላሴ ፊታውራሪ ገብረማርያም ቀኛዝማች ደቻሳ ሌሎችም የማናውቃቸው ወይም የዘነጋናቸው ሊኖሩ ይችላሉ ። ከዚህም በተ ጨማሪ ደጃዝማች ጫጫ ፤ ፊታውራሪ ገበየሁ ፤ ፊታውራሪ ዳምጠውና ቀኛዝማች ታፈሰ ዓባይነህ የተባሉት ስመጥር መኳንንት በዚህ መ ጽሐፍ ውስጥ በየምዕራፉ ታሪካቸው የተወሳ ስለሆነ ፤ ከዚህ እ ንደገና መዘርዘሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም ።

# ዋቢ መጻሕፍት

## ካገር ውስጥ


**መንግሥቱ ለማ**

መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ፤ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ. ማተሚያ ቤት ፤ 1959 ዓ.ም.

**መሠረት ስብሐት ለአብ**

ትውፊታዊ ኃሳብ ዘመንና ታሪኩ ንግድ ማተሚያ ቤት 1981

**ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (ብላቴንጌታ)**

ዝክረ ነገር ፤ 2ኛ እትም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1962 ዓ.ም.

**መኩንን እንዳልካቸው (ቢትወደድ)**

መልካም ቤተሰቦች ፤ አሥመራ ፤ ኮሬዮሬ ኤሪትሬዮ ፤ ማህበር ማተሚያ ቤት ፤ 1949 ዓ.ም.

**ተክለ ሥላሴ ዋቅጅራ (አለቃ)**

ታሪካዊ የእጅ ጽሑፍ (ያልታተመ)

**ተክለ ጻድቅ መኩሪያ**

የኢትዮጵያ ታሪክ ፤ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ አዲስ አበባ ፤ መርኃ ጥበብ ማተሚያ ቤት ፤ 1938 ዓ.ም.

———

የኢትዮጵያ ታሪክ ፤ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ (5ኛ እትም) አዲስ አበባ ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፤ 1965 ዓ.ም.

———

የግራኝ አህመድ ወረራ ፤
አዲስ አበባ ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፤ 1966 ዓ.ም.

**ታደሰ ዘወልዴ (ቀኛዝማች)**

ማይቱ ብጡል አዲስ አበባ ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት 1979 ዓ.ም.

**ታዬ ገብረ ማርያም (አለቃ)**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ፤ አዲስ አበባ ፤ ሴንትራል ማተሚያ ቤት ፤ 1964 ዓ.ም.

**ኃይለ ጊዮርጊስ ዘሐረር (ግራጌታ)**

ዜናሁ ለልዑል ራስ መኰንን ፤ አዲስ አበባ ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፡ 1965 ዓ.ም.

**ኃይለ ማርያም ሰራብዮን**

የኢትዮጵያ ትእምርተ መንግሥት ፡ ስንደቅ ዓላማና ዘውዱን የጃንሆይንም ዐዋጅ የሚናገር ፡ አዲስ አበባ ፡ ኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ፡ 1906 ዓ ም

**ኅሩይ ወልደ ሥላሴ (ብላቴን ጌታ)**

የኢትዮጵያ ታሪክ ፡ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዓድዋ ጦርነት (ያልታተመ)

---

የሕይወት ታሪክ

መጽሐፈ ቅኔ በኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በ1981 ዓ.ም

**ዐጥሜ (ዐጽመ ጊዮርጊስ)**

የጋላ ታሪክ (ያልታተመ)

**አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ (ነጋድራስ)**

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ፤ ሮማ ፡ 1901 ዓ ም

**ከበደ ተሰማ (ደጃዝማች)**

የታሪክ ማስታወሻ ፤ አዲስ አበባ ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፡ 1962 ዓ ም

**ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ (ጸሐፊ ትእዛዝ)**

ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ አዲስ አበባ ፡ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት ፡ 1959 ዓ ም



## ከውጭ አገር

Annaratore, C., **In Abyssinia.**
Bairu Tafla, **Ethiopia and Germany.**
Baratieri, O. Gen., **Memoire d' Afrique.**
Battaglia, R., **La Prima Guerra d'Africa.**
Bellavita, E., **Adua.**
Bureau, J., **Ethiopie: Un Drame Imperial Et Rouge.**
Cane Vari, E. & Comisso, E.H., **le Generale Tomaso Salsa.**
Crispi, F. & Palamenghi ,T., **La Prima Guerra d' Africa.**
Coulbeaux, J.B., **Histoire Politique et Religlenese d' Abyssinie, 2 tomes .**
De Coppet, M., **Chronique du Regne de Menelik II.**
Del Boca, A., **Gli Italiani in Afrca Orlentale.**
Giglio, C., **L'Italia In Africa: Ethiopla—Mar Rosso.**
Jones, A.H.M. e Monroe, **Histoire del' Abyssinie.**
Le Roux, H. **Menellk et Nous—**
Martini, F., **Diario Eritreo, Cose Africane.**
Mazzucconi, R., **La Giornata di Adua.**
Merab, P Dr., **Impressions d' Ethiopie.**
Milano, C.T.I., **Guida dell' Africa Orientale.**
Pankhurst, R. The Ethiopian Royal Chronicle.
Pantano, G.Gen., **Ventitre Anni di Vita Africana.**
Pierre—Alype, **L'Ethiopie et les Convoitises Allemandes.**
——————**'L'Empire des Negus.**
Prouty, C., **Empress Taytu and Menelik II.**
Rossini, C.C., **Italia ed Ethiopla,DAL Trattato d'Ucciaill alla Battaglia di Adua.**
Rossetti, C., **Storia Diplomatica Durante il Regno dl Menelik II.**
Sapelli, A., **Memorie d' Africa.**
Tedone, G., **Anghera.**
Vigneras, S., **Une Mission en Abyssinie .**
Ximenes, (ed.), **Sul Compo di Adua.**
Zaghi, C., **I Russi in Ethiopla,** 2Volume.
——————**,Crispi e Menelich nel Dlario Inedito del Conte A. Sallmbeni.**

## ያልታተሙ ሰነዶች
## UNPUBLISHED MATERIALS.

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ቤተመጽሐፍት ወመዘክር (ባሕል ሚኒስቴር)**

Public Records Office,
F.O. 40116 4249—F.0.403 (LONDON)

Archivio Storico del Sopresso Ministero dell'Africa Italiana.
Etiopia ,Posizione ,36—2—19—36 3—37—36 3—39... (ROMA)

Ministere des Affaires Etrangeres; Memoires e Documentsl Afrique
II. 106—107. Mer Rouge, V—VI
(1886—1887), 136—137, Mer Rouge, VII—Ix (1887—1895)
Collection de M.Mondon Vidaillet ... VII,Manuscrips ... B.M.
Mss Ethiopie 269 Mondon 82. (PARIS)